ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግብርና ዘርፍ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

## *(የመጨረሻ ረቂቅ ሰነድ)*

**ግብርና ሚኒስቴር**
**ሐምሌ 18/2014 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

## ማውጫ

ይዘት........................................................................................................ ገጽ
1. ድርሞ /Executive Summary/ .................................................................. 1
2. መግቢያ ................................................................................................ 6
3. ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ................................................ 6
3.1 የአነስተኛ ይዞታ አዝዕርት ልማት ............................................................. 7
3.2 የሆርቲካልቸር ሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ........................................... 8
3.3 የቡና ሻይና ቅመማቅመም ልማት ............................................................. 9
3.4 የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋት ......................................................... 10
4. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማትን ማሳደግ .................................... 11
4.1 የወተት ምርትና ምርታማነት .................................................................. 11
4.2 የቀይ ሥጋ፣ ቆዳ እና ሌጦ ምርትና ምርታማነት ............................................ 12
4.3 የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት ................................................. 12
4.4 የዓሳ ምርትና ምርታማነት ..................................................................... 12
4.5 የማር ምርትና ምርታማነት .................................................................... 13
4.6 የእንስሳትና ዓሳ መኖ ልማት ................................................................. 13
4.7 እንስሳትና ዓሳ ሀብት ዝርያ ማሻሻል ......................................................... 14
4.8 የተሻሻለ የእንስሳት በሽታ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት ................................ 15
4.9 የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ............................................................ 15
5. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ..................................................... 15
5.1. የተፋሰስ ልማት ................................................................................ 15
5.2 የአፈር ለምነት ................................................................................... 18
5.3. አፈር መረጃና ካርታ ........................................................................... 19
5.4. በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ......................................................... 20
5.5. አነስተኛ መስኖ ልማት ......................................................................... 21
6. ደን ልማት ......................................................................................... 21
7. ብዝሀ ሕይወት ..................................................................................... 22
8. የግብርና ኢንቨስትመንት ግብዓት አቅርቦትና ምርት ግብይት ................................. 23
8.1 የእርሻ ኢንቨስትመንት አፈፃፀም ............................................................. 23
8.2 የእንስሳት ኢንቨስትመንት አፈፃፀም .......................................................... 24
8.3 የሰብል ግብዓት አቅርቦት .................................................................... 25
8.4 የግብርና ሜካናይዜሽን ......................................................................... 26
8.5 የግብዓት ግዥ ፋይናንስ አቅርቦት ........................................................... 27
8.6 የግብርና ምርት ግብይት ........................................................................ 27
9. የግብርና ምርምር ................................................................................. 30
10. ህብረት ስራ ማህበራት ......................................................................... 32
11. ግብርና ትራንስፎርሜሽን ....................................................................... 34
12. የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማጠናከር ........................................................... 36
13. የግብርና ቁጥጥር ሥራዎች ..................................................................... 37
14. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ............................................................................. 39

14.1 የግብርና ዘርፍ የሥራ ዕድል ፈጠራ ........................................................................................ 39
14.2 የምግብ ዋስትና ........................................................................................................ 40
14.3 ምግብና ስርዓተ-ምግብ ................................................................................................. 41
14.4 የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ....................................................................................... 42
14.5 የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ .................................................................. 43
14.6 ኤች አይቪ ኤድስ ...................................................................................................... 44
15. የከተማ ግብርና ልማት ................................................................................................ 45
16. በክልሎች የተሠጠ ልዩ ድጋፍ ........................................................................................ 45
17. በተደጋጋሚ በድርቅ የሚጎዱ አካባቢዎችን ዘላቂ መፍትሄ መስጠት ........................................... 45
18. የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ........................................................................................... 46
19. የግብርና ሚኒስቴር የኦዲት ግኝት ምልከታ ........................................................................... 48
20. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ ............................................................................... 48
21. የፕሮግራሞችና ኢኒሽቲቮች አፈፃፀም ................................................................................... 49
22. ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ ..................................................................................... 50
23. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም......................................................................................... 52
24. ያጋጠሙ ተግዳሮቶች የተወሰዱ እርምጃዎችና በቀጣይ ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮች.......................... 65
25. ማጠቃለያ ............................................................................................................... 67
26. ቁልፍ የውጤት አመልካቾች ዝርዝር አፈፃፀም ........................................................................ 68
አባሪ አንድ: - የግብርና ቁልፍ የውጤት አመልካቾች ............................................................... 68
አባሪ ሁለት ፡- የ2014 ዓ.ም የግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት መደበኛ በጀት ዕቅድ አፈጻጸም ........................................................................................................................ 82
አባሪ ሦስት ፡- የ2014 ዓ.ም የግብርና ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማት የካፒታል በጀት ዕቅድ አፈጻጸም........................................................................................................................ 84

## 1. ድርሞ /Executive Summary/

ሀገራዊ የምግብና የኢንዱስትሪ ፍላጎትን የማርካትና የውጭ ምርቶችን አቅርቦት በመጨመር የውጪ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ ተቀናጅተው በተሰሩ የግብርና ንቅናቄ፣ የሰብል ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የግብዓት አጠቃቀም፣ የግብርና ሜካናይዜሽን፣ የነፍሳት ተባይና በሽታ መቆጣጠር፣ የዘር ብዜት፣ የእንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት አጠበበቅና አጠቃቃም፣ የግብርና ኢንቨስትመንት፣ ግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት፣ እንዲሁም የዘርፈ-ብዙ ሥራዎች በማከታት፣ ፕሮግራሞችና ኢኒሼቲቮችን በመንደፍ ከሚመለከታቸው የግብርና ሴክተር ተቋማትና የባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ ይገኛሉ፡፡

የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ቁጥር 11,982 ሺህ ለማድረስ ታቅዶ ከክልሎች በተሰበሰበ መረጃ መሰረት የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች 19,237 ሺህ (100+ በመቶ) ለማድረስ ተችሏል፡፡ በሰብል ልማት እና በእንስሳት ሀብት ልማት የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚዎች 7,804 ሺህ ለማድረስ ታቅዶ 8,281 ሺህ (100+ በመቶ) ደርሷል፡፡ የሞዴል አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር ለማሳደግ በታቀደው መሰረት የሰብል ልማት፣ የተፈጥሮ ሀብት እና የእንስሳት ሀብት ልማት የተጠቃሚዎችን 4,114 ሺህ ለማድረስ ታቅዶ 4,765 ሺህ (100+ በመቶ) ማድረስ ተችሏል፡፡

በአነስተኛ አርሶ አደሮች በ2013/14 ምርት ዘመን የመኸር እርሻ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በተደረገው ጥረት በአስተዳደራዊ መረጃ መሰረት 13,137 ሺህ ሄ/ር መሬት በተገቢው ድግግሞሽ ታርሶ 12,980 ሺህ ሄ/ር (ከዕቅዱ 98.1 በመቶ) መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከዚህም ውስጥ 2,040 ሄ/ር (ከታረሰው 16 በመቶ፣ እንዲሁም ከዕቅዱ 80 በመቶ) በዘመናዊ የእርሻ ትራክተር ለማስረስ ተችሏል፡፡ በዘር ከተሸፈነው ጠቅላላ መሬት ውስጥ 4,740 ሺህ ሄ/ር (37 በመቶ) በገበያ መር ኩታ-ገጠም እርሻ ዘዴ የለማ ሲሆን ከእቅዱ 85.3 በመቶ ተከናውኗል፡፡ በዋና ዋና ሰብሎች ሊደረስበት የተያዘው ዕቅድ 374 ሚ/ን ኩ/ል ሲሆን በቅድመ ምርት ግምት ትንበያ መሰረት 336.60 ሚ/ን ኩ/ል (90 በመቶ) ምርት ማምረት ተችሏል፡፡ ከውጪ የሚገባ የስንዴ ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በተደረገው ጥረት በመጀመሪያ ዙር የመስኖ ስንዴ ልማት በአማራ፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማና አፋር ክልሎች 400 ሺህ ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ በ1ኛው እና 2ኛው ዙር 450.17 ሺህ ሄ/ር (100+ በመቶ) መሬት ታርሶ ተዘርቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ 16 ሚ/ን ኩ/ል ለመሰብሰብ ታቅዶ 15.90 ሚ/ን (99.4 በመቶ) ኩ/ል ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ የምርት ዘመኑ የአነስተኛ አርሶ አደር የበልግ እርሻ ልማት አፈፃፀም በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልሎች 2,204 ሺህ ሄ/ር ለማረስ ታቅዶ 2,381 ሺህ (100+ በመቶ) ሄ/ር መሬት ታርሶ 1,909 ሺህ ሄ/ር በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከዚህም 46 ሚ/ን ኩ/ል ምርት ይጠበቃል፡፡ የምርጥ ዘር ብዜት ለማሳደግ በተከናወኑ ተግባራት በሀገር አቀፍ ደረጃ በምርጥ ዘር እንዲሸፈን ከተቃደው 97.84 ሺህ ሄ/ር ውስጥ 79.92 ሺህ ሄ/ር መሬት (81.7 በመቶ)

በምርጥ ዘር መሸፈን ተችሏል፡፡ በዘር ብዜት ከተሸፈነው መሬት ላይ 1.9 ሚ/ን ኩ/ል ምርጥ ዘር ለመሰብሰብ ታቅዶ 1.09 ሚ/ን ኩ/ል (57.4 በመቶ) ምርጥ ዘር ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

የሆርቲካልቸር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በመኸር በአትክልት ሰብሎች 1,178.98 ሺህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 1,118.08 ሺህ ቶን ምርት (94.8 በመቶ) ተመርቷል፡፡ እንዲሁም ምርታማነት 85 ኩ/ል በሄ/ር ታቅዶ 81.6 ኩ/ል በሄ/ር (96 በመቶ) ማድረስ ተችሏል፡፡ በፍራፍሬ ሰብሎች 1,561.16 ሺህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 1,419.24 ሺህ ቶን (90.91 በመቶ)፣ ምርታማነትን 90 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 87.89 ኩ/ል በሄ/ር (97.66 በመቶ) ማድረስ ተችሏል፡፡ በስራስር ሰብሎች 5,573.54 ሺህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 5,114.41 ሺህ ቶን (91.76 በመቶ)፣ እንዲሁም ምርታማነትን 212 ኩ/ል በሄ/ር ታቅዶ 208.53 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ ተችሏል፡፡ ፍራፍሬ ምርትን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪን ለማሳደግ የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን ምርት ከላኪዎች ጋር በማገናኘት 200 ቶን የአቮካዶ ምርት ለመላክ ታቅዶ ከአማራ ክልል 170 ቶን፣ ከኦሮሚያ ክልል 16 ቶን የአቮካዶ ምርት በድምሩ 186 ቶን (93 በመቶ) ወደ ውጭ እንዲላክ የማስተባበር ሥራዎች ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም በመኸር 144,410 (17,747 ሴት) አርሶ አደሮችን በማሳተፍ በ31,899 ሄ/ር ማሳ ላይ 79.747 ሚ/ን የእንሰት ችግኝ ተከላ የተከናወነ ሲሆን፣ ቀደም ሲል ከተተከለ ከ61,520 ሄ/ር የእንሰት ማሳ ላይ 18,287,531 ኩ/ል የእንሰት ምርት ተሰብስቧል፡፡

የእንስሳትና አሳ ምርትን ለማሳደግ በተከናወኑ ስራዎች 7,443 ሚ/ን ሊትር ወተት ለማምረት ታቅዶ 7,082.4 ሚ/ን (95.16 በመቶ) ለማምረት ተችሏል፡፡ በዝርዝር ከዳልጋ ከብት (የላም የወተት) ምርት 5,923 ሚ/ን ለማምረት ታቅዶ 5,751.05 (97.10 በመቶ) ፣ የፍየል ወተት 192 ሚ/ን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 227.39 (100+ በመቶ) ፣ የግመል 1,328 ሚ/ን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 1,103.96 ሚ/ን ሊትር (83.13 በመቶ) የወተት ምርት ለማግኘት ተችሏል፡፡ የሥጋ ምርት መጠን (ከዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ግመል) በድምሩ 431.52 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 447.77 ሺህ ቶን (100+ በመቶ) የሥጋ ምርት ለማግኘት የተቻለ ሲሆን፣ በዝርዝር ከዳልጋ ከብት 261፣ ከበግ 91፣ ከፍየል 78፣ ከግመል 1.39 ሺህ ቶን የሥጋ ምርት ታቅዶ ከዳልጋ ከብት 283.85፣ ከበግ 84.4፣ ከፍየል 78፣ ከግመል 1.52 ሺህ ቶን ሥጋ ምርት ተገኝቷል፡፡ የዚህም አፈፃፀም በተከታታይ የዳልጋ ከብት 100+ በመቶ፣ የበግ 92.75 በመቶ፣ የፍየል 100+ በመቶ፣ እና የግመል ሥጋ ምርት 100 በመቶ ተከናዉኗል፡፡ የዶሮ ስጋ 76 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 90.55 ሺህ ቶን (100+ በመቶ) ለማምረት የተቻለ ሲሆን እንቁላል 3,254.7 ሚ/ን ለማምረት ታቅዶ 3,246.54 ሚ/ን (99.75 በመቶ) ማምረት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 27 ሚ/ን ጫጩት ለማምረት ታቅዶ 27.93 ሚ/ን (100+ በመቶ) ለማምረት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 18.38 ሚ/ን ቆዳና ሌጦ ለማምረት ታቅዶ 18.33 ሚ/ን (99.73 በመቶ) ማምረት ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ ከዳልጋ ከብት ቆዳ 1.99 ሚ/ን፣ የበግ ሌጦ 8.68 ሚ/ን፣ የፍየል ሌጦ

7.71 ሚ/ን ታቅዶ የዳልጋ ከብት ቆዳ 2.46 ሚ/ን (100+ በመቶ) ፣ የበግ ሌጦ 8.96 ሚን (100+ በመቶ) እና የፍየል ሌጦ 6.91 ሚ/ን (89.62 በመቶ) ምርት ተመርቷል፡፡

በሶስተኛው የአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሀግብር (2013/14 በጀት ዓመት) "ኢትዮጵያን እናልብሳት" በሚል መሪ ቃል 6 ቢ/ን ችግኞች በአገር ውስጥና 1 ቢ/ን ችግኞች በጎረቤት አገራት ለመትከል ታቅዶ ከ6.75 ቢ/ን ችግኞች በላይ በሀገር ውስጥ የተተከለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100 በመቶ በላይ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ 3.02 ቢ/ን የደን ዛፍ፣ 3.3 ቢ/ን የጥምር ደን እርሻ፣ 371.9 ሚ/ን የፍራፍሬ እና 62.9 ሚ/ን ደግሞ የከተማ ውስጥ የተተከሉ ናቸው፡፡ በተካሄደው የችግኝ ተከላ 2.104 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ለመሸፈን የተከላ ቦታ ልየታ የተካሄደ ሲሆን፣ ከተወሰኑ ክልሎች በደረሰን መረጃ መሠረት የ304,257 ሄ/ር የመጠነ-ዙሪያ ልኬት የጂፒኤስ (Polygon Sides GPS) መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ይህም በጎግል ኧርዝ (Google Earth) ካርታ ላይ በማሳረፍ የተለያዩ አካላት ክትትል ሊያደርጉ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በጎረቤት አገራት ለሚደረግ ተከላ ችግኞቹን ለማጓጓዝ የሚያስፈልገውን ወጪ የኢትዮጵያ መንግስት የተሸፈነ ሲሆን ተከላው የተካሄደበት ሀገራት ኤርትራ 181,000፣ ሶማሊ ላንድና ፑንትላንድ ሶሚሊ 40,000 እና ጂቡቲ 40,000 በአጠቃላይ 261,000 የተለያዩ ችግኞችን ለማድረስ ተችሏል፡፡ የድህረ-ተከላ ስራዎችን በተመለከተ በሃገር አቀፍ ደረጃ ከተተከሉት 6.7 ቢ/ን ችግኞች ውስጥ ለ4.82 ቢ/ን ችግኞች የድህረ ተከላ ስራዎች የአረም፣ ኩትኳቶና ውሃ የማጠጣት ሥራዎች ተሰርቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ የተተከሉ ችግኞች አማካይ የጽድቀት መጠኔ 80.6 በመቶ መሆኑን በክልሎች በተካሄደ ምዘና መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአራተኛ አመት ተከላ (2014/15 በጀት ዓመት) 6 ቢ/ን ችግኞችን ለማዘጋጀትና ለመትከል ታቅዶ 7.6 ቢ/ን (100+) ችግኞች ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ 3.6 ቢ/ን (48 በመቶ) የደን ዛፍ፣ 1.6 ቢ/ን (52 በመቶ) የጥምር ደን-እርሻ ችግኞች ሲሆን 2.4 ቢ/ን የዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያለው ችግኝ ፣ 538.56 ሚ/ን የፍራፍሬ፣ 954.34 ሚ/ን የመኖ ዛፍ እንዲሁም 28.04 ሚ/ን ከተማ ውስጥ የሚተከሉ የውበት ዛፎች ናቸው፡፡ 2,200 ሺ.ህ ሄ/ር የተከላ ቦታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,644.04 (74.73 በመቶ) ሺ.ህ ሄ/ር ቦታ የተዘጋጀ ሲሆን፤ 51.5 ሺ.ህ ሄ/ር ቦታ ዙሪያ ልኬት ለመውሰድ ታቅዶ 102.86 (100+ በመቶ) ሺ.ህ ሄ/ር ተለክቷል፡፡ ተከላን በተመለከተ ከታቀደው 6 ቢ/ን ውስጥ 3.15 ቢ/ን (52.51 በመቶ) የተተከለ ሲሆን፤ 20 ሚ/ን ህዝብ በንቅናቄ ለማሳተፍ ታቅዶ 16.67 ሚ/ን (83.35 በመቶ) ተሳትፏል፡፡

የገጠር መሬት ልኬትና ምዝገባ ለማካሄድ 2.6 ሚ/ን ማሳ ታቅዶ ለ2.9 ሚ/ን (100+ በመቶ) ማሳዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ለ2.6 ሚ/ን ማሳዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ2.3 ሚ/ን (88.46 በመቶ) ማሳዎች ሠርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡ ለባለይዞታዎች የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለ0.74 ሚ/ን ባለይዞታዎች (0.52 ሚ/ን አባወራና 0.22 ሚ/ን እማወራ) ለመስጠት ታቅዶ ለ0.66 ሚ/ን (88.83 በመቶ) ባለይዞታዎች (0.46 ሚ/ን አባወራና 0.2 ሚ/ን እማወራ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡

የአነስተኛ ባለይዞታዎች የግብርና ውሀ አቅርቦትን ለማሳደግ በ2013 የተደረሰበትን 846.77 ሺህ ሄ/ር መነሻ በማድረግ በ2014 ዓ.ም ተጨማሪ 27.10 ሺህ ሄ/ር መሬት አዲስ ለመስኖ ልማት ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ 40.04 ሺህ ሄ/ር (100+ በመቶ) ዝግጁ ማድረግ ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ ከግብርና ምርቶች የውጪ ንግድ 2.98 ቢ/ን የአሜሪካ ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የወጪ ንግድ 72 በመቶ ሸፍኗል፡፡ ከዚህም ውስጥ የቡና ሻይና ቅመማቅመም 314,291 ቶን ምርት ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 312,196.20 (99.33 በመቶ) እና የሆርቲካልቸር 363,267 ቶን ምርት ታቅዶ 326,917 (89.99 በመቶ) ሲሆን፣ በድምሩ 677,558 ቶን ምርት ለመላክ ታቅዶ 639,113.20 (94.33 በመቶ) ተከናዉኗል፡፡ በተመሳሳይ ከስገኙት የአሜሪካን ዶለር ገቢ አንጻር ከቡና ሻይና ቅመማቅመም 1,155.33 ሚ/ን የአሜሪካ ዶላር ለማስገኘት ታቅዶ 1,443.26 (124.92) እና ከሆርቲካልቸር 589.90 ሚ/ን የአሜሪካ ዶላር ታቅዶ 628.58 (100+ በመቶ) በድምሩ 1,745.24 ሚ/ን ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ 2,071.84 (100+ በመቶ) ገቢ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪ ከስጋና ወተት ምርቶችና ሌሎች ውጤቶች፡- የበግና ፍየል ስጋ፣ የዳልጋ ከብት ስጋ፣ የእርድ ተረፈ-ምርት፣ የዓሣና ሌሎች ስጋ ምርት፣ ማር፣ ሰም ምርቶች (ወተትን ሣይጨምር) በጥቅሉ 18.938.28 ቶን ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 22,932.12 (100+ በመቶ) ተከናዉኗል፡፡ የወተት ምርትን በተመለከተ 1,229,300 ሊትር ታቅዶ 805,595 ሊትር (65.53 በመቶ) ወደ ውጭ መላክ ተችሏል፡፡ የስጋ፣ የወተት፣ የማር ምርቶችና ውጤቶች ባስገኙት የአሜሪካን ዶላር ገቢ ከበግና ፍየል ሥጋ ምርት በድምሩ 95.23 ሚ/ን ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ 120.64 (100+ በመቶ) ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ (ወተትን ሣይጨምር) ከላይ ከተዘረዘሩት የግብርና ምርት ውጤቶች 696,496.28 ቶን ወደ ውጪ ለመላክ ታቅዶ 662,045.33 ቶን (95.05 በመቶ) የተላከ ሲሆን፣ ከዚህም ወተትን ጨምሮ የ1,840.46 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2,192.48 ሚ/ን (100+ በመቶ) ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም የአቮካዶ ኤክስፖርትን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 2,910.38 ቶን ምርት ወደ ውጭ የተላከ ሲሆን 1,502,240.85 የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን ሜጫ ወረዳ እና አካባቢው የተሻሻለ የሀስ አቮካዶ ዝርያ በክላስተር በማምረት 170 ቶን ምርት ለመላክ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን በሉሜ ወረዳ የተሻሻለውን የሀስ ዝርያ አቮካዶ ምርትን በክላስተር በማምረት ለአውሮፓ ገበያ 18 ቶን የተላከ ሲሆን ይህ በጥሬው የተላከው ምርት በኪሎ ከ1.5 እስከ 2.8 የአሜሪካ ዶላር ተሸጧል፡፡

የበጀት አጠቃቀምን በሚመለከት ለሚ/ር መ/ቤቱ በ2014 በጀት ዓመቱ በመደበኛ 0.55 ቢ/ን በካፒታል 15.18 ቢ/ን ብር በድምሩ 15.72 ቢ/ን የተፈቀደ ቢሆንም በበጀት ዕጥረት ምክንያት ተጨማሪ ብር 900.55 ሚ/ን ተፈቅዷል፡፡ ይህም በአፈጻጸም ላይ ተጨምሮ መደበኛ በጀት 1.54 ቢ/ን ብር (100+ በመቶ) ፣ የካፒታል በጀት 18.67 ቢ/ን ብር (100+ በመቶ) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የ8ቱ ተጠሪ ተቋማት (የኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በስተቀር) የበጀት አጠቃቀም በመደበኛ 1.73 ቢ/ን

በካፒታል 0.53 ቢ/ን ብር በድምሩ 2.26 ቢ/ን የተፈቀደ ሲሆን አፈጻጸሙ መደበኛ በጀት 1.64 ቢ/ን ብር (94.63 በመቶ) ሲሆን የካፒታል በጀት ደግሞ 0.3 ቢ/ን ብር (56.32 በመቶ) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በመደበኛና በካፒታል አፈጻጸሙ 1.94 ቢ/ን ብር (85.62 በመቶ) ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ የግብርና ዘርፍ **የፊዝካል አፈጻጸም 90.39 በመቶ** - በጣም ከፍተኛ ደረጃ እና **አማካይ የበጀት አፈጻጸም በጣም ከፍተኛ** ደረጃ ሆኖ ተፈጽሟል፡፡

በዕቅድ ትግበራው ሂደት ወቅት ***ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን በሚመለከት፡-*** *ሀገራዊ የሰላምና ጸጥታ በአፈጻጸሙ ላይ ያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ፣ የውጪ ምንዛሬና የብድር እጥረትና የዓለም አቀፍ የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ መናር ጫና፣ የፕሮጀክት የግንባታ ግብዓቶች ዋጋ መናር፣ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው በሚመለከታቸው አካላት ቶሎ አለመጽደቅ እና የክልሎችና የፌዴራል ተቋማዊ አደረጃጀት አለማናበብ በሥራው ላይ ተጽእኖ ያሳደሩ ሲሆን፣* ***ተግዳሮቶቹን ለመፍታት፡-*** *በአንጻራዊ ሰላሙ ያለበቸውን አከባቢዎችን በጥናት በመለየት የማካካሻ ዕቅድ ተዘጋጅቶ የመንግስትና የባለድርሻ አካላትን፣ እንዲሁም አመራሩና ፈጻሚው ርብርብ አድርጎ በማስተባበር ድጋፍ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡ የማዳበሪያ የዋጋ ንረትን አርሶአደሩ መቋቋም እንዲችል የፌዴራል መንግስት 15 ቢ/ን ብር ድጎማ አድርጓል፡፡ የፕሮጀክቶች ዋጋ መናርን ለማሻሻልም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የግንባታ ግብዓቶች በተለይም ሲሚንቶ በተደራጁ ማህበራት በቀጥታ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርብ ጥረት ተደርጓል፡፡ የህግ ማዕቀፎች ቶሎ እንዲጸድቁ አስቸኳይ የሆኑትን በመለየት በህዝብ ተወካዮች የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት እና ከፍትህ ሚ/ር ጋር በቅርበት እየተሰራ ይገኛል፡፡ የአደረጃጀት ማነቆን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር እየተሰራ ይገኛል፡፡*

## 2. መግቢያ

የ2014 ዓመታዊ ዕቅድ የዘርፉን ቁልፍ የውጤት መስኮችና ውጤቶችን ለማሳካት የሚያስችሉ የትግበራ መስኮችን መሰረት በማድረግና ግልፅ ዒላማዎችን በማስቀመጥ ዒላማዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ የማስፈጸሚያ ስልቶችን በማካተት እንዲዘጋጅ በማድረግና በዕቅዱ ላይ የሚመለከታቸውን የፌዴራልና የክልል ፈፃሚ አካላት ጋር መግባባት ላይ በመድረስ ተተግብሯል፡፡

ሀገራዊ ለውጡን በመከተል የአሠራር፣ የአደረጃጀትና የሰው ሃይል ልማት ሥራዎችም ተጠናክሮ በመሰራት ላይ ሲሆኑ፣ የልማት ዕቅድን በሚመለከት በትኩረት የ10 ዓመት ዕቅድንም ሆነ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶችን ወደ መሬት የምናወርድበት ዋናው መሳሪያ ዓመታዊ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት ነው፡፡ የ2014 ዓመታዊ የልማት ዕቅድ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ ዓላማዎችን፣ ግቦችንና የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የሚረዱ የማስፈጸሚያ ስልቶችን በማካተት ተከናዉኗል፡፡

ለበጀት ዓመቱ ልማት ዕቅድ አመራሩና ፈጻሚው የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በቁልፍ የውጤት አመልካቾች፣ በፕሮግራም በጀት፣ በአዲት ግኝትና የዕርምት ሥራዎች፣ የተቋማት አደረጃጀትና የሪፎርም ሥራዎች፣ ለክልሎች የተሰጡ ድጋፎች እና ፕሮግራሞችና ኢኒሽቲቮችን ተለይተው በትኩረት እንዲተገባሩ ተደርጓል፡፡

ዓመታዊ ሪፖርቱ በአራት የዘርፉ ስትራቴጅክ ዓላማዎች፣ የሰብል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት ማስፋፋት እና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ተግበራት፣ የስራ ዕድል ፈጠራን በቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች፣ የስኬት መስኮች እና የዘርፈብዙ ጉዳዮችን በማካተት አፈፃፀምን በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

የሪፖርት ይዘቱም ድርሞ፣ መግቢያ፣ የቁልፍ የውጤት አመልካቾች አፈፃፀም፣ ፕሮግራም በጀት፣ ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ፣ የተቋማት አደረጃጀትና የሪፎርም ስራዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ኢኒሽቲቮችን፣ ያጋጣሙ ተግዳሮቶችና የመፍትሄ ሀሳቦችን እና ማጠቃለያ አካቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ይህ ሪፖርት የተዘጋጀው የአፈፃፀም መረጃዎችን ከየፈፃሚ አካላት በተሰበሰበ አስተዳደራዊ መረጃ የተዘጋጀ ሲሆን የሰብልና እንስሳትና ዓሳ ምርት ሪፖርት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ዓመታዊ የዳሰሳ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ሲወጣ ለውጦች የሚኖሩ ከሆነ ሪፖርት ተስተካክሎ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

## 3. ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የአነስተኛ ይዞታ አዝዕርት የመኸር እና በልግ እርሻ፣ የአነስተኛ ይዞታ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ፣ የቡና ሻይና ቅመማቅመም ልማት እንዲሁም የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋት ያካትታል፡፡

## 3.1 የአነስተኛ ይዞታ አዝዕርት ልማት

በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች በ2012/13 ምርት ዘመን የነበረውን የመኸር ሰብል ልማት ማስጠበቅና የኩታ ገጠም እርሻን በማጠናከርና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ በተለይም የቅድመና ድህረ ምርት ማሰባሰቢያ ማሽነሪዎችን ጥቅም እንዲውሉ እና የበጋ መስኖ በተላይም ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በሰፊው ታቅዶ በትኩረት በመስራት በሁሉም መስኖ ስንዴ የተዘራባቸው ክልሎች ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ በመስጠት ተከናውኗል፡፡

በዚሁ መሠረት በምርት ዘመኑ በመኸር 13,230 ሺህ ሄ/ር መሬት በተገቢው ድግግሞሽ ታርሶ በዘር ለመሸፈን ታቅዶ 13,137 ሺህ ሄ/ር (99.23 በመቶ) በዘር የተሸፈነ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 2,550 ሺህ ሄ/ር በዘመናዊ የእርሻ ትራክተር ለማረስ ታቅዶ 2,040 ሺህ ሄ/ር (80 በመቶ) ታርሶና በአግባቡ ተዘጋጅቶ፤ 12,980 ሺህ ሄ/ር (98.11 በመቶ) መሬት በዘር መሸፈን የተቻለ ሲሆን ቀሪው መሬት ግን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው የፀጥታ ችግር መረጃዎችን ማግኘት ስላልተቻለ አፈፃፀም ሪፖርቱ ውስጥ ባለመካተቱ አፈፃፀሙ በሚፈለገው ደረጃ እንዳይደርስ አድርጎታል፡፡ በዘር ከተሸፈነው ጠቅላላ መሬት 5,560 ሺህ ሄ/ር በክላስተር ለመማረስ ታቅዶ 4,740 ሺህ ሄ/ር (85.25 በመቶ) የተከናወነ ሲሆን ጠቅላላ ከታረሰው መሬት በኩታ-ገጠም እርሻ ዘዴ (ክላስተር) የታረሰው 37 በመቶ ይሸፍናል፡፡ በ2013/14 ምርት ዘመን በዋና ዋና ሰብሎች ሊደረስበት የተያዘው ዕቅድ 374 ሚ/ን ኩ/ል ለማምረት ታቅዶ በግብርና ምርት ቅድመ-ትንበያ ግምት መሰረት የትግራይ ክልልን ሳይጨምር 336.6 ሚ/ን (90 በመቶ) ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

የምርጥ ዘር ብዜት በተመለከተ በሀገር አቀፍ ደረጃ በምርጥ ዘር እንዲሸፈን ከተያዘው 97.84 ሺህ ሄ/ር በምርጥ ዘር ብዜት ለመሸፈን ታቅዶ 79.92 ሺህ ሄ/ር መሬት (81.68 በመቶ) ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዘር ብዜት ከተሸፈነው መሬት ላይ 1.9 ሚ/ን ኩ/ል ምርጥ ዘር ለመሰብሰብ ታቅዶ ሪፖርቱ እስከተዘጋጀበት ድረስ 1.09 ሚ/ን (57.37 በመቶ) ኩ/ል ምርጥ ዘር ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በዕቅዱ መሰረት ላለፈፀሙ ምክንያት በአንድአንድ ዘር አምራች ክልሎች በፀጥታ ችግር ምክንያት የተባዛ ዘር ማሰባሰብ ያለመቻል ነው፡፡

በሀገር ደረጃ ያለውን የስንዴ እጥረት ለመቅረፍ እና ከውጪ የሚገባውን ምርት ለመተካት በመጀመሪያ ዙር የመስኖ ስንዴ ልማት በአማራ፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማና አፋር ክልሎች 400 ሺህ ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ በ1ኛው እና 2ኛው ዙር 450.17 ሺህ ሄ/ር (112.54 በመቶ) (በ1ኛ ዙር 405.726 ሄ/ር እና በ2ኛ ዙር 44.291 ሄ/ር) መሬት ታርሶ ተዘርቷል፡፡ የተገኘ ምርትን በሚመለከት 16 ሚ/ን ኩ/ል ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ1ኛ ዙር 391.515 ሺህ ሄ/ር ላይ 14.473 ሚ/ን ኩ/ል እና ከ2ኛው ዙር 40.573 ሺህ ሄ/ር ላይ 1.429 ሚ/ን ኩ/ል በድምሩ ከ432.088 ሺህ ሄ/ር ላይ 15.90 ሚ/ን (99.38 በመቶ) ኩ/ል ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል በተገኘው ሪፖርት መሰረት

በበልግ 259.719 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት እየለማ ሲሆን በአንደኛና ሁለተኛ ዙር መስኖ ከለማው 393.647 ሺ.ህ ሄ/ር ጋር በድምሩ 653.366 ሄ/ር ለምቷል። በኦሮሚያ በበልግ ከለማው 259.719 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት በአማካይ ምርታማነት በሄ/ር ተወስዶ ሲሰላ 9,349,866 ኩ/ል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡ ፡ ይህ የመስኖ ስንዴ ልማት አፈጻጸም አምና በተመሳሳይ ወቅት ከለማው 168.630 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት ጋር ሲጻጸር የ484.736 ሺ.ህ ሄ/ር ብልጫ አለው።

በምርት ዘመኑ የበልግ እርሻ ልማት አፈፃፀም በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፤ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች 2,204 ሺ.ህ ሄ/ር ታቅዶ 2,381 ሺ.ህ (100+ በመቶ) ሄ/ር መሬት ታርሶ 1,910 ሺ.ህ ሄ/ር (86.66 በመቶ) መሬት መሬት በዘር ተሸፍኗል። ከዚህም 46 ሚ/ን ኩ/ል ምርት ይጠበቃል። ለዕቅድ አፈጻጸም ማነስ ዋና ምክንያት የበልግ ዝናብ መዘግየትና ዝናብ በጀመረባቸው አካባቢዎች ደግሞ መልሶ ማቋረጡ ነው።

## 3.2 የሆርቲካልቸር ሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

በመኸር አትክልት ልማትን በተመለከተ በአነስተኛ አርሶአደር ይለማል ተብሎ የታቀደው 138.7 ሺ.ህ ሄ/ር ሲሆን 137 ሺ.ህ ሄ/ር ማሳ (98.77 በመቶ) ማልማት ተችሏል። በመኸር በአትክልት ሰብሎች 1,178.98 ሺ.ህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 1,118.08 ሺ.ህ ቶን ምርት (94.83 በመቶ) ተከናውኗል፤ እንዲሁም ምርታማነት 85 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 81.6 ኩ/ል በሄ/ር (96 በመቶ) የተከናወነ ሲሆን ይህም ከ2012/13 ምርት ዘመን ጋር ሲነፃፀር በመሬት 8.8 በመቶ እና በምርት 9.75 በመቶ መጨመሩን ያሳያል። በፍራፍሬ ሰብሎች 173 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 161 ሺ.ህ ሄ/ር (93 በመቶ) መሬት ማልማት ተችሏል። እንዲሁም ምርታማነትን 90 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 87.89 ኩ/ል በሄ/ር (97.66 በመቶ) የተከናወነ ሲሆን ከ2012/13 ምርት ዘመን ጋር ሲነፃፀር በመሬት 31.75 በመቶ እና በምርት 22.28 በመቶ መጨመሩን ያሳያል። በስራስር ሰብሎች 5,573.54 ሺ.ህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 5,114.41 ሺ.ህ ቶን (91.76 በመቶ) እንዲሁም ምርታማነትን 212 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 208.53 ኩ/ል በሄ/ር የተከናወነ ሲሆን፣ ከ2012/13 ምርት ዘመን ጋር ሲነፃፀር በአማካይ በመሬት 39.76 በመቶ እና በምርት 70.03 በመቶ መጨመሩን ያሳያል።

በመኸር 144,410 (17,747 ሴት) አርሶ አደሮችን በማሳተፍ በ31,899 ሄ/ር ማሳ ላይ 79.747 ሚ/ን የእንሰት ችግኝ ተከላ የተከናወነ ሲሆን፣ ቀደም ሲል ከተተከለው ከ61,520 ሄ/ር የእንሰት ማሳ ላይ 18,287,531 ኩ/ል የእንሰት ምርት ተሰብስቧል። በ2013/14 መኸር ወቅት የአረንጓዴ አሻራ ልማትን ለማጠናከር በፍራፍሬ ተከላ ሰፊ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ከክልሎች በተገኘው መረጃ ከተዘጋጀው 83,557,454 ችግኝ ውስጥ 83,554,515 ችግኞች (99.9 በመቶ) ተከላ ተከናውኗል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ካለው የውሃ አማራጭ አኳያ በሆርቲካልቸር ልማት 587,037 ሄ/ር በማልማት 101,374,911 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ የነበረ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ ከክልሎች በደረሰን

አስተዳደራዊ መረጃ መሰረት በድምሩ 2,395,036 (476,513 ሴት) አርሶ አደሮችን በማሳተፍ እና 1,169,120 ኩ/ል ማዳበሪያ፣ 197,325.5 ቶን ኮምፖስት እና 2,505,079 ኩ/ል ምርጥ ዘር (ከዚህ ውስጥ 2,250,636 ኩ/ል ስራስር ሰብሎች ኮረት)፣ እንዲሁም 24,780,250 የስኳር ድንች ቁርጥራጭ ጥቅም ላይ መዋሉን እንዲሁም 1,050,409.69 ሄ/ር ማሳ በማዘጋጀት 1,021,649.91 ሄ/ር በዘር ተሸፍኗል። ይህም እንደ ሀገር ከተያዘው የሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት ዕቅድ አኳያ ከ100 በመቶ በላይ የተከናወነ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፣ ክልሎች ይለማል ብለው ከያዙት ዓመታዊ ዕቅድ አኳያ 87.98 በመቶ ተፈፅሟል። ከምርት አሰባሰብ አንፃር የ1ኛ ዙር መስኖ ልማት ዕቅድ 101,374,901 ኩ/ል ምርት ሲሆን፣ ከ543,336 ሄ/ር ማሳ ላይ 93,115,510 ኩ/ል (91.8 በመቶ) ምርት ተሰብስቧል።

በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት የ2ኛ ዙር መስኖ ልማት በመልማት ላይ ያለና ምርት በመስብሰብ ሂደት ላይ ሲሆን እስካሁን ድረስ ከደቡብ፣ ሲዳማ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና አማራ ክልሎች 326,429 (73,158 ሴት) አርሶ አደሮችን በማሳተፍ 103,127.35 ኩ/ል ማዳበሪያ፣ 385 ቶን ኮምፖስት እና 255,995.4 ኩ/ል የአትክልት እና ስራስር ምርጥ ዘር (ከዚህ ውስጥ 142,025.85 ኩ/ል አትክልት፣ 128,416 ኩ/ል ስራስር እና 6,380,000 ቁርጥራጭ) በመጠቀም ከተዘጋጀው 77,352.07 ሄ/ር ውስጥ 63,2797 ሄ/ር በዘር ተሸፍኗል።

## 3.3 የቡና ሻይና ቅመማቅመም ልማት

የቡና ማሣ ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በመፈፀም በአነስተኛ አርሶ አደር እና በባለሀብት 794.23 ሺ.ህ ሄ/ር ማሳ በማልማት በ7.15 አማካይ ምርታማነት 12.35 ሚ/ን ኩ/ል የቡና ምርት ለማምረት ታቅዶ በባለስልጣኑ በተካሄደዉ የቡና ቅድመ-ምርት ትመና ፈጣን ዳሰሳ ጥናት መሰረት 931.73 ሺ.ህ ሄ/ር ማሳ (100+ በመቶ) ላይ በ7.5 ኩ/ል በሄ/ር ምርታማነት 6.52 ሚ/ን ኩ/ል ምርት እንደሚገኝ ተገምቷል። በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት በተወሰኑ የቡና አብቃይ አካባቢዎች የቡና በሽታ መከሰት በምርታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ አፈፃፀሙ አነስተኛ ሊሆን ችሏል።

በአልሚ ባለሀብቶች እና በአውት ግሮወርስ ከ3.26 ሺ.ህ ሄ/ር ማሳ ላይ በ31.80 ኩ/ል/ በሄ/ር አማካይ ምርታማነት 11.95 ሺ.ህ ቶን የቡና ምርት ለማምረት ታቅዶ በ27.33 ኩ/ል/ በሄ/ር አማካይ ምርታማነት 10.34 ሺ.ህ ቶን (86.49 በመቶ) ምርት ማምረት ተችሏል።

የቅመማ ቅመም ምርታማነት በማሳደግ ረገድ በቅመማ ቅመም ክላስተር በታቀፉ እና ዳይቨርሲፋይ በሚያደርጉ አካባቢዎች 454.86 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት የማሳ ሽፋን በማልማት እና ምርት መስጠት ከሚችለዉ 451.97 ሺ.ህ ሄ/ር ላይ የእንክብካቤ ስራዎችን በማከናወን በዋና ዋና የቅመማ ቅመም ምርቶች 744.80 ሺ.ህ ቶን ለማድረስ ታቅዶ በተለያዩ ዋና ዋና ቅመማ ቅመሞች 451.97 ሺ.ህ ሄ/ር (99.36 በመቶ) በማልማት በ15.8 ኩል/ በሄር አማካይ ምርታማነት 715 ሺ.ህ ቶን (96 በመቶ) ምርት ተሰብስቧል።

### 3.4 የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋት

በ250 ወረዳዎች ላይ የበረሃ አንበጣ አሰሳና መከላከል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ70 ወረዳዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ በበጀት ዓመቱ በአምስት ክልሎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር (አፋር፣ ኦሮሚያ ፣ ሶማሌ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር) በአውሮፕላንና በተሽከርካሪ በ4,937,964 ሄ/ር ላይ የአሰሳ ሥራ ተሰርቶ በ50,358 ሄ/ር ላይ የተከሰተውን የበረሃ አንበጣ በሰብልም ሆነ በግጦሽ ላይ ጉዳት ከማድረሱ በፊት በአውሮፕላን 10,890 ሄ/ር እና በግራውንድ 225 ሄ/ር በድምሩ 11,115 ሄ/ር በማደግ ላይ ያለ (Immature) እና ያደገ (Mature) የበረሃ አንበጣ መንጋ ላይ የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡ በአጠቃላይ ለቁጥጥር ሥራው 10,977 ሊትር ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በዓመቱ 12 የግሪሳ ወፍ መራቢያ ስፍራዎች በመለየት ለመከላከል ታቅዶ በ19 (100⁺ በመቶ) ተከናውኗል፡፡ በአፋር ክልል በ5 ወረዳዎች (አዋሽ ፈንታሌ፣ አሚባራ፣ ገለአሎ፣ ሀሩቃ እና ገዋኔ) በ9 የመራቢያ ስፍራ እና በኦሮሚያ ክልል 4 ወረዳዎች (አዳሚ ቱሉ፣ ዱግዳ፣ ሊበን ጭቋላ እና ሉሜ) 10 የመራቢያ ስፍራዎች የልየታ ስራ ተከናውኗል፡፡ የግሪሳ ወፍ ክትትል፤ አሰሳና የመከላከል ስራ በ30 ማደሪያ ስፍራዎች ለማከናወን ታቅዶ 29 የማደሪያ ስፍራዎች ላይ 74 ሚ/ን የሚገመት የግሪሳ ወፍ የተከሰተ ሲሆን፣ 1,000 ሊትር የፀረ-ወፍ ኬሚካል በመጠቀም በ500 ሄ/ር (100⁺ በመቶ) ላይ የመከላከል ስራ ተከናውኗል፡፡

በ60 ወረዳዎች የአዲሱ መጤ ተምች ክትትል፣ አሰሳና መከላከል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በ72 ወረዳዎች (100⁺ በመቶ) በአማራ ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ክልሎች ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ593,354 ሄ/ር የተከሰተውን የአዲሱ መጤ ተምች በባህላዊ 332,894 ሄ/ር እና በኬሚካል በ114,258 ሄ/ር በድምሩ በ447,152 ሄ/ር መሬት ላይ የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡ ጥቅም ላይ የዋለ ኬሚካል 120,404 ሊትር ነው፡፡

የመደበኛ ተምች በ7 ክልል (ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ፣ ጋምቤላ፣ አማራ፣ ሲዳማ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ) ፣ በ25 ዞኖች እና በ113 ወረዳዎች ላይ ተከስቶ ቁጥጥር በመደረግ ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ በሁሉም ክልሎች 111,361 ሄ/ር መሬት በተባዩ የተወረረ ሲሆን በተደረገው የመከላከል ስራም በባህላዊ 20,058 ሄ/ር እና በኬሚካል 38,387 ሄ/ር በድምሩ በ606,699 ሄ/ር መሬት ላይ የተከሰተውን ተባይ መከላከል የተቻለ ሲሆን ጥቅም ላይ የዋለ ኬሚካልም 36,716 ሊትር ነው፡፡

የዕፅዋት በሽታዎችን አሰሳና መከላከል በመስኖ፣ በልግና መኸር ወቅት በ211 ወረዳዎች ላይ ለማከናወን ታቅዶ በ293 (በስንዴ ዋግ 77 ወረዳዎች፣ በቲማቲምና ድንች ብላይት በ42 ወረዳዎች፣ በበቆሎ ገዳይ ቫይረስ በሽታ 49 ወረዳዎች፣ በአገዳና ብርዕ ሰብሎች የአረማሞ በሽታ ዳሰሳ ጥናት መረጃ ማሰባሰብ መተንተን እና ክትትልና ድጋፍ 74 ወረዳዎች (100 በመቶ) ላይ ተከናውኗል፡፡

መጤ አረም ቁጥጥርና መከላከል መመሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተከለሰውን ማፀደቅና የቁጥጥርና መከላከል ሠነዱን ተግባራዊ እንዲሆን መከታተል በእቅድ የተያዘ ሲሆን የቁጥጥርና መከላከል መመሪያው ለሚመለከታው አካል ቀርቧል። የዕፅዋት ነፍሳት ተባዮችን አሰሳና መከላከል በመስኖና በመኸር ወቅት በ45 ወረዳዎች ለማካሄድ ታቅዶ በ40 ወረዳዎች (87 በመቶ) በኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕረብ ኢትዮጵያ ህዝቦች፣ አማራ እና ደቡብ ክልሎች ተከናውኗል።

በ7 (ሰባት) ነባርና አንድ አዲስ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ግንባታ ጥናት ለማካሄድ በጀት ማፈላለግ ታቅዶ 6 የአወሮፕላን ማረፊያ ሜዳ (ሽዋሮቢት፣ መቂ፣ ኮንሶ፣ መልካ ሰዲ፣ ኑራይኔ፣ ዶደታ) የማስጠረግ ስራ ተሰርቷል። አንድ ነባርና አንድ አዲስ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ የጥገና ግንባታ ታቅዶ ሁለት የአውሮፕላን ሜዳ ጠረጋ (መልካ ሰዲ እና ዶዶታ) ተከናውኗል። 380,000 ሊትር ለወረርሺኝ ተባዮች መከላከል የሚውል የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግዢ ለማካሄድ ታቅዶ 564,217 ሊትር (100 በመቶ) ግኘ ተፈጽሟል።

ኢትዮጵያ አባል ከሆነችባቸው 4 ዓለም አቀፍ ድርጅቶች (ለምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከል፣ CRC፣ DLCC and CABI ድርጅቶች) ዓመታዊ መዋጮን ለመክፈል 4 በዕቅድ ተይዞ 4ቱም ተከናውኗል።

የእርሻና ሆርቲካልር ልማት ተግባራት ሊያሳልጡ የሚችሉ የሕግ ማዕቀፎችና አሰራሮች መዘርጋትና ማሻሻልን በተመለከተ ሀገራዊ የስንዴ ሰብል የልማት ፕሮግራሞ ረቂቅ ሰነድ ለሚመለከታቸው አጋር አካላት ቀርቦ ተተችቷል። በ3 አዳዲስ በስነ-ምግብ ይዘታቸው ጠቃሚ የሆኑ ሰብሎች (የምግብ ሲናር፣ ኩኒዋ እና ከሜላና) የአመራረትና የአመጋገብ ፓኬጅ ተዘጋጅቷል። የአርሶና አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት መመሪያ፣ የልማት አካላት የአፈጻጸም መመሪያ፣ የአርብቶ አደር ኤክስቴንሽን ሥርዓት፣ የግብርናዉ ዘርፍ የሙያ ደረጃዎች ቀረጻ እና ክለሳ፣ ስትራቴጂክ በሆኑ የተባዮች መራቢያና መግቢያ በሮች አካባቢ ማዕከላት(Base) የማቋቋሚያ ጥናት የጥናት ዶክመንት ተዘጋጅቶ ለውሳኔ ቀርቦ ፀድቋል።

## 4. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማትን ማሳደግ

### 4.1 የወተት ምርትና ምርታማነት

በዓመቱ 7,443 ሚ/ን ሊትር ወተት ለማምረት ታቅዶ 7,082.40 (95.16 በመቶ) ለማምረት ተችሏል። በዝርዝር ከዳልጋ ከብት የላም የወተት ምርት 5,923 ሚ/ን ለማምረት ታቅዶ 5,751.05 ሚ/ን (97.10 በመቶ) ፣ የፍየል ወተት 192 ሚ/ን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 227.39 ሚ/ን (100+ በመቶ) ፣ የግመል 1328 ሚ/ን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 1,103.96 ሚ/ን ሊትር (83.13 በመቶ) የወተት ምርት ለማግኘት ተችሏል። የግመል ወተት ምርት ዝቅ ያለበት ምክንያት በቦረና እና በሶማሌ አካባቢ ድርቅ በመከሰቱ ምክንያት ነው።

## 4.2 የቀይ ሥጋ፣ ቆዳ እና ሌጦ ምርትና ምርታማነት

በ2014 በጀት ዓመት የሥጋ ምርት መጠን (ከዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ግመል) በድምሩ 431.52 ሺ.ህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 447.77 ሺ.ህ ቶን (100⁺ በመቶ) የሥጋ ምርት ለማግኘት የተቻለ ሲሆን፣ በዝርዝር ከዳልጋ ከብት 261፣ ከበግ 91፣ ከፍየል 78፣ ከግመል 1.52 ሺ.ህ ቶን የሥጋ ምርት ለማምረት ታቅዶ ከዳልጋ ከብት 283.85፣ ከበግ 84.40፣ ከፍየል 78፣ ከግመል 1.52 ሺ.ህ ቶን ሥጋ ምርት ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ በቅደም ተከተል የዳልጋ ከብት 100⁺በመቶ፣ የበግ 92.75 በመቶ የፍየል 100 በመቶ የግመል ሥጋ ምርት 100 በመቶ ነው፡፡

በዕቅድ ዘመኑ 18.38 ሚ/ን ቆዳና ሌጦ ለማምረት ታቅዶ 18.33 ሚ/ን (99.73 በመቶ) ማምረት ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ ከዳልጋ ከብት ቆዳ 1.99 ሚ/ን፣ የበግ ሌጦ 8.68 ሚ/ን፣ የፍየል ሌጦ 7.71 ሚ/ን ታቅዶ የዳልጋ ከብት ቆዳ 2.46 ሚ/ን (100⁺ በመቶ) ፣ የበግ ሌጦ 8.96 ሚ/ን (100⁺ በመቶ) እና የፍየል ሌጦ 6.91 ሚ/ን (89.62 በመቶ) ምርት ተመርቷል፡፡

## 4.3 የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት

በዓመቱ የዶሮ ስጋ 78 ሺ.ህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 90.55 ሺ.ህ ቶን (100⁺ በመቶ) ለማምረት የተቻለ ሲሆን እንቁላል 3,254.70 ሚ/ን ለማምረት ታቅዶ 3,246.54 ሚ/ን (99.75 በመቶ) ማምረት ተችሏል፡፡ 27 ሚ/ን ጫጩት ለማምረት ታቅዶ 27.93 ሚ/ን (100⁺ በመቶ) ማምረት ተችሏል፡፡

## 4.4 የዓሳ ምርትና ምርታማነት

በ2014 በጀት ዓመት ከሀይቆች፣ከግድቦችና ትንንሽ ውሀ አካላት፣ ከወንዞች፣ ከዓሣ ግብርና (ኩሬ) በአጠቃላይ 78.95 ሺ.ህ ቶን የዓሣ ምርት ለማምረት ታቅዶ በአጠቃላይ 73.14 ሺ.ህ ቶን (92.64 በመቶ) ዓሣ ምርት ማምረት ተችሏል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት የደረቅ ዓሣና/በጨው የተዘጋጀ የዓሳ ምርት ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ 3.5 ሺ.ህ ቶን የደረቅ ዓሣ አፈጻጸሙ 3.10 ሺ.ህ ቶን እና በጨው የተዘጋጀ 0.6 ሺ.ህ ቶን ታቅዶ አፈጻጸሙ 0.5 ሺ.ህ ቶን በድምሩ 3.6 ሺ.ህ ቶን (87.81 በመቶ) ተመርቷል፡፡ በዓመቱ የዓሣ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በአርሶ አደር፣ በሀይቅና ግድቦች (Stock Enhancment) 1.15 ሚ/ን የዓሳ ጫጩት ለመጨመር ታቅዶ 1.08 ሚ/ን ጫጩት (93.83 በመቶ) ስርጭት ተከናውኗል፡፡ ለዓሳ ዕርባታ የተዘጋጁ አዳዲስ የዓሳ ኩሬዎች ብዛት 1,800 ታቅዶ 1,520 (84.44 በመቶ) የዓሣ እርባታ ኩሬዎች ተቆፍሯል፡፡ የህብረተሰቡን በተለይም የሴቶችና ወጣቶቸን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ እርካታ ማሳደግን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ በሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና በዓሣ ግብርና የዓሳ ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ አስጋሪዎችና አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር 15,000 ለማድረስ ታቅዶ በዓሣ ሀብት ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚዎች 13,900 (92.67 በመቶ) ለማድረስ ተችሏል፡፡

### 4.5 የማር ምርትና ምርታማነት

በዓመቱ 138 ሺህ ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ 146.70 ሺህ ቶን (100+ በመቶ) ማር ተመርቷል፡፡ እንዲሁም የሐር ኮኮን ምርት 40 ቶን ታቅዶ 36.69 ቶን (91.73 በመቶ) ተመርቷል፡፡
የሽግግር ቀፎ 974,455 ለማሰራጨት ታቅዶ 856,735 (87.92 በመቶ) ፣ የፍሬም ቀፎ 258,256 ታቅዶ 270,861 (100+ በመቶ) ተሰራጭቷል፡፡ የንግስት ንብ ለማባዛት 144 ሺህ በቁጥር ታቅዶ 114.2 ሺህ (79.31 በመቶ) ማባዛት ተችሏል፡፡ በቁጥር 658 ሺህ ህብረ-ንብ ወደ ሽግግርና ወደ ፍሬም ቀፎ ለማዛወር ታቅዶ 445 ሺህ (67.63 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ የሐር ትል እንቁላል 15 ሚ/ን ለማሰራጨት ታቅዶ 13.7 ሚ/ን (91.33 በመቶ) ተሰራጭቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የሐር ትል እንቁላል ስርጭት በፕሮጀክት የተደገፈ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከፍ ሊል ችሏል፡፡ የለማ የሐር ትል መኖ (የጉሎ መሬት ስፋት) 200 ሄ/ር ታቅዶ 112.5 ሄ/ር (56.25 በመቶ) ተከናዉኗል፡፡

### 4.6 የእንስሳትና ዓሳ መኖ ልማት

ከሁሉም የእንስሳት መኖ ምንጮች (የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርት፣ ከተሻሻለ የመኖ ዕፅዋት ልማት፣ ከኢንዱስትሪ መኖ ልማት፣ ከወልና ከግል የግጦሽ መሬት ልማት፣ ወ.ዘ.ተ.) 146.63 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 142.89 ሚ/ን (97.45 በመቶ) ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም መኖ ማልማት እና በቆላ ስንዴ ልማት በአብዛኛዎቹ ክልሎች ሰፊ ንቅናቄ በመፍጠራቸዉ ተጨማሪ ሰብል ተረፈ ምርት መኖ ማስገኘት በመቻሉ፣ እንዲሁም ለመኖ ዘር/ቁርጥራጭና ግንጣይ ግዢ በፌዴራልና በክልሎች ከፍተኛ በጀት በመመደብና ተገቢዉን ድጋፍ በማድረግ በተሻሻለ መኖ ልማት አፈፃፀሙን የተሻለ ቢያደርገዉም በአርብቶ አደር አካባቢ በዝናብ እጥረት የተከሰተዉ ድርቅ በግጦሽ መሬት /Rangeland/ ላይ የሚገኘዉን ምርት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የተለያዩ የተፈጥሮ ግጦሽ የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመተግበር እና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ 44.60 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 37.10 ሚ/ን ቶን (83.18 በመቶ) የተፈፀመ ሲሆን፣ ለዚህም የአፈፃፀም ዝቅተኛነት በአርብቶ አደር አካባቢ በአየር ንብረት ለዉጥ በተከሰተዉ የዝናብ እጥረት ምክንያት ድርቅ በመከሰቱ ነዉ፡፡ የተሻሻለ መኖን ለማልማት ፓኬጆችን በማዘጋጀትና ድጋፍ በማድረግ 11 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 10.60 ሚ/ን ቶን (96.36 በመቶ) ለማምረት ተችሏል፡፡ የሰብል ተረፈ ምርትን በተገቢዉ በማሰባሰብ ለመጠቀም እንዲቻል 64.5 ሚ/ን ቶን በአሰባሰብ በተገቢዉ በማከማቸት ጥቅም ላይ እንዲዉል ለማድረግ ታቅዶ 63.30 ሚ/ን ቶን (98.14 በመቶ) ተሰብስቧል፡፡ ለምርት አፈፃፀሙ የተሻለ መሆን በዋናነት የቆላ የመስኖ ስንዴ ልማት በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋ መደረጉ በስንዴ ተረፈ ምርት መኖ ያመጣዉ መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡ የኢንዱስትሪ (ስኳርና ሌሎች) ተረፈ ምርቶችን 7 ሚ/ን ቶን በማምረት ጥቅም ላይ እንዲዉል ለማድረግ ታቅዶ 7.40 ሚ/ን ቶን (100+ በመቶ) ተፈጽሟል፡፡ ለአፈፃፀሙ የተሻለ መሆን በዋናነት የተሻሻለ ዶሮ ልማት መስፋፋት

የፍላጎት መጨመር የተቀነባበረ መኖ አጠቃቀም መሻሻል ነዉ። የወል ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን የተለያዩ ማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመጠቀምና ድጋፍ በማድረግ 18.4 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 17.60 ሚ/ን ቶን (95.65 በመቶ) ተመርቷል።

ከግል የአርሶ አደር ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን በማሻሻል 1.14 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 4.28 ሚ/ን ቶን (100⁺ በመቶ) በማምረት ከእቅድ በላይ ተፈፅሟል። ለአፈፃፀሙ ከፍ ማለት በኦሮሚያ ክልል ላይ በግጦሽ መሬት ማልማት ላይ የተተገበረዉ አፈፃፀም ከዕቅድ አንፃር ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸዉ በመሆኑ ነዉ። የመኖ ዘር ምርታማነትን በማሳደግና ጥራት ያለዉ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮች 3 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 3.6 ሺህ ቶን (100⁺ በመቶ) መኖ ዘር ተመርቷል። በሁሉም ስነ ምህዳር በመስኖ የመኖ ማልማት ትግበራ ላይ የስልጠናና የመስክ ላይ ድጋፍ በማድረግ 21,466 ሄ/ር መሬት በመስኖ ለማልማት ታቅዶ 15,370 ሄ/ር (71.6 በመቶ) ተፈጽሟል። ለዚህም በዋናነት ከዚህ በፊት ሰፊ አፈፃፀም የነበራቸዉ የአማራና አፋር ክልል አፈፃፀም በወቅታዊ ሁኔታ ዝቅ በማለቱ ነዉ።

## 4.7 እንስሳትና ዓሳ ሀብት ዝርያ ማሻሻል

የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል በዓመቱ 1,400 ሺህ ዶዝ አባለዘር ለማምረት ታቅዶ 1,333 ሺህ ዶዝ (95.23 በመቶ) እንዲመረት ተደርጓል። ከተመረተው ምርት ውስጥ 1,060.36 ሺህ ዶዝ በዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩቱ ለመምረት ታቅዶ 1,060.36 ሺህ ዶዝ (100 በመቶ) የተመረተ ሲሆን፣ ቀሪው 339.65 ሺህ ዶዝ በሦስቱ የክልሎች በነቀምት፣ በባህርዳርና ሀዋሳ አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት ለማምረት ታቅዶ በድምሩ 273 ሺህ ዶዝ (80.34 በመቶ) የተመረተ ነው። የአባለዘር ምርት አፈጻጸም ከባለፈዉ ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ምርት ጋር ሲነጻጸር በ237,083 (21 በመቶ) ዶዝ ብልጫ/እድገት አሳይቷል። የአባለዘር ሥርጭትን በተመለከተ በዓመቱ በክልሎችና በዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት 1,314.24 ሺህ ዶዝ አባለዘር ለማሰራጨት ታቅዶ 786 ሺህ ዶዝ (59.81 በመቶ) ተከናውኗል። ምርትን በተመለከተ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነው የሆነው ቀደም ሲታቀድ በአራት አባለዘር ማምረቻ ላቦራቶሪዎች በነቀምቴ፣ በባህርዳር፣ በሐዋሳ እና በመቀሌ አባለዘር ማምረቻ ላቦራቶሪዎች እያንዳንደቸው 100,000 ዶዝ ያመርታሉ በሚል የዕቅድ ዕሳቤ ነበር። ነገርግን የሐዋሳ ላቦራቶሪ በፈሳሽ ናይትሮጂን መሳሪያ ብልሽት ምክንያት ያላመረተ በመሆኑ፣ የመቀሌ ላቦራቶሪ ዓመቱን በሙሉ በአካባቢው በተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት አገልግሎት ያልሰጠ በመሆኑ ነው። የአባለዘር ሥርጭትን በተመለከተ በ2014 ዓ.ም ለማሰራጨት የታቀደው በፀጥታ ችግር ምክንያት መሰረጫት ባለመቻሉ ከፍተኛ መጠን ያለው አባለዘር በኢንስቲትዩቱ እና በክልል ማከማቻ ማዕከላት ያለ በመሆኑ በቀጣይ ዓመት ለመሰረጫት በዕቅድ ታይዟል።

በአጠቃላይ የተመረተ ፈሳሽ ናይትሮጂንን በተመለከተ 385 ሺህ ሊትር ለማምረት ታቅዶ 337.85 (87.75 በመቶ) እንዲመረት ተደርጓል። ከተመረተው ምርት ውስጥ 65 ሺህ ሊትር በኢንስቲትዩቱ

ታቅዶ 57.32. (88.16 በመቶ) የተመረተ ሲሆን ቀሪው 298 ሺህ በክልሎች አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት ለማምረት ታቅዶ 280.55 (94.14 በመቶ) የተመረተ ነው፡፡ የፈሳሽ ናይትሮጂን ሥርጭትን በተመለከተ በዓመቱ በክልሎችና በዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት 346 ሺህ ሊትር ለማሰራጨት ታቅዶ 311.44 ሺህ ሊትር (90.01 በመቶ) ተሠራጭቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በኢንስቲትዩቱ 58 ሺህ ሊትር ለማሰረጫት ታቅዶ 47.77 (82.36 በመቶ) እና በክልሎች 288 ሺህ ሊትር ናይትሮጂን ለማሰረጫት ታቅዶ 263.67 (91.55 በመቶ) ተሰረጭቷል፡፡

### 4.8 የተሻሻለ የእንስሳት በሽታ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት

በበጀት ዓመቱ 140 ሚ/ን ዶዝ የእንስሳት ክትባት ለማሰራጨት ታቅዶ 129.31 ሚ/ን ዶዝ (92.36 በመቶ) ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለክትባት መበጥበጫ የሚሆን 16,900 ሊትር ጨዋማ ውሃ ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ ከተሰራጨት ክትባቶች መካከል ከፍተኛ ቁጥር የያዘው የዶሮ ፈንግል በሽታ (NCD) 46.22 ሚ/ን ዶዝ ቀዳሚ ሲሆን፣ በመቀጠል የጉርብርብ ክትባት (LSD) 26.34 ሚ/ን ዶዝ ክትባት የተሰራጨ፣ በዝቅተኛነት የግመል ፈንጣጣ (Camel Pox) 481.5 ሺህ ዶዝ ነው፡፡ እንዲሁም 20.49 ሚ/ን ዶዝ ደስታ መሰል የበጎችና ፍየሎች (PPR) ክትባት ለማሰራጨት ተችሏል፡፡

የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል 119,851 ካ.ኪ.ሜ መሬት ለመሸፈን ታቅዶ 96,780.94 ካ.ኪ.ሜ (80.75 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን ዋናው ምክንያት ኬሚካል ግዥ በውጪ ምንዛሪ እጦት ባለመፈጸሙ እና መስክ በሚወጣባቸው ሥራ አካባቢዎች ከፍተኛ የፀጥታ ችግር በመኖሩ ሥራዎችን በተያዘው ፕሮግራም መሠረት ወጥቶ ማከናወን ባለመቻሉ ነው፡፡

### 4.9 የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት

ለ145 የእንስሳት በሽታ ፍንዳታዎች ክስተት ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ በአጠቃላይ ለ136 (93.79 በመቶ) የበሽታ ፍንዳታ ክስተት መንስኤዎችን ለመለየት የተቻለ ሲሆን በዚሁ ስራ ወቅት ቁጥራቸው 1,724 የመሆኑ ናሙናዎችም በላቦራቶሪ ምርመራ ተደርጎላቸዋል፡፡ የበሽታ ፍንዳታ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል 1,040 ናሙና ለመመርመር ታቅዶ የቀረቡት 600 ናሙና ምርመራ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በበጎችና ፍየሎች ላይ ከፍተኛ ኦኮኖሚያዊ ችግር እያስከተለ ያለው የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ የአሰሳና ቅኝት ስራ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን 6,600 ናሙናዎችን የሴሮሎጂ ምርመራ ዘዴን በመጠቀም ለመመርመር ታቅዶ 8,215 ($100^{+}$ በመቶ) ተከናውኗል፡፡

## 5. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

### 5.1. የተፋሰስ ልማት

የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠባበቅ ተግባራትን አስመልክቶ አረንጓዴ ልማትን መሰረት ያደረገ ኢኮኖሚ በዘላቂነት በማስቀጠል የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን በመቋቋም ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲረጋገጥ

የማድረግ ሥራዎችን በትኩረት እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በዚሁም መሠረት በአረንጓዴ አሻራ ልማት ፕሮግራም “ኢትዮጵያን እናልብሳት” በሚል መሪ ቃል በ2013/14 በጀት ዓመት 6 ቢ/ን ችግኞች በአገር ውስጥና 1 ቢ/ን ችግኞች በጎረቤት አገራት ለመትከል ታቅዶ ከ6.7 ቢ/ን ችግኞች በላይ በሀገር ውስጥ የተተከለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100 በመቶ በላይ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ 3.02 ቢ/ን የደን ዛፍ፣ 3.3 ቢ/ን የጥምር ደን እርሻ፣ 371.9 ሚ/ን የፍራፍሬ እና 62.9 ሚ/ን ደግሞ የከተማ ውስጥ የተተከሉ ናቸው፡፡ በተካሄደው የችግኝ ተከላ 2.104 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ለመሸፈን የተከላ ቦታ ልየታ የተካሄደ ሲሆን ከተወሰኑ ክልሎች በደረሰን መረጃ መሠረት የ304,257 ሄ/ር የመጠነ-ዙሪያ ልኬት የጂፒኤስ (Polygon Sides GPS) መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ይህም በጎግል ኧርዝ (Google Earth) ካርታ ላይ በማሳረፍ የተለያዩ አካላት ክትትል ሊያደርጉ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በጎረቤት አገራት ለሚደረግ ተከላ ችግኞቹን ለማጓጓዝ የሚያስፈልገውን ወጪ የኢትዮጵያ መንግስት የተሸፈነ ሲሆን ተከላው የተካሄደበት ሀገራት ኤርትራ 181,000፣ ሶማሊ ላንድና ፑንትላንድ 40,000 እና ጂቡቲ 40,000 በአጠቃላይ 261,000 የተለያዩ ችግኞችን ለማድረስ ተችሏል፡፡

የድህረ-ተከላ ስራዎችን በተመለከተ በሃገር አቀፍ ደረጃ ከተተከሉት 6.7 ቢ/ን ችግኞች ውስጥ ለ4.82 ቢ/ን ችግኞች የድህረ ተከላ ስራዎች ማለትም የአረም፣ ኩትኳቶና ውሃ የማጠጣት ሥራዎች ተሰርቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ የተተከሉ ችግኞች አማካይ የጽድቀት መጠን 80.6 በመቶ መሆኑን በክልሎች በተካሄደ ምዘና መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የችግኝ ጣቢያ ዝግጅትን በተመለከተ በአገራችን ውስጥ የሚገኙ የችግኝ ጣቢያዎችን ብዛት፣ ችግኝ የማፍላት አቅማቸውን፣ መገኛ ቦታቸውን (Geo-reference) ፣ የሚሸፍኑት ስፋት እና የባለቤት ዓይነት የመለየት ሥራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በአጠቃላይ 121,985 ችግኝ ጣቢያዎች እንዳሉ ማወቅ የተቻለ ሲሆን በባለቤትነት ይዞታ 2,056 የመንግስት፣ 121 የመያድ፣ 75,524 የፕሮጀክት 31,937 የማኅበረሰብና የልማት ቡድኖች እንዲሁም 12,072 ችግኝ ጣቢያዎች ደግሞ የግለሰብና የተቋማት መሆኑን ለመለየት ተችሏል፡፡

የዛፍ ዘር አቅርቦትና ስርጭት ሥራዎችን በተመለከተ በዓመቱ 6,500 ኩ/ል ዘር ለማዘጋጀት ታቅዶ 7,374 ኩ/ል (113.44 በመቶ) በተለያዩ ክልሎች ማለትም ኦሮሚያ 5,951 ኩ/ል፣ አማራ 441 ኩ/ል፣ ደቡብ 822 ኩ/ል፣ ሲዳማ 155 ኩ/ል፣ እና ሶማሌ 5 ኩ/ል) ዘር ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ለችግኝ ዝግጅት የሚሆን የችግኝ ፕላስቲክ እስካሁን በተሰበሰበ መረጃ መሠረት 1,118,464 ኪ.ግ የችግኝ ፕላስቲክ የቀረበና በስራ ላይ የዋለ መሆኑን ለመለየት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለ2014/15 በጀት ዓመት ተከላ 6 ቢ/ን ችግኞችን ለማዘጋጀትና ለመትከል ግብ የተጣለ ሲሆን በበጀት በዓመቱ 47.6 ቢ/ን (127 በመቶ) ችግኞች ተዘጋጅቷል፡፡ ይኼውም ችግኞች በዓይነት ሲታይ 3.63 ቢ/ን የደን ዛፍ፣ 2.47 ቢ/ን የዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያለው ችግኝ፣ 538.56 ሚ/ን የፍራፍሬ፤ 954.34 ሚ/ን የመኖ ዛፍ እና 28.04 ሚ/ን የከተማ ውስጥ የሚተከሉ የውበት ዛፎች ናቸው፡፡

ሪፖርቱ እስከተዘጋጀበት ድረስ 2,200 ሺህ ሄ/ር የተከላ ቦታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,644.04 (74.73 በመቶ) ቦታ የተዘጋጀ ሲሆን፤ 51.5 ሺህ ሄ/ር ቦታ ዙሪያ ልኬት ለመውሰድ ታቅዶ 102.86 (100+ በመቶ) ተለክቷል። ተከላን በተመለከተ ከታቀደው 6 ቢ/ን ውስጥ 3.15 (52.51 በመቶ) የተተከለ ሲሆን፤ 20 ሚ/ን ህዝብ በንቅናቄ ለማሳተፍ ታቅዶ 16.67 (83.35 በመቶ) ተሳትፏል።

ሀገራዊ የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን አስመልክቶ "የአየር ንብረት ለውጥንና ህልውናችንን በተባበረ ክንድ" በሚል መሪ ቃል መሠረት በኅብረተሰብ ተሳትፎ የሚሠራ ሥነ-አካላዊና ሥነ-ሕይወታዊ አፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን አኳያ በበጀት ዓመቱ ለታቀደው የተፋሰስ ልማት ሥራ 9,538,604 አባወራ እና 6,938,947 እማወራ በድምሩ 16,477,551 የሰው ኃይል ልየታ ተካሂዶ በተፋሰስ ልማት ስራ ማሰማራት ተችሏል። በተመሳሳይ መልኩ ለ2,243 ባለሙያዎች በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎች ስልጠና በክልሎች አማካኝነት የተሰጠ ሲሆን የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት የቻለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም 156,663 አርሶ አደሮችን በተፋሰስ ልማት እና በቅየሳ ስራ ላይ ማሰልጠን ተችሏል። ከዚህ ጎን ለጎን 5,650,475 የልማት መሳሪያና 190,957 የቅየሳ መሳሪያ በስራው ላይ ለማሰማራት ልየታ ተደርጓል።

የተፋሰስ ልማት ትግበራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብዓቶች በማቅረብ እና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በመተገበር ተከልለው ከንክኪ ነጻ የሆነ ተዳፋት የወል መሬት 400 ሺህ ሄ/ር ታቅዶ 529.78 ሺህ ሄ/ር የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀም በመቶ ሲታይ 132.45 በመቶ መሆኑ፣ የማህበረሰብ ተፋሰስን በስነ-አካላዊ አፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች እንዲሸፈን ለማድረግ 2,500 ሺህ ሄ/ር ታቅዶ በ2,503.32 ሺህ ሄ/ር የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ከመቶ ሲታይ 100.13 በመቶ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

የተፋሰስ ልማትና ሴፍቲኔት መረጃዎችን ለማዘመን የማህበረሰብ ስራዎች የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተጠናቆ የማስፋት ስራ እየተሰራ ነው።

በልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም አምስተኛ ምዕራፍ ሲተገበር ከሚመደበው የማህበረሰብ ስራ ካፒታል በጀት 3 በመቶ ለስነ-ምግብ ተግባራት ተመድቦ በትኩረት እየተሰራ ነው። የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎች ቢግ ፑሽ ፕላስ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ለሚተገበሩ የውሃ ማሰባሰቢያ ስራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አጭር የቴክኒክ የትግበራ መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል።

የአየር ንብረት ትግበራ የመሬት አያያዝ ፕሮግራም ላይ የ1,899 ተፋሰሶች ዝርዝር መለኪያ መረጃዎች ተሰብስቦ ለአረጋገጩ አካል ቀርቦ 1,455 በመረጋገጫ ሥርዓቱ መሥፈርቶች ብቁ ሆነው የማረጋገጥ ሥራዎች ተከናውኗል። በዚህም መሠረት 840,757.20 ሄ/ር ተፋሰሶች በውጤት አመለካች ሁለት ማረጋገጫ በማግኘታቸው ለአገራችን 53,808,460.80 የአሜሪካን ዶላር ማስገኘት ተችሏል። በበጀት ዓመቱ በሁለተኛው ዙር ለውጤት አመለካች ሁለት ማረጋገጫ እንዲያገኙ 1,842 የማኅበረሰብ ተፋሰሶች ለኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የቀረቡ ሲሆን 1,528ቱ ሁሉንም መስፈርቶች ያሟሉ በመሆኑ

48.8 ሚ/ን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱ የማረጋገጥ ዙሮች 2,983 የማኅበረሰብ ተፋሰሶች የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ተቋቁመውላቸው ባለቤት ተበጅቶላቸዋል፡፡

## 5.2 የአፈር ለምነት

የአፈርን ምርታማነት በመጠበቅ ረገድ አዳዲስ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጤንነቱና ለምነቱ የተጠበቀ መሬት ሽፋን በማሳደግ ረገድ የኮትቻ አፈር በአይባር ቢ.ቢ.ኤምና በባህላዊ ዘዴ ለማንጣፈፍ የሚያገለግሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የአርሶ አደሮችን ግንዛቤ በማሳደግ 650,000 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ በዘመናዊ 381,281 ሄ/ር እንዲሁም በባህላዊ ዘዴ 256,138 ሄ/ር በድምሩ 637,419 ሄ/ር (98 በመቶ) መሬት ለምቷል፡፡ የተቀናጀ የኮትቻና የአሲዳማ አፈር ልማት የኤክስቴንሽን ፓኬጅ ለማዘጋጀት ታቅዶ 200 የኮትቻና 480 የአሲዳማ አፈር ፓኬጅን አስመልክቶ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በተገኘው በጀት ድጋፍ ታትሞ ለማሰራጨት ዝግጁ ሆኗል፡፡ የግል የግብርና ኖራ አምራቾችን በማሳተፍ ኖራን እንደማንኛውም ግብዓት በብድርና በቀጥታ ግዢ በማቅረብ ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል ተብሎ እየተዘረጋ ባለው የኖራ አቅርቦት ሰንሰለትን ለማጠናከር የሚቻልበትን ሁኔታ ለመወሰን ከባለድርሻ አካላት፣ ከክልል አመራሮችና ከሚመለከታቸው ከፍተኛ ባለሙያዎች ጋር አራት ዙር የምክክር መድረክ ለማካሄድ ተችሏል፡፡ ይኸውም በአመራርና በባለድርሻ አካላት ዘንድ የአሲዳማ አፈርን ከማልማት አንፃር ያለውን ግንዛቤ ፈጥሯል፡፡

በአሲዳማ አፈር የተጠቃው መሬት ለማከም የሚያገለግለውን የግብርና ኖራን ለማምረት የተቋቋሙ የኖራ ወፍጮዎችን በኦሮሚያ ክልል (ጉደር)፣ አማራ ክልል (ደጀንና መራዣቤተ) እና ደቡብ ክልል (ኬላ) በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የመስክ ዳሰሳ ጥናት ተሰርቷል፡፡ ከሪፖርቱ በመነሳት የበጀት ድጋፍ ለማፈላለግ የሚረዳ አንድ የባለሙያ ቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቋሞ ፕሮፖዛል እንዲዘጋጅ ተድርጓል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን ጨዋማነትን የሚቋቋሙ የመኖና የሰብል ዝርያዎችን ዘር 800 ኪ/ግ ለማሰራጨት ታቅዶ 1,015 ኪ.ግ (100+ በመቶ) በአፋር፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ክልሎች ተሰራጭቷል፡፡ በአፋርና በኦሮሚያ ክልሎች ጨዋማነትን የሚቋቋሙ የመኖና የሰብል ዝርዎችን በማስተዋወቅ ጨዋማ መሬትን ማልማት ያስገኘውን ፋይዳ አኳያ የመ/ቤታችን ሕዝብ ግንኙነትና ዋልታ ቴሌቪዥን የሚዲያ ሽፋን ተሰጥቷል፡፡ በአፈር ጤንነት ዙሪያ ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የአፈር ለምነትና ጤንነት የትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ እንዲካተት ተድርጓል፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በጥራጥሬ ሰብሎች 150,000 ሄ/ር መሬት በህየወ ማዳበሪያ ለማልማት ታቅዶ 135,000 ሄ/ር (90 በመቶ) መሬት ለማልማት የተቻለ ሲሆን ለዚህም 152,158 ሳቼት ህያው ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የአፈር ጤንነትና ለምነትን በማሻሻል የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በበጀት አመቱ 4.5 ሚ/ን

ሄ/ር በኮምፖስት ለማልማት ታቅዶ 6.77 ሚ/ን ሄ/ር (100+ በመቶ) መሬት ለምቷል፡፡ ይኸውም አፈፃፀም የተመዘገበው በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ነው፡፡ ከባዮ-ጋዝ ማብላያ ፕላንት በተረፈ ምርትነት የሚወገደውን የባዮስላሪ ኮምፖስት ለተፈጥሮ ማዳበሪያነት በመጠቀም 170,800 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 31,480 ሄ/ር ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ በፊት የተዘጋጀውን የባዮ ስላሪ ኮምፖስት የስልጠና ማንዋል ለማሻሻል ከኤስ ኤን ቪ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት ታቅዶ በተያዘለት ድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ማከናወን ተችሏል፡፡

የቨርሚ ኮምፖስት ቴክኖሎጂን በመጠቀም 8,000 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ ሲዳማ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 6,450 ሄ/ር (80.63 በመቶ) መሬት ለምቷል፡፡ በ12,500 ሄ/ር መሬት ላይ በዕቀባ እርሻ (Conservation Agriculture) ለማልማት ታቅዶ በደቡብና በሲዳማ ክልሎች 11,750 ሄ/ር (94 በመቶ) ለማከናወን ተችሏል፡፡

በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ሀረሪ ክልሎች እና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳደርን የማዕድን ማደበሪያ፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሰርቶ ማሳያ (የማዕድን እና የተፈጥሮ ማዳበሪያ በተቀናጀ መልኩ) በ1,000 አርሶ አደር ማሳ ላይ ለመስራት ታቅዶ በ908 ሰርቶ ማሳያ (90.8 በመቶ) ተከናውኗል፡፡

## 5.3. አፈር መረጃና ካርታ

የአፈር ሀብት ዓይነትና ባህርይ በመስክ በመለየት ካርታ ከማዘጋጀት አንፃር በተለያየ ጊዜያት በፌደራልና ክልል ባሉ ተቋማት ከተሰበሰቡ 20,000 ፕሮፋይል ውስጥ 17,133 የአፈር መረጃዎችን በመጠቀም የአፈር ዓይነት ካርታ በ250 ሜትር ሪዞሊሽን ተዘጋጅቶ ከዩኒቨርስቲዎችና ከምርምር ተቋማት ከፍተኛ የአፈር ሳይንስ ባለሙያዎች የማረጋገጫ ፍተሻ ባደረጉት መሰረት አነስተኛ የአፈር ናሙና መረጃ ያላቸውን ሳይጨምር በአገር አቀፍ ደረጃ 18 የአፈር ዓይነት ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም ለረጅም ዓመታት ጥቅም ላይ ይውል የነበረውን 1፡2 ሚ/ን ስኬል የአፈር ዓይነት ካርታ በመከለስ ማሻሻል ተችሏል፡፡ የጂኦስፓሽያል ቴክኖሎጂን በመጠቀም በተመረጡ በ13 ወረዳዎች የአፈር ጨዋማነት ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ (ከኦሮሚያ ክልል 4 እና ከሶማሌ ክልል 7 ወረዳዎች) ከመስክ የአፈር ናሙና የመሰብሰብ እንዲሁም ለአፈር ጨዋማነት ካርታ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ከሳተላይት ምስልና ከተለያዩ ምንጮች የማሰባሰብና የማጠናቀር ሥራ የተሰራ ሲሆን ለ9 ወረዳዎች (81.82 በመቶ) የአፈር ጨዋማነት ካርታው ተዘጋጅቷል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ወረዳ (ስኳር ድንች) እና አማራ ክልል ደብረ-ኤልያስ ወረዳ (ስንዴ) የኢኖቨሽን (የሰብል ተስማሚነት) ምክረ-ሀሳብ ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ለተመረጡ ወረዳዎች (በሶማሌ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል) የጂኦ-ኒውትሪሽን ካርታ ለማዘጋጀት ለ3 ወረዳዎች የታቀደ ሲሆን የዳሰሳ ጥናት በሁሉም ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ

ተጠናቆ ለካርታ ዝግጅት ለ1 ወረዳ ከመስክ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የአፈር እና ተያያዥ መረጃዎችን በየፈርጁ በማደራጀት ለተጠቀሚው በሚፈለገው አግባብ ተደራሽ ለማድረግ ማዕከላዊ ጂኦ-ስፓሻል የአፈር መረጃ ቋትና ጂኦፖርታል በዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት የማበልጸግ ስራ ተጠናቆ የማብሰሪያ (launching) ተድርጓል፡፡

## 5.4. በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

በበጀት ዓመቱ 2.6 ሚ/ን ማሳ ልኬትና ምዝገባ ለማካሄድ ታቅዶ ለ2.3 ሚ/ን (88.46 በመቶ) ማሳዎች ላይ ተከናዉኗል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፊኬት አሰጣጥን በተመለከተ ለ2.6 ሚ/ን ማሳዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ1.8 ሚ/ን (112.5 በመቶ) ማሳዎች ሠርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡ ለባለይዞታዎች የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋጫ ሰርተፍኬት አሰጠጥን በተመለከተ ለ0.743 ሚ/ን ባለይዞታዎች (0.52 ሚ/ን አባወራ እና 0.223 ሚ/ን እማወራ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ0.66 ሚ/ን (88.83 በመቶ) ባለይዞታዎች (0.46 ሚ/ን አባወራ እና 0.2 ሚ/ን እማወራ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡

የብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት ዝርጋታን በተመለከተ ለ105 ወረዳዎች ለመዘርጋት ታቅዶ በ93 ወረዳዎች (88.57 በመቶ) የመረጃ ማጥራትና ወደ መረጃ ሥርዓቱ የማሸጋገር ስራዎች የተከናወነ ሲሆን በ25 ወረዳዎች መረጃ የማሸጋገር ስራ ተጀምሯል፡፡ በሌላ የሁለተኛ ደረጃ ሰርተፊኬትን በመጠቀም በወረዳ ደረጃ የተመዘገቡና የተከናወኑ የመሬት ግብይት (Land Related Transactions) ብዛት 87 ሲሆን ያለፈው ዓመት 114 ወረዳዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ በ201 ወረዳዎች ውስጥ 187,729 የመሬት ግብይቶች ተከናውኗል፡፡

አሳታፊ ገጠር መሬት ዕቅድ አዘገጃጀትን አስመልክቶ በቀበሌ ደረጃ 1,000 የአሳታፊ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 247 (24.7 በመቶ) ሰነዶች ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም ለ700 የቀበሌ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ትግበራ ለማስጀመር ታቅዶ 280 (40 በመቶ) ቀበሌዎች ለማስጀመር ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ 225 የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን ለመመስረት ታቅዶ በ122 (54.22 በመቶ) ቀበሌዎች ሙሉ በሙሉ ማዕከላት እንዲመሰረቱ ተደርጓል፡፡

ለአሳታፊ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅት መረጃ የሞባይል መተግበሪያ LandPKS app ማንዋል ለሁሉም ክልል እንዲዳረስ የተደረገ ሲሆን በሦስት ክልሎች (በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ) በስድስት ቀበሌዎች የሙከራ ትግበራ ተከናውኗል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ያላቸው የመጠቀም መብታቸውን ለብድር ዋስትና በማስያዝ ከአነስተኛ የብድር ተቋማት ብድር የመውሰድ ልምዱ በየክልሉ እየጨመረ ሲሆን ለአብነት በኦሮሚያ ክልል ባለፈው ዓመት የመጠቀም መብታቸውን በማስያዝ 30 በመቶ ገንዘብ በመቆጠብ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 231 ትራክተሮችን እና 48 ኮምባይነሮችን የመሬት ይዞታ ሠርተፍኬታቸውን

በማስያዝ በብድር የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣ ይኸውም የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

የቀበሌ የልማት ጣቢያ እና የወረዳ ሠራተኞችን በመሬት አስተዳደርና የመሬት ግብይት ዙሪያ በጽንሰ ሀሳብና በተግባር ላይ ያተኮረ ዕውቀት ከማስጨበጥ አንፃር ከሦስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና ከአሶሳ ATVET ጋር በተደረገ ስምምነት በሳባት ዙር ለ2,800 ባለሙያዎች የአንድ ወር አጫጭር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ2,789 ባለሙያዎች (ሴት 642) ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ለ1,584 ባለሙያዎች (251 ሴት) የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የክልል ባለሙያዎችን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በተለያዩ ርዕሶች ለ411 (ሴት 50) ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለመስጠት የተቻለ ሲሆን በአጠቃላይ በፌዴራልና በክልል ደረጃ በድምሩ 3,190 (ሴት 503) ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

## 5.5. አነስተኛ መስኖ ልማት

የአነስተኛ ባለይዞታዎች የግብርና ውሀ አቅርቦትን ለማሳደግ በ2013 የተደረሰበትን 846.77 ሺ.ህ ሄ/ር መነሻ በማድረግ በ2014 ተጨማሪ 27.10 ሺ.ህ ሄ/ር በማሳካት 873.87 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት አዲስ ለመስኖ ልማት ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ 40.04 ሺ.ህ ሄ/ር (100+ በመቶ) መሬት ለመስኖ ተዘጋጅቷል፡፡ በሌላ በኩል አዲስ የመስኖ ውሀ ተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደሮች 298,.3 ሺ.ህ ተሳታፊ ለማድረግ ታቅዶ 119.6 ሺ.ህ (40.09 በመቶ) ተጠቃሚ የተደረገ ሲሆን፣ በመረጃ ክፍተት ምክንያት 10 ዓመቱ ዕቅድ ላይ የተጋነነ የተጠቃሚዎች ቁጥር በዕቅድ መያዙ የዕቅድ አፈፃፀሙን ዝቅተኛ አድርጎታል፡፡ በማህበረሰብ ደረጃ የሚተዳደሩ 197 የመስኖ አውታሮችን ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 218 (100+ በመቶ) የተከናወነ ሲሆን፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ከማድረግ አንፃር ለ197 ማህበራት ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ለ167 ህጋዊ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

# 6. ደን ልማት

በበጀት ዓመቱ 0.02 ሚ/ን ሄ/ር የቀርከሃ ተከላ መሬት ለመለየት ታቅዶ በአማራ 326 ሄ/ር፤ በኦሮሚያ 34,800፤ በደቡብ 19,358.73፤ በሲዳማ 2,880፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 624፤ በቤንሻንጉል ጉምዝ 1,792፤ በጋምቤላ 1,200፤ በጠቅላላው ለቀርከሃ የተለየ መሬት 0.06 ሚ/ን (100+ በመቶ) ሄ/ር ነው፡፡ የደን እና የቀርከሃ በአጠቃላይ 716,411.5 ሄ/ር መሬት መለየት ተችሏል፡፡ እስካሁን በተካሄደው ችግኝ ተከላ በአማራ ክልል 53.30 ሚ/ን፤ ኦሮሚያ 443.78 ሚ/ን (3.67 ሚ/ን ቀርከሃ) ፤ ደቡብ ክልል 2.17 ሚ/ን (0.01 ሚ/ን ቀርከሃ) ፤ ሲዳማ 59.00 ሚ/ን (9 ሚ/ን ቀርከሃ) ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች

23.53 ሚ/ን (2.53 ሚ/ን ቀርከሃ) በአጠቃላይ 596.99 ሚ/ን ችግኝ የተተከለ ሲሆን 15.22 ሚ/ን የተተከለው የቀርከሃ ችግኝ ነው፡፡

የሀብት ግኝትን ከማሳደግ አንፃር ደንን በመንከባከብ ከውጤቱ ለመጠቀም በተደረገው ጥረት (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ክልሎች እና አዲስ አበባ መስተዳደር) ከደን ሮያሊት እና ከተወረሰ ደን ሀብት እና የሀገሪቱ የደን ህግን ከተላለፉ አካላት ቅጣት በድምሩ 200 ሚ/ን ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 293 ሚ/ን (100+ በመቶ) ብር ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የወጪ ገቢን ከማሳደግ አንፃር 18,379 ቶን የደን ምርት ውጤቶች (አጣና 1,2587.1 ቶን፤ ፈርኒቸር 5,7912.8 ቶን፤ ቀርከሀ 17.1 ቶን) የደን ውጤቶች ወደ ውጭ በመላክ 20 ሚ/ን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 2.38 ሚ/ን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል፡፡ የውጭ ምንዛሬ ግኝት አፈፃፀም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በሱዳን በኩል የሚላከው አጣና በጸጥታ ምክንያት በመቋረጡ እና በወቅታዊ ሁኔታ ምክንያት ከሰሜኑ የሃገራችን አካባቢዎች እጣንና ሙጫ ወደ ውጭ መላክ ባለመቻሉ ነው፡፡ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ግብርና ልማት ውጤታማነት ከማሻሻል አንፃር የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን 5 ሚ/ን ሜትሪክ ቶን $Co_2e$ ለመቀነስ ታቅዶ 10 (100+ በመቶ) መቀነስ ተችሏል፡፡

ሀገራዊ የደንና የጥበቃ ቦታዎች ሽፋንን ለማሳደግ በተደረገ ጥረት 18.5 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ 17 (92 በመቶ) በመቶ ለማሳደግ ተችሏል፡፡ የተፈጥሮ እና የሰው ሰራሽ ነባር ደን አጠባበቅን ለማሻሻል በተሰሩ ስራዎች 19.2 ሚ/ን ሄ/ር ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም የቀርከሀ ደን ልማት ለማሻሻል 0.02 ሚ/ን ሄ/ር ለመትከል ታቅዶ 0.06 (100+ በመቶ) ተከናውኗል፡፡

ሀገራዊ የደን ማኔጅመንት ፕላን 0.2 ሚ/ን ሄ/ር ለማዘጋጀት ታቅዶ 0.97 (100+ በመቶ) ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም የደን ሀብት ቆጠራ 50 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 በመቶ (30 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ ለዚህም አፈፃፀም ማነስ ምክንያት ባለሙያዎች በጸጥታ ምክንያት በደን ዉስጥ ለመንቀሳቀስ መቸገራቸው ነው፡፡ በከተሞች የደን አያያዝ እና ማኔጅመንት በተመረጡ 5 ከተሞች (ጅማ፣ ሀዋሳ፣ አርባ ምንጭ፣ አዲስ አበባ እና ባህርዳር) ለማሻሻል ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ተከናውኗል፡፡

## 7. ብዝሀ ሕይወት

ተፈጥሮ ሀብት ብዝሀ ህይወት ጥበቃን በሚመለከት የብዝሀ ህይወትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀት በጥናት መለየትና ዝርያዎች እንዲታወቁ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ 31 ጥናቶች ለማካሄድ ታቅዶ 43 (100+ በመቶ) ተከናውኗል፡፡ የብዝሀ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በዘቦታ 78 ዝሪያዎች ለማንበር ታቅዶ 76 (100+ በመቶ) የተከናወነ ሲሆን፣ 82 ናሙናዎችን ለማንበር ታቅዶ 86 (100+ በመቶ) ተከናዉኗል፡፡

የብዝሀ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በኢዘቦታ 239 ዝርያዎችና 1,070 ናሙናዎች በቅደም ተከተል ለማንበር ታቅዶ 250 እና 1,178 (100+ በመቶ) ተከነዉኗል፡፡ ብዝሀ ሕይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በኢዘቦታ 2 ዝሪያዎችና 5,000 አባለዘር ቀሰም ለማንበር ታቅዶ ኮርማዎቹ ዘር ለመስጠት በለመድረሳቸዉ ምክንያት አልተከናወነም፡፡

የብዝሀ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በዘላቂታዊነት አጠቃቀሙን ለማሳደግ 50 ዝርያዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 74 (100+ በመቶ) ፣ እንዲሁም 10,200 ናሙናዎችን ለመውሰድ ታቅዶ 23,019 (100+ በመቶ) ተከናውኗል፡፡

## 8. የግብርና ኢንቨስትመንት ግብዓት አቅርቦትና ምርት ግብይት

### 8.1 የእርሻ ኢንቨስትመንት አፈፃፀም

2013/14 ምርት ዘመን በባለሀብቶች እርሻ 2,287 ሺህ ሄ/ር መሬት ለምቶ, 27,600 ሺህ ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዷል፡፡ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ከ7 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ህ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ሶማሌ) የተሰበሰበው መረጃ የሚያሳየው በተለያዩ ሰብሎች 884.80 ሺህ ሄ/ር (38.69 በመቶ) መሬት ለምቷል፡፡ ከለማው መሬት 19,398 ሺህ ኩ/ል (70.28 በመቶ) ምርት ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ባለሀብቶች እርሻ በበጋ መስኖ ስንዴ እስካሁን በደረሰን መረጃ 3,959.83 ሄ/ር (አማራ ክልል 610.83 ሄ/ር፣ ኦሮሚያ 2,862 ሄ/ር፣ ደቡብ 487 ሄ/ር) መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡

በ19 ባለሀብቶች በበልግና በመኸር ከለማው 25,533 ሄ/ር መሬት የተመረተው ምርት 343,668 ኩ/ል (ሰሊጥ 44,257 ኩ/ል፣ ማሾ 86,279 ኩ/ል፣ አኩሪ አተር 16,000 ኩ/ል፣ ቦለቄ 193,082 ኩ/ል እና ጤፍ 4,050 ኩ/ል) ከየክልል ግብርና ቢሮዎች ጋር ከተረከቡትና ከተዋዋሉት መሬት ስለመመረቱ በተሰጠው ማረጋገጫ መሰረት የኤክስፖርት ገበያ እንዲመቻችላቸው ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለ362 ሀገር ውስጥ ለአልሚ ባለሀብቶች ጋምቤላ 73,191.8 ሄ/ር፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ 54,823 ሄ/ር፣ ደቡብ 500 ሄ/ር፣ አማራ 2,027.3 ሄ/ር በድምሩ 130,541.4 (94.52 በመቶ) ሄ/ር መሬት ወደ ልማት እንዲገባ ተላልፏል፡፡

ለእርሻ ኢንቨስትመንት መዋል የሚችል መሬት በመለየት ወደ ልማት ለመግባት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች በደ/ብ/ብ/ህ 32,238፣ በኦሮሚያ 65,853፣ በሶማሌ 650,000፣ አፋር 399,204 ሄ/ር፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል 98,757 በአጠቃላይ 1,246,052 ሄ/ር መሬት ዝግጁ ሆኗል፡፡

**በአጠቃላይ ለአፈጻጸሙ ማነስም** በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች በተከሰተው ጦርነት ይለማል ተብሎ የተያዘው 159.114 ሺህ ሄ/ር መሬት ልማት እቅድ በክልሉ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ወደ ልማት የገባው አለመታወቅ፣ በተመሳሳይ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ (መተከልና ካማሻ ዞኖች) እና

አፋር ክልሎች በተከሰተው የፀጥታ ችግር ለባለሀብት የተላለፈው መሬት ሙሉ በሙሉ ወደ ልማት መግባት አለመቻልና የብድር አቅርቦት ውስንነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ዋና ዋናዎች ናቸው።

## 8.2 የእንስሳት ኢንቨስትመንት አፈፃፀም

በተሰጠ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰረት እየለሙ ያሉ 1,622 የእንስሳት እርባታ ማዕከላት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ማድረግና ለማጠናከር ታቅዶ ከክልሎች በተገኘው መረጃ መሰረት በወተት ከብት እርባታ 488፣ ዳልጋ ከብት ማድለብ 418፣ በግና ፍየል እርባታና ማድለብ 84፣ ዶሮ እርባታ 118፣ ንብ እርባታ 17፣ ዓሳ እርባታ 3፣ እንዲሁም መኖ ልማት 20 በአጠቃላይ 1,148 (70.78 በመቶ) ላይ ለሚሰሩ ባለሀብቶች የሙያ፣ የስልጠና፣ የምክር እና በሚመለከተው ተቋም በኩል የማስፋፊያ ቦታ እንዲሰጣቸው አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል። የግል ባለሀብቱን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የእንስሳትና እንስሳት ምርት ለሚያቀናብሩ ኢንዱስትሪዎችና ተጠቃሚዎች ደረጃውን የጠበቀ ምርት በባለሃብቱ በኩል እንዲቀርብ ክትትል ለማድረግ የታቀደ ሲሆን በተሰባሰበው መረጃ መሰረት የእርድ ፍየል ዕቅድ 66,732 ክንውን 28,454፣ የዕርድ በግ ዕቅድ 25,206 ክንውን 11,835፣ የዳልጋ ከብት ዕቅድ 24,143 ክንውን 29,017፣ ጥሬ ወተት ዕቅድ በሚ/ን ሊትር 4.7 ክንውን 16.7፣ የስጋ ዶሮ ዕቅድ 129,682 ክንውን 215,906፣ የዶሮ ዕንቁላል ዕቅድ 6.72 ሚ/ን ክንውን 28.85 ሚ/ን፣ የማር ምርት ዕቅድ በቶን 88 ክንውን 67.7 እንዲሁም መኖ ምርት ዕቅድ አጻጸም 48 ሺህ ኩ/ል ነው። ለዕቅድ አፈጻጸሙ ማነስ የወተት ምርት ዝቅተኛ መሆን፣ የመኖ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ መጨመር እርባታው በሚፈልገው መንገድ መኖ መቅረብ አለመቻል፣ የተቀነባበረ መኖ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የመኖ ግብዓት ዋጋ መጨመር፣ ለዶሮ መኖ የሚውል የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርት ዋጋ መጨመር፣ ከፍተኛ የማር ምርትና ዓሳ ምርት አምራች አካባቢዎች የተሟላ መረጃ አለመኖር በመሰረታዊነት ይጠቀሳሉ።

የእንስሳት ኢንቨስትመንት ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሀብቶች ብር 1.43 ቢ/ን ገቢ ለማግኘት የታቀደ ሲሆን በተሰራው የምርት ሺያጭ ትመና መሰረት ብር 2.05 ቢ/ን (100+ በመቶ) ገቢ ተገኝቷል። አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው በአሁኑ ወቅት የእንስሳት ምርት ዋጋ እየጨመረ በመምጣቱ ነው።

በእንስሳት ኢንቨስትመንት የተሰማሩ እና በአዲስ የሚሰማሩ ባለሃብቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ክትትል ለማድረግ በታቀደው መሰረት በኢንቨስትመንቱ ውስጥ 15,415 ወንድ እና 13,505 ሴቶች በድምር 28,920 ዜጎች በቋሚነት እና 4,374 ወንድ ና 1,507 ሴቶች በድምሩ 5,881 በጊዜያዊነት የስራ ዕድል ተጠቃሚ በመሆን እየሰሩ ይገኛሉ።

## 8.3 የሰብል ግብዓት አቅርቦት

### የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት

የ2014 የተለያየ የአፈር ማዳበሪያ ግዢ 18.5 ሚ/ን ኩ/ል ለማቅረብ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የማዳበሪያ ዋጋ በ3 እጥፍ በማደጉ እንደ ሀገር መግዛት የምንችለው አምና ያቀረብነውን 70 በመቶ ብቻ ወይም 12.9 ሚ/ን ኩ/ል እንዲሆን በተወሰነው መሰረት በኢ.ግ.ሥ.ኮ በኩል ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በማውጣትና የግዢ ትዕዛዝ በመስጠት በአንደኛው ዙር 12.9 ሚ/ን ኩ/ል ግዥ ተፈጽሟል፡፡ የተገዛው ማዳበሪያ ከመነሻ ዕቅድ ጋር ሲታይ 70 በመቶ ሲሆን በሀገር ደረጃ ከተወሰነው የግዥ መጠን ጋር ሲነፃፀር ከ100 በመቶ በላይ ግዥ መፈፀም ተችሏል፡፡ ካለፉት ዓመታት አጠቃቀማችንና በየዓመቱ ከሚተርፈው ማዳበሪያ አንፃር በዚህ ዓመት ተገዝቶ የሚቀርበውና በመጋዘን ያደረውን 2.3 ሚ/ን ኩ/ል ጨምሮ 15.2 ሚ/ን ኩ/ል የቀረበ ሲሆን፣ ይህም አምና ጥቅም ላይ ከዋለው የአፈር ማዳበሪያ አንፃር የ600 ሺ.ህ ኩ/ል ብልጫ አለው፡፡ ሪፖርቱ እስከተዘጋጀበት ድረስ በአጠቃላይ 12.9 ሚ/ን ኩ/ል ማዳበሪያ ወደ ክልሎች ለማቅረብ ታቅዶ 11.77 ሚ/ን ኩ/ል (91.24 በመቶ) የቀረበ ሲሆን፣ 758,379.30 ሜ/ቶን ለመሰረጫት ታቅዶ 848,028.55 ሜ/ቶን (100⁺ በመቶ) ለተጠቃሚው ተሰራጭቷል፡፡

### የኬሚካል አቅርቦትና ስርጭት

በበጀት ዓመቱ ከስቶክ (Stock) ያለ 2.20 ሚ/ን/ኪ.ግ/ሊትር ኬሚካል ለአርሶ/አርብቶ አደሩ የቀረበ ሲሆን፣ ከክልሎች የተሰበሰበው የፀረ-ተባይ ኬሚካል ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ በምንዛሪ እጥረት ምክንያት በፍለጎቱ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተገዝቶ ባይቀርብም አስፈላጊነቱ ታምኖበት ለመንግስት ጥያቄው ቀርቦ 60 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ተፈቅዶ በግዥ ሂደት ላይ ነው፡፡

### የዕፅዋት ምርጥ ዘር አቅርቦትና ስርጭት

የሰብል ምርጥ ዘር በተመለከተ የ2014/15 ምርት ዘመን የክልሎች ፍላጎት 1,761.84 ሺ.ህ ኩ/ል የተሰበሰበ ሲሆን፣ ከተዘራው የዘር ብዜት ውስጥ 2,079.90 ሺ.ህ ኩ/ል ምርት እንደሚገኝ በመገመት፣ ከዚህ ውስጥ 70 በመቶው 1,455.93 ሺ.ህ ኩ/ል ጥሬ ዘር ለመሰብሰብ ታቅዶ 1,025.50 ሺ.ህ ኩ/ል (70.44 በመቶ) ተሰብስቧል፡፡ ከዚህ ውስጥ 1,310.33 ሺ.ህ ኩ/ል የተበጠረ ዘር ለማቅረብ እና 1,179.30 ሺ.ህ ኩ/ል ለማሰራጨት ታቅዶ ተበጥሮ ለዘር እንዲሆን የተዘጋጀ የዘር ዕቅድ 786.20 ሺ.ህ ኩ/ል አፈፃፀሙም 489.84 ሺ.ህ ኩ/ል (62.3 በመቶ) ነው፡፡ ሪፖርቱ እስከተዘጋጀበት ድረስ 1310.33 ሺ.ህ ኩ/ል ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ 922.14 ሺ.ህ ኩ/ል (70.37 በመቶ) ሊቀርብ ተችሏል፡፡ 979.93 ሺ.ህ ኩ/ል ለማሰራጨት ታቅዶ 664.84 ሺ.ህ ኩ/ል (67.85 በመቶ) ማሰራጨት ተችሏል፡፡ ለአፈጻጸሙ ማነስም ዕቅዱ ከጥር 1 እስከ ታህሳስ 30/2015 ዓ.ም ድረስ ታሳቢ የተደረገ በመሆኑ፣ በቀጣይ የሚቀርቡ ሰብሎች ያሉ በመሆኑ አፈጻጸሙ የሚጨምር ይሆናል::

## 8.4 የግብርና ሜካናይዜሽን

በ2013/14 ምርት ዘመን 2,550 ሺህ ሄ/ር በዘመናዊ የእርሻ ትራክተር ለማረስ ታቅዶ 2,040 ሺህ ሄ/ር (80 በመቶ) በዘመናዊ የእርሻ ትራክተር ታርሶ በዘር የተሸፈነ ሲሆን፣ አጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ከታረሰው 13,137 ሺህ ሄ/ር አንጻር ሲታይ 16 በመቶ በእርሻ ትራክተር ታርሷል። ምርት ማሰባሰብን በተመለከተ በሜካናይዜሽን ለመደገፍ በተደረገው ስራ 1,197 ኮምባይነሮች (በአማራ 112፣ ኦሮሚያ 848፣ በደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል 190 እና ሶማሌ 47 ኮምባይነሮች ጥቅም ላይ በማዋል ከ4,120 ሺህ ሄ/ር ማሳ ላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ 651.06 ሺህ ሄ/ር (15.8 በመቶ) በኮምባይነር ሲሰበሰብ፣ 921 መውቂያዎችና መፈልፈያዎች በመሰብሰብ ሂደቱ ስራ ላይ ውሏል። በሁለገብ መውቂያ የተወቃ ምርት 866.84 ሺህ ኩ/ል መሰብሰብ ተችሏል። በአጠቃላይ ከዚህ ስራ 1,764.21 ሺህ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆን ችሏል። በበጋ መስኖ የለማ የስንዴ ማሳ ሰብል ስብሰባ ስራን ጨምሮ 865.52 ሺህ ሄ/ር መሬት ላይ የተሰበሰበ ሲሆን፣ ከተወቃው ሰብል ውስጥ 26,749.28 ሺህ ኩ/ል ምርት መሰብሰብ ተችሏል።

በሀገር ደረጃ በመካሄድ ላለው መስኖ ስንዴ ልማት ስራዎች ላይ ባለሙያዎችን በመመደብ የማሽነሪ አጠቃቀም እና አግልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ላይ ቴክኒካል ድጋፍ ተደርጓል። የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች አገልግሎት የማስፋት ስራ ላይ ለሚቋቋሙ ሁለት ማዕከላት በጊምቢቹ እና በቸሃ ወረዳዎች ማሽነሪ የማሟላት እና ስራ ለማስጀመር የኦፕሬተሮች ስልጠናን ጨምሮ የተለያዩ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ተችሏል። ለ113 የተለያዩ የጸረ ሰብል ኬሚካል መርጫ አስመጪዎች የቴክኒክ ምርመራ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ ለ112 አስመጪዎች (99.11 በመቶ) ድጋፍ መስጠት ተችሏል። በዚህም ድጋፍ 627,868 የተለያዩ የሰብል ጸረ-ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ዉስጥ ገብቷል።

የሜካናይዜሽን ማዕከላት በመቋቋም ከግብርናው ዘርፍ የሚጠበቀውን ለሀገር ግንባታ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት የማሻሻል እና የማሳደግ አላማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የአሰራር ስርዓት እና ተቋማዊ ሪፎርም በማካሄድ ላይ ይገኛል። ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች፣ ቴክኖሎጂዎች እና እቃዎች የቀረጥ እና ታክስ ነጻ ማረጋገጫ ለ493 አስመጪዎች በመስጠት በድምሩ 1,147,844 የተለያዩ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ማለትም 168,697 ፓምፖች፣ 217,435 የውሀ ፓምፕ ቱቦዎች፣ 637 ትራክተሮችና 1,043 ተቀጽላዎች 270 አጭዶ መውቂያዎችና 1,062 ባለሞተር አነስተኛ ሁለገብ መውቂያዎችና መፈልፈያዎች፣ 11,000 የዶሮ ማስፈልፈያና ልማት ዕቃዎች እና 689,000 ናፕሳክ መርጫዎች ከነመለዋወጫዎቻቸው 12,628 የተለያዩ የመስኖ ቴክኖሎጂ ክፍሎችና መለዋወጫዎች 46,709 ሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂዎች ከውጪ ሀገር በማስገባት ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ማድረግ ተችሏል።

በተለያዩ የቅድመ ምርት እና ድህረ ምርት ማሽነሪዎች ላይ በአፋር፣ ደቡብ ክልል፣ ኦሮሚያ፣ አዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በትራክተር፣ ቤለሮች፣ መውቂያዎች እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችና ላይ ሰርቶ ማሳያዎች እና ቴክኒካል ስልጠናዎች ተሰጥቷል።

ለዕቅድ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል በአማራና ትግራይ ክልል በተከሰተው ጦርነት የመረጃ ዕጥረት መኖሩ፣ በሶማሌ እና ቤኒሻንጉል ክልል በተለያዩ ምክንያቶች መረጃዎች አለመሰብሰቡ (በክልሎች የግብርና ሜካናይዜሽን መዋቅር አለመኖሩ) ፣ ሪፖርቱ በተለያዩ ትላልቅ የግልና የመንግስት እርሻ ልማቶች የተሰሩ በማሽን የሰብል አጨዳና ውቂያ መረጃን ያላካተተ መሆኑ፣ በግብርና ዕድገት ፕሮግራም ተገዝተው ለ10 የሜካናይዜሽን አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ሊሰራጩ የነበሩ ማሽነሪዎች በግዢ ሂደት መዘግየት ባለመሰራጨቱ ስልጠናውን ለማከናወን አልተቻለም።

## 8.5 የግብዓት ግዥ ፋይናንስ አቅርቦት

ለ2014 በጀት ዓመት የግብዓት መግዣ ብር 29.993 ቢ/ን ብር የተፈቀደ ሲሆን የአለም የማዳበሪያ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ተጨማሪ ብድር አስፈልጓል። በመሆኑም ከብሔረዊ ባንክ 48.2 ቢ/ን ብር እና 1 ቢ/ን የአሜሪካን ዶላር ተፈቅዶ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ተደርጓል። በተጨማሪም የተፈጠረውን ወቅታዊ የዋጋ ንረት ተከትሎ የፌዴራል መንግስት ለአፈር ማዳበሪያ የ15 ቢ/ን ብር ድጎማ አድርጓል።

## 8.6 የግብርና ምርት ግብይት

የግብርና የወጪ ንግድ በሚመለከት የቡና ሻይና ቅመማቅመም 314,291 ቶን ምርት ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 312,196.20 (99.33 በመቶ) እና የሆርቲካልቸር 363,267 ቶን ምርት ታቅዶ 326,917 (89.99 በመቶ) ሲሆን፣ በድምሩ 677,558 ቶን ምርት ለመላክ ታቅዶ 639,113.2 (94.33 በመቶ) ተከናዉኗል። በተመሳሳይ በገቢም ከቡና ሻይና ቅመማቅመም 1,155.33 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማስገኘት ታቅዶ 1,443.26 (124.92 በመቶ) እና ከሆርቲካልቸር 589.90 ሚ/ን ታቅዶ 628.58 (106.56 በመቶ) በድምሩ 1,745.24 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ 2,071.84 (118.71 በመቶ) ተከናዉኗል። ከዚህ ውስጥ ከጠቅላላ ከተላከው ቶን ምርት በቅደም ተከተል ቡና፣ አትክልት፣ አበባ፣ ፍራፍሬ፣ ቅመማቅመም እና ሻይ 47.37፣ 27.81፣17.68፣ 5.66፣1.34 እና 0.14 መቶኛ ድርሻ ሲኖራቸው በጥቅሉ ቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም ምርቶች (48.85 በመቶ) እና ሆርቲካልቸር ምርቶች (51.15 በመቶ) ድርሻ አለቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ባስገኙት የአሜሪካን ዶላር ገቢ በቅደም ተከተል ቡና፣ አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ቅመማቅመም እና ሻይ 68.76፣ 26.14፣ 3.36፣ 0.84፣ 0.81 እና 0.09 መቶኛ የገቢ ድርሻ ሲኖራቸው፣ በጥቅሉ በገቢ ቡና፣ ሻይና ቅመማቅመም (69.66 በመቶ) እና ሆርቲካልቸር (30.34 በመቶ) ድርሻ ነበራቸው።

በተጨማሪም ከስጋና ወተት ምርቶችና ሌሎች ውጤቶች ማለትም፡- የበግና ፍየል ስጋ፣ የዳልጋ ከብት ስጋ፣ የእርድ ተረፈ-ምርት፣ የዓሣና ሌሎች ስጋ ምርት፣ ማር፣ ሰም እና ወተት የተገኘው ምርት በቶን እና ገቢ በሚ/ን አሜሪካን ዶላር እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩ ምርቶች (ወተትን ሣይጨምር) በጥቅሉ 18.938.28 ቶን ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 22,932.12 (100+ በመቶ) ተከናዉኗል፡፡ በዝርዝር የበግና ፍየል ስጋ 15,510.24 ቶን ታቅዶ 17,204.59 (110.92 በመቶ) ፣ የዳልጋ ከብት ስጋ 219.48 ቶን ታቅዶ 359.15 (100+ በመቶ) ፣ የእርድ ተረፈ-ምርት 2,618.80 ቶን ታቅዶ 4,632.76 (100+ በመቶ) ፣ ከዓሣና ሌሎች ስጋ ምርት 342.89 ቶን ታቅዶ 523.68 (152.73 በመቶ) ፣ ማር 13.46 ቶን ታቅዶ 53.91 (100+ በመቶ) ፣ ሰም 233.41 ቶን ታቅዶ 158.02 (67.70 በመቶ) የተከናወነ ሲሆን፡፡ የወተት ምርትን በተመለከተ 1,229,300 ሊትር ታቅዶ 805,595 ሊትር (65.53 በመቶ) ወደ ውጭ መላክ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ በጠቅላላ ከተላከው የስጋና ወተት ምርቶችና ሌሎች ውጤቶች በቶን ቅደም ተከተል በግና ፍየል ሥጋ ምርት፣ እርድ ተረፈ-ምርት፣ ዳልጋ ከብት ስጋ፣ ሰም፣ ማር እና ዓሣና የሌሎች ስጋ ምርት፣ 76.4፣ 20.43፣ 2.16፣ 0.74፣ 0.14 እና 0.13 መቶኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ **(ዝርዝሩ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ 1 ቀርቧል)** ፡፡

## ሠንጠረዥ 1፡- የ2014 የግብርና ውጭ ንግድ ምርቶች የተጠቃለለ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | የ2014 ዕቅድና አፈጻጸም በመጠን (ቶን/ሊትር) | | | የ2014 ገቢ ዕቅድ እና አፈጻጸም በሚ/ን. ዶላር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | አፈጻጸም | በመቶ | ዕቅድ | አፈጻጸም | በመቶ |
| **1** | **የቡና፣ሻይና ቅ/ ቅመም** | **314,291.00** | **312,196.20** | **99.33** | **1,155.33** | **1,443.26** | **124.92** |
| 1.1 | ቡና | 298,340.00 | 302,762.00 | 101.48 | 1,135.02 | 1,424.58 | 125.51 |
| 1.2 | ሻይ | 1,922.00 | 902.00 | 46.93 | 3.07 | 1.86 | 60.59 |
| 1.3 | ቅ/ቅመም | 14,029.00 | 8,532.20 | 60.82 | 17.24 | 16.82 | 97.59 |
| **2** | **የሆርቲካልቸር ምርቶች** | **363,267.00** | **326,917.00** | **89.99** | **589.90** | **628.58** | **106.56** |
| 2.1 | አበባ | 118,857.00 | 112,996.00 | 95.07 | 508.05 | 541.60 | 106.60 |
| 2.2 | አትክልት | 200,768.00 | 177,729.00 | 88.52 | 65.90 | 69.67 | 105.73 |
| 2.3 | ፍራፍሬ | 43,642.00 | 36,192.00 | 82.93 | 15.95 | 17.30 | 108.47 |
| **3** | **ጠቅላላ (1+2)** | **677,558.00** | **639,113.20** | **94.33** | **1,745.24** | **2,071.84** | **118.71** |
| **4** | **የስጋና ወተት ምርቶች** | **18,938.28** | **22,932.12** | **121.09** | **95.23** | **120.64** | **126.69** |
| 4.1 | የበግና ፍየል ስጋ | 15,510.24 | 17,204.59 | 110.92 | 85.23 | 104.29 | 122.36 |
| 4.2 | የዳልጋ ከብት ስጋ | 219.48 | 359.15 | 163.64 | 1.37 | 1.44 | 105.11 |
| 4.3 | የእርድ ተረፈ-ምርት | 2,618.80 | 4,632.76 | 176.90 | 6.43 | 12.77 | 198.60 |
| 4.4 | የዓሣና ሌሎች ስጋ ምርት | 342.89 | 523.68 | 152.73 | 0.07 | 0.66 | 916.67 |
| 4.5 | ማር | 13.46 | 53.91 | 400.55 | 0.07 | 0.22 | 305.56 |
| 4.6 | ሰም | 233.41 | 158.02 | 67.70 | 1.92 | 1.16 | 60.42 |
| 4.7 | ወተት (ሊትር) | 1,229,300 | 805,595 | 65.53 | 0.13 | 0.10 | 74.63 |
| **5** | **ጠቅላላ (4.1+4.2+4.3+4.4+4.5+4.6)** | **18,938.28** | **22,932.12** | **121.09** | **95.23** | **120.64** | **126.69** |
| **6** | **ጠቅላላ ድምር (3+5)** | **696,496.28** | **662,045.32** | **95.05** | **1,840.46** | **2,192.48** | **119.13** |

አጠቃላይ የግብርና ምርቶች 2,782.11 ሚ/ን የአሜሪካ ዶላር ለማስገኘት ታቅዶ 2,967.26 (106.66 በመቶ) ሚ/ን አስገኝቷል፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ከተመዘገበው 2,470.72 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ጋር ሲነፃፀር 469.75 (20.11 በመቶ) ሚ/ን ጭማሪ አሳይቷል፡፡ የግብርና ምርት ኤክስፖርት ከሁሉም ዘርፎች ከተገኘው አጠቃላይ ገቢ አንጻር ሲታይ 72 በመቶ ድርሻ ሲኖረው፣ የማኑፋክቸሪንግ 12 በመቶ እና የማዕድን 13 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በግብርና ምርቶች የተገኘውም ገቢ 4,122.18 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ነው፡፡ ለዚህም ቡና 48.01 በመቶ፣ አበባ 18.25 በመቶ፣ ጫት 13.22 በመቶ፣ የቅባት እህሎች 8.89 በመቶ፣ የጥራጥሬ ሰብሎች 7.23 በመቶ፣ አትክልትና ፍራፍሬ 2.87 በመቶ እና የቁም እንስሳት 0.97 በመቶ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ የግብርና ምርቶች የ0.56 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ግብርና የወጪ ንግድ ገቢ በየዓመቱ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ለዚህም የቡናና አበባ የወጪ ምርት ከፍተኛ ድርሻ ይዟል፡፡ ይህም ውጤት ሊገኝ የቻለው በዓለም ደረጃ የቡና ዋጋ መጨመሩ፣ ጥራቱ

መሻሻሉ እና ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ በመንግስት እና በተለያዩ የባለድርሻ አካላት በመደረጉ ነው።

የግብርና ዘርፍ ምርቶች የ2014 በጀት ዓመት አፈፃፀም ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም እና አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ 2,071.84 ሚ/ን (50.26 በመቶ) የአሜሪካን ዶላር ያስገኙ ሲሆን፣ ሁሉም የግብርና ውጤቶች /የቅባት እህሎች፣ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ የተፈጥሮ ሙጫና እጣን፣ ጫት እና የቁም እንስሳት ጨምሮ 1,095,690 ቶን በመላክ 2,782,110 ሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለመሰበሰብ ታቅዶ 2,967,265 (106.66 በመቶ) ገቢ ማግኘት ተችሏል። ይህም ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም የ20 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። ቅመማ ቅመም፣ የቅባት እህሎች፣ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ጫት እና የቁም እንስሳት በመጠንና በገቢ ከ2015 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር የመቀነስ አዝማሚያ ያሳዩ ሲሆን ቡና፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዕድገት አሳይቷል። በ12 ወራት በገቢ ከተያዘው ዕቅድ በላይ ያስመዘገቡ (72 በመቶ) ቡና፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ሥጋና ወተት የግብርና ውጤቶች ናቸው። እንደ አገር ከተገኘው የሁሉም ዘርፎች ገቢ 4,566,863.84 ሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር ውስጥ የግብርና ምርቶች ድርሻ 2,967,265.56 (65 በመቶ) ነው።

## 9. የግብርና ምርምር

### የምርምር ሙከራዎች/ጥናቶች

በበጀት ዓመቱ 2,584 የምርምር ሙከራዎችን ለማካሄድ ታቅዶ 2,490 (96.36 በመቶ) ሙከራዎች የተከናወኑ ሲሆን የ264 የምርምር ሙከራዎች ተጠናቋል።

### የቴክኖሎጂ እና መረጃ አቅርቦት ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ 491 የምርምር ውጤቶች (133 ቴክኖሎጂና 358 መረጃዎች) ለማውጣት ታቅዶ 420 የምርምር ውጤቶች (111 ቴክኖሎጂዎችና 309 መረጃዎች) (85.54 በመቶ) ወጥቷል።

### የቴክኖሎጂ ማላመድ ሥራዎች

ለአገሪቱ የግብርና ቀጠናዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ አገር በማስመጣትና በማላመድ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት ከማቅረብ አንጻር 99 ዝርያ/ቴክኖሎጂዎችን በማስመጣት የማላመድ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። በበጀት ዓመቱ 7 የሰብል፣ 2 የእንስሳት፣ 1 የግብርና ምህንድስና እና 2 የግብርና ባዮቴክኖሎጂ በድምሩ 12 ዝርያዎች የማላመድ ጥናታቸው ተጠናቆ ለብሔራዊ የዝርያ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቧል።

## የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ ለ30,883 (23,084 ወንድና 7,799 ሴት) ተጠቃሚዎች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ ታቅዶ ለ31,609 (23,758 ወንድና 7,851 ሴት) (100+ በመቶ) ተጠቃሚዎችን ለማስተዋወቅ ተችሏል፡፡

## የቴክኖሎጂ ማስፋት ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ 20,914 (15,470 ወንድ እና 5,444 ሴት) የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ታቅዶ ለ23,975 (19,218 ወንድ እና 4,757 ሴት) (100+ በመቶ) ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## የሰብል ምርምር ቴክኖሎጂዎች ብዜት አፈጻጸም

### አራቢ የዘር (የሰብል ዝርያዎች)

በበጀት ዓመቱ በዝርዝር ለተጠቀሱት ሰብሎች ማለትም በብርዕ፣ በአገዳ፣ በጥራጥሬ፣ በቅባት፣ በኢንዱስትሪ፣ በአትክልት፣ በስራስር፣ በመዓዛማና መድሃኒት፣ በቅመማ ቅመም፣ በፍራፍሬ እና በቡና ሰብሎች በአጠቃላይ 1.35 ሺህ ኩ/ል፣ 91.95 ሺህ ችግኞች እና 372.2 ሺህ ቁርጥራጭ እና 22 ሺህ ቀንበጥ በአራቢ የዘር ደረጃ ለማባዛት ዕቅድ ተይዞ 1.47 ሺህ ኩ/ል (100+ በመቶ) ፣ 136.54 ሺህ ችግኞች (100+ በመቶ) ፣ 463.5 ሺህ ቁርጥራጭ እንዲሁም 23.49 ሺህ ቀንበጥ ሊባዛ ችሏል፡፡

### ቅድመ-መስራች ዘር (የሰብል ዝርያዎች)

በቅድመ-መስራች ዘር ደረጃ 315.8 ኩ/ል ሁለት የድንች ዝርያዎች ዘር፣ 8,100,000 የሰብል ቁርጥራጮች ለማባዛት ታቅዶ 315.97 ኩ/ል ዘር እና 7,510,000 ቁርጥራጭ ሊባዛ ችሏል፡፡

### መስራች ዘርና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች

በመስራች ዘር ደረጃ የሀገሪቱን የግብርና ልማት ስራ ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ 435 ኩ/ል ሁለት የድንች ዝርያዎች ዘር፣ እንዲሁም 6,850 የሰብል ችግኞች ለማባዛት ታቅዶ 330 ኩ/ል ድንችና 7,093 የኮክ እና የአፕል ችግኞችን ለማባዛት ተችሏል፡፡

## የእንስሳት እና የእንስሳት መኖ ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በእንስሳት ቴክኖሎጂዎች 1,550 ሌይንግ የሐር ትል እንቁላል፣ 70 እናት ንብ፣ 120 የንብ ጠላት ማጥመጃ ቀፎ፣ 170 የቀንድና የዳልጋ ከብቶች፣ 420 በግና ፍየሎች፣ እንዲሁም 1,150,000 የዓሳ ጫጩት ለማባዛት ታቅዶ 145 ጊደሮች፣ 20 ኮርማዎች፣ 348 በግ፣ 120 ፍየል፣ 1,062,900 የዓሳ ጫጩት፣ 1,510 እንቁላል ጣይ የሐር ቢራቢሮ፣ 75 እናት ንብ፣ 125 የንብ ጠላት ማጥመጃ ቀፎዎች ተባዝቷል፡፡

የእንስሳት መኖን በተመለከተ በ2014 በጀት ዓመት 176.20 ኩ/ል ዘር፣ 12,000 ቁርጥራጭ፣ እንዲሁም 25,000 ችግኝ ለማባዛት ታቅዶ 208.09 ኩ/ል፣ 11,100 ቁርጥራጭ፣ እንዲሁም 38,500 ችግኞች ተባዝቷል፡፡

### የተፈጥሮ ሃብት ቴክኖሎጂዎች ብዜት

በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ልማት የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ 7,000 ፓኬት የራይዞቢያ ሕየወ-ማዳበሪያ (ባዮፈርቲላይዘር)፣ 2 ኩ/ል የቨርሚኮምፖስት ትል፣ እንዲሁም 30 ኩ/ል ቨርሚ ኮምፓስት ለማባዛት ታቅዶ 7,148 ፓኬት የራይዞቢያ ሕያው-ማዳበሪያ፣ 3.6 ኩ/ል የኮምፖስት ትል፣ 60.51 ኩ/ል ቨርሚ ኮምፓስት ተባዝቷል፡፡ ተጨማሪ ፍላጎት በመፈጠሩ ምክንያት አፈፃፀሙ ከፍ ሊል ችሏል፡፡

### የስንዴ ዘር ብዜት

የስንዴ ዝርያዎችን ብዜት በተመለከተ ለሚቀጥለው ምርት ይውል ዘንድ በ950 ሄ/ር መሬት ላይ ምርጥ ዘር (የመጀመሪያ ትውልድ ዘር) በመስኖ ለማባዛት ታቅዶ በጠቅላላው 2,588.33 ሄ/ር በዘር የተሸፈነ ሲሆን፣ ከተሰበሰበው 2,414.89 ሄ/ር ላይ 93,614.5 ኩ/ል ዘር ለማግኘት ተችሏል፡፡

### ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች

በበጀት ዓመቱ 60,963 (42,645 ወንድና 18,318 ሴት) ተጠቃሚዎችን ለማሰልጠን ታቅዶ ለ61,968 (43,726 ወንድና 18,242 ሴት) (100+ በመቶ) የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ማሰልጠን ተችሏል፡፡

## 10. ህብረት ስራ ማህበራት

በበጀት ዓመቱ 21,058 የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማጠናከር ታቅዶ 19,435 (92.3 በመቶ) መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከር ተችሏል፡፡ እንደ ሴክተር በአጠቃላይ ኅብረት ሥራ ማህበራት ባልተዳረሱባቸዉ አካባቢዎች እና ችግሮቻቸውን በተናጠል መፍታት ያልቻሉ የማህበረሰብ አካላትን በፍላጎታቸው መሠረት ትኩረት በመስጠት በበጀት ዓመቱ 1,000 አዳዲስ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት ታቅዶ 2,289 (100+ በመቶ) መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት ተችሏል፡፡

ነባር የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተሰማሩበት ዘርፍ ጠንካራና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የውስጥ የካፒታል አቅማቸዉን ለማሳደግ እንዲሁም አዳዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በጠንካራ የካፒታል አቅም ለማቋቋም ብር 2.28 ቢ/ን ብር ታቅዶ በመሠረታዊ ብር 1.8 ቢ/ን እና በዩኒየን ብር 572.6 ሚ/ን በፌዴሬሽን ብር 15.75 ሚ/ን በአጠቃላይ 2.39 ቢ/ን ብር (100+ በመቶ) የካፒታል አቅማቸዉን ማሳደግ ተችሏል፡፡ በዚህም የተሻለ አፈፃፀም በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በሲዳማ ክልሎች ታይቷል፡፡

የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች በሥራቸው የሚያቅፏቸውን ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር በበጀት ዓመቱ 2,375 የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የዩኒዬን አባል ለማድረግ ታቅዶ፤ 621 (32.7 በመቶ) መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በዩኒየኖች አባል ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የዩኒየን አባል እንዲሆኑ አስገዳጅ ሕግም ይሁን የአሠራር መመሪያ ባለመኖሩ በኅብረት ሥራ ማህበራቱ ፈቃደኝነት ተመስርቶ አባል የሚሆኑ በመሆኑ ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ግብይት ድርሻ 24 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 22.3 (92.92 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በዓለም አቀፍ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት አንጻራዊ በሆነ መንገድ በአገራችንም ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለመከላከል በማቀድ በሀገራችን ውስጥ ባሉት የክልል እና የዞን ከተሞች ውስጥ የመንገድ ዳር የቅዳሜ እና የእሁድ ገበያ በየሳምንቱ እንዲሁም ኢግዝቢሽኖችንና ባዛሮችን በየክልሉ ተደርጓል፡፡ ዕቅዱን ለማሳከት የተሻለ ጥረት ቢደረግም ዕቅዱን በታቀደው ልክ መፈጸም ያልተቻለበት በዋናነት የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ትስስር ውል ቢፈጽሙም የተሻለ የገበያ ዋጋ ሲያገኙ ላገኙት ገዥ የመሸጥ ሁኔታ ያለ በመሆኑ ለሸማች በውል ከማቅረብ አንጻር አሁንም ሥራ የሚጠይቅ የቤት ሥራ እንዳለ ያሳያል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርቶች የወጪ ግብይት መጠን ድርሻ 22 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 15.50 (70.45 በመቶ) ማድረስ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በሀገር ውስጥ ያለው የወቅቱ የአገራዊ ሁኔታ ጫና፤ የምርቱ የሀገር ውስጥ ገበያ ዋጋ ወደ ውጪ ከሚላከው ከፍ በማለቱ ለውጪ ገበያ ከማቅረብ ይልቅ ለሀገር ውስጥ ገበያ የማቅረብ አዝማሚያ መኖሩ፣ የምርት ጥራት ዱካውን የሚገልጽ ዓለም አቀፍ የጥራት የምስክር ወረቀት በየጊዜው መጠየቁ እና ክፍያው ከፍተኛ መሆኑ፣ የምርት ግዥ ዋጋ ከፍተኛ መሆን እና በዓለም አቀፍ ዋጋ ጋር መወዳደር አለመቻል፣ ማር፣ እጣን እና ሙጫ በሰሜኑ የአገራችን ክልሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ኤክስፖርት ይደረግ የነበሩ እና አሁን ባለው አገራዊ ሁኔታ ኤክስፖርቱ በመቆሙ፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ ከጥራት ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮች ባለመፈታቱ ከችግሩ ማገገም አልተቻለም፡፡ የሀገር ውስጥ ምርት ለመሰብሰብ በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ለግብይት የሚያስፈልግ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር መኖሩ እና በወረራ የተያዙ አካባቢዎች የግብይት ተሳትፎ መቀነስ በዕቅድ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ምክንያት ሆኗል፡፡

በኑሮው የተረጋጋ ሕብረተሰብ እንዲኖር ከማድረግ አንጻር በበጀት ዓመቱ 12 ቢ/ን ብር የሚያወጣ የተለያየ የግብርና የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እና መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ ምርቶች ግብይት ለማካሄድ ታቅዶ፤ ብር 7.377 ቢ/ን የሚያወጣ የተለያየ የግብርና የኢንዱስትሪ ሸቀጦችና ምርቶች፣ እንዲሁም መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ ምርቶች ግብይት በማካሄድ አባላትን እና ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ 3 ቢ/ን ብር ለመቆጠብ ታቅዶ፤ ብር 3.14 ቢ/ን ብር ከዕቅድ በላይ (100+ በመቶ) መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው ኦሮሚያና አማራ ክልሎች፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በፌዴራል የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው።

በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን በማሳደግ በበጀት ዓመቱ ብር 3 ቢ/ን ብር ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ብድር ለማሰራጨት ታቅዶ፤ ብር 6.85 ቢ/ን ብር ለ457,562 (ወንድ 291,879 ሴት 165,683) አባላት በብድር አሰራጭተው በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ ውሏል። የገንዘብ ቁጠባና እንቨስትመንት ጥሩ አፈጻጸም ያላቸው አማራ፣ ኦሮሚያ፣ እና ደቡብ ክልሎች ናቸው። በአብዛኛው በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰራጨው ብድር በጊዜ የተገደበ በመሆኑ የተመለሰውም ብድር ተመልሶ ለሌሎች በብድር ዳግም ስለምሰራጭ ከዕቅድ በላይ ማሰራጨት ተችሏል።

## 11. ግብርና ትራንስፎርሜሽን

የገበያ መር ኩታ ገጠም እርሻ (ክላስተር) ዘዴ በአምስት ክልሎች (በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕ/፣ ሲዳማ እና የደቡብ ምዕራብ ህዝቦች) በአምስቱ ዋና ዋና ሰብሎች (ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ቢራ ገብስ እና ሰሊጥ) 3.6 ሚ/ን አርሶ አደሮችን በማሳተፍ 2.6 ሚ/ን ሄ/ር ማሳ እንዲሸፈን የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 1.4 ሚ/ን ሄ/ር ማሳ በ1.9 ሚ/ን በአርሶ አደር ምርት ክለስተር ተሳታፊ አርሶ አደሮች የተሸፈነ ነው። የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር አርሶ አደሮች ለምርጥ ዘር 2.4 ሚ/ን፣ ለማዳበሪያ 3.2 ሚ/ን እና ለግብርና ግብዓት ብድር 488,600 ተደራሽ ሆኗል። ከዚህም ውስጥ ምርጥ ዘር 63 በመቶ፣ ማዳበሪያ 59 በመቶ እና ለግብርና ግብዓት ብድር 68 በመቶ የአርሶ አደር ምርት ክላስተር ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ናቸው።

በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ እና ሲዳማ ክልሎች የቅድመና ድህረ ምርት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር አርሶ አደሮች ብዛት 1.59 ሚ/ን ሲሆኑ፣ ከዚህም ውስጥ 1.18 ሚ/ን (75 በመቶ) አርሶ አደሮች የአርሶ አደር ምርት ክላስተር ፕሮጀክት አርሶ አደሮች ናቸው። ከ2.6 ሚ/ን ሄ/ር ማሳ ላይ 99.8 ሚ/ን ኩ/ል ምርት ተሰብስቧል። ከዚህም ውስጥ 1.4 ሚ/ን ሄ/ር ማሳ (53.8 በመቶ) እና 62 ሚ/ን ኩ/ል ምርት (62 በመቶ) የአርሶ አደር ምርት ክላስተር ድርሻ ነው።

በአምስቱም ዋና ዋና ሰብሎች (ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ቢራ ገብስ እና ሰሊጥ) የተሸጠ ምርት (Market Surplus) 32.1 ሚ/ን ኩ/ል ሲሆን የሽያጩም ግምት 82.2 ቢ/ን ብር ነው። ከዚህ ጠቅላላ የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር አርሶ-አደሮች ምርትና የምርት ሽያጭ ውስጥ 18.3 ሚ/ን ኩ/ል (57 በመቶ) እና 46.2 ቢ/ን ብር (56.2 በመቶ) የአርሶ አደር ምርት ክላስተር ድርሻ ነው። ከዚህም ውስጥ 7.9 ሚ/ን

ኩ/ል ምርት የኮንትራት ሽያጭ ውል የተፈረመበት ሲሆን የምርቱ ዋጋም 22.7 ቢ/ን ብር ነው፡፡ በኮንትራት ፊርማ ከተሸጠው ውስጥ 5.8 ሚ/ን ኩ/ል ምርት (73.4 በመቶ) እና 15.6 ቢ/ን የምርት ዋጋ (68.7 በመቶ) የአርሶ አደር ምርት ክላስተር ድርሻ ነው ፡፡

የአቮካዶ ኤክስፖርትን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 2,910.38 ቶን ምርት ወደ ውጭ የተላከ ሲሆን 1,502,240.85 የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን ሜጫ ወረዳ እና አካባቢው የተሻሻለ የሀስ አቮካዶ ዝርያ በክላስተር በማምረት 170 ቶን ምርት ለመላክ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን በሉሜ ወረዳ የተሻሻለውን የሀስ ዝርያ አቮካዶ ምርትን በክላስተር በማምረት ለአውሮፓ ገበያ ማቅረብ ተችሏል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት የሙከራ ፕሮጀክት ለመተግበር በኦሮሚያ፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕ እና አማራ ክልል 26,000 አርሶ አደሮች (ከዚህም 5,006 ሴቶች) የእርሻ እና የምርት መሰብሰብ የሜካናይዜሽን አግልግሎት በማዕከላቱ በኩል አግኝተዋል፡፡ የማዕከላት ግንባታ ጋለማ 95 በመቶ፤ አምቦ 82 በመቶ፤ ሲኮማንዶ 95 በመቶ፣ ጊቤ ዴዴሳ 98 በመቶ፣ መሊቅ 83 በመቶ፣ ወላይታ 55 በመቶ፣ ማንዴላ ተመስገን 90 በመቶ፣ ቡሬ ዳሞት 67 በመቶ እና ጎዛምን 25.9 በመቶ ደርሷል፡፡ በኦሮሚያ 4 ማዕከላት፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ 2 ማዕከላት፣ በአማራ 2 ማዕከላት በአጠቃላይ 8 ማዕከላት የመስክ ጉብኝት በማካሄድ የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

የግብርና ግብዓትና አገልግሎት ፕሮጀክት በተመለከተ 28 ማዕከላት ሚጠበቅባቸውን መስፈርት በማሟላት ወደ ስራ የገቡ ሲሆን እስከአሁን 186 ማዕከላት የግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ለ3.1 ሚ/ን ለአ/አደሮች በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡ የግብርና ግብዓት የኩፖን ሽያጭ ሥርዓት ፕሮጀክት በተመለከተ 7.7 ሚ/ን አርሶአደሮች የግብዓት ኩፖን ሽያጭ ስርዓትን በመጠቀም 12.3 ሚ/ን ኩ/ል ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘር እና ኬሚካሎችን በ22.4 ሚ/ን ብር ገብይቷል፡፡ 507 ሺህ (82 በመቶ ሴት) አርሶአደሮች 1.6 ሚ/ን ብር የግብዓት ብድር አግኝተው 1.47 ሚ/ን ኩ/ል ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘር እና ኬሚካሎችን በአማራ ክልል ገብይተዋል፡፡

መሰረታዊ የገንዘብ አያያዝ እና የቁጠባ ግንዛቤን በአርሶ አደሩ ዘንድ ለማሳደግ የሚያስችል የሥልጠና ሞጁል ተዘጋጅቶ ወደ 8028 የድምፅ ቅብብሎሽ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን እስከ በጀት አመቱ ማገባደጃ ድረስ ከ122,100 በላይ ተጠቃሚዎች መረጃ እንዳገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በበጀት አመቱ ከ308,361 በላይ አዲስ ተጠቃሚዎች በስርአቱ የተመዘገቡ ሲሆን በጥቅሉ በአመቱ አዳዲስ እና ነባር የስርአቱ ተጠቃሚዎች ከ3,027,756 በላይ የስልክ ጥሪዎችን በማድረግ የመረጃ እና ምክረ-ሃሳብ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ ተጠቃሚዎች ግብይታቸውን በመረጃና በዕውቀት ላይ ተመስርተው እንዲወስኑ በበጀት ዓመቱ 29,325 ትክክለኛነታቸው የተረጋገጡ ሳምንታዊ የገበያ መረጃ በ6,077 ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማ የዓቅም ግንባታ ፕሮጀክት በተመለከተ በአቅም ምዘናና ክፍተት መለያ ዘዴ ለ173 (15 ሴት) የገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት ዩንየን ማኔጀሮች፤ የብድርና የሂሳብ ባለሙያዎች እንዲሁም የክልልና የዞን ኅ/ሥራ ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ለገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት የአቅም ክፍተትና ምዘና መለያ ዘዴ በመጠቀም ለ334 ገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት የአቅም ክፍተት የዳሰሳ ጥናትና አቅም ምዘና ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ለ340 የገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት ዩንየን ሃላፊዎችና ቦርድ አባላት በማህበራት አመራር፣ ፋይናንስና ቢዝነስ ማኔጅመንት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማህበራትን የዉስጥ አሰራርን ለማቀድና ለመተግበር የሚረዱ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች እንዲኖራቸዉ ለማድረግ በስጋት/አደጋ ማኔጅመንት እና በገንዘብ ዕዳና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲና መመሪያ ማንዋሎች ዝግጅት 100 በመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በተዘጋጁት ማኑዋሎች ስልጠና ለ51 (5 ሴቶች) የገ/ቁ/ብ/ህ/ሥ/ማህበራት ዩንየን ማኔጀሮችና ለኅ/ሥራ ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡

ከ17 የምርምር ተቋማት የተውጣጡ የግብርና ተመራማሪዎችን ጨምሮ ለ595 የግብርና ባለሙያዎች፣ የልማት አጋሮች እንዲሁም የ8028 የሄልፕ ዴስክ (የእገዛ ዴስክ) ምላሽ ሰጭዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልል ለ212 የማዕከላት ቅጥር ሠራተኞች የንግድ ስራ አመራር ስልጠና ተሠጥቷል፡፡ በተጨማሪም በደቡብና በአማራ ክልል የሚገኙ 21 ማዕከላት የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ (AI Service) ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይህም ስራ ለማዕከላት ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ሲሆን ለአ/አደሮች ደግሞ የተሻሻሉ ዝርያዎችን እንዲያገኙ ያስችላል፡፡

የተቀናጀ ጥልቅ ያልሆነ የከርሰ ምድር ውሃ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ለመተግበር 24,774 ሄ/ር መሬት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኙ አትክልት ሰብሎች በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች ተሸፍኗል፡፡ 1,927,956 ኩ/ል ምርት (ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ቃሪያ፣ ካሮት፣ ጥቅል ጎመንና ሌሎች የአትክልት ሰብሎች) ጥልቅ ካልሆነ ጉድጓድ በወጣ ውሃ ተመርቶ በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች ለገበያ ቀርቧል፡፡

## 12. የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማጠናከር

በሁሉም ክልሎች የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎችን ቁጥር ለማሳደግ በታቀደዉ መሰረት የእማወራ፣ አባወራ፣ የባለትዳር ሴቶች እና ወጣቶች ተጠቃሚነት በማሳደግ ከመቶ ፐርሰንት በላይ ለማሳካት ተችሏል፡፡ ይህን በተሻለ ደረጃ ለማሳካት ከባለድርሻዎች ጋር በመቀናጀትና በርካታ ተግባራትን በማከናወን በሁሉም ክልሎች ለአርሶ/አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የሚሰጠውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት በማጠናከር የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች እርካታ ለማሰደግ እየተሰራ ነው፡፡ የእርካታ መጠኑን ለማወቅ የመጀመሪያ ደረጃ ዳሳሳ ጥናት በ7 ክልሎች ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሰረት በብዛት አርሶ አደር በሚገኝባቸው ክልሎች (አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት እና ሲዳማ) ያለው አማካይ እርካታ 65.42 በመቶ ሲሆን አርብቶ እና ከፊል አደር በስፋት በሚገኙባቸው ክልሎች

(ጋምቤላ፣ አፋር እና ሶማሌ) ያለው የእርካታ መጠን 29 በመቶ እንደሆነ የጥናት ውጤቱ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ እንደሀገር ያለው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች እርካታ 49.36 በመቶ እንደሆነ ከጥናት ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ብዛት በሺህ ቁጥር ወደ 11,982 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን ከክልሎች በተሰበሰበ መረጃ መሰረት የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች በሺህ ቁጥር 19,237 (161 በመቶ) ለማድረስ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከፍተኛ ሊሆን የቻለው ዒላማው የተቀመጠው የማዕከላዊ ስታቲክስ ኤጀንሲ የ2012 ዓ/ም መረጃ መነሻ በመደረጉ ነው፡፡ በሰብል ልማት እና በእንስሳት ሀብት ልማት የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚዎች በሺህ ቁጥር 7,804 ለማድረስ ታቅዶ 8,281 (106 በመቶ) ተከናወኗል፡፡ የሞዴል አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር ለማሳደግ በታቀደው መሰረት የሰብል ልማት፣ የተፈጥሮ ሀብት እና የእንስሳት ሀብት ልማት የተጠቃሚዎችን በሺህ ቁጥር 4,114 ለማድረስ ታቅዶ 2,868 (68.2 በመቶ) ማድረስ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ከትግራይና ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች መረጃ ማግኘት ባለመቻሉ ነው፡፡

በሁሉም ክልሎች በተለዩ የተሻለ አፈጻጸም በታየባቸው አሰራሮች ማለትም በእንስሳት፣ በሰብል፣ በተፈጥሮ ሀብትና ወይም በሌሎች ዘርፎች በኦሮሚያ ክልል የአርሶ/አርብቶ አደር በዓል ቀን በጅማ ዞን ቦተር ጦላይ፣ ሶኮሩ፣ ጎሬ ወረዳ በምዕራብ ሸዋ ዞን እሉ ገላን፣ ኤጀርሳ ላፎ እና ኤጀሬ ወረዳ በምስራቅ ወለጋ ዞን ጎቡ ሰዮ፣ ሲቡ ስሬ ፣ ዋዩ ጡቃ ወረዳ፣ በቡኖ በደሌ ዞን ዳቡ ሀና እና በደሌ ወረዳ የሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ የተሳታፊዎች ብዛት አርሶ አደር 3,339፣ ልማት ጣቢያ ባለሙያ 194፣ SMS 431 እና በየደረጃ ያሉ አመራር አካላት 326 በድምሩ 4,290 በተገኙበት በተላዩ ሰብል ክላስተር ላይ የመስክ ጉብኝት ተካሂዷል፡፡ አንድ የኢኮቴ የግብርና ኤክስቴንሽን መድረክ ለማዘጋጀት ታቅዶ በታቀደዉ መሰረት ለማከናወን ተችሏል የአፈፃፀም ንፅፅሩም 100 በመቶ ነዉ፣

## 13. የግብርና ቁጥጥር ሥራዎች

**የኤክስፖርት ሥጋና ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚዉሉ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ጤንነት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ከማድረግ አንጻር** በቦሌ ኤርፖርት ለሚወጣ ስጋ ለ15,500 ቶን ስጋ በቦሌ ኳራንቲን ጣቢያ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ18,358.48 (100+ በመቶ) ቶን ስጋ ምርመራ አገልግሎት ተደርጎ ከሀገር እንዲወጣ የይለፍ ፍቃድ ተሰጥቷል፡፡ ለ8,000 የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለምርቱ ለመስጠት ታቅዶ 8,714 (100+ በመቶ) የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ኤክስፖርቱን ለመደገፍ ተችሏል፡፡

**የእንስሳት ውጤቶች ተዋጽኦና ተረፈ ምርቶች ጤንነት ጥራትና ደህንነት በላቦራቶሪ ምርመራ ማረጋገጥን በሚመለከት** 1,858 ሺህ እንስሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 1,823.30 ሺህ

(98.13 በመቶ) እንስሳት ለመመርመር ተችሏል፣ 1,838 ሺህ እንስሳት የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 1,658 ሺህ (90.21 በመቶ) እንስሳት መመርመር ተችሏል፡፡

## የእንስሳት መኖ መድሃኒት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

በበጀት ዓመቱ ለ54 ነባር የመኖ ንግድ ድርጅቶች ዓመታዊ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ47 (87 በመቶ) የብቃት ፍተሻ በማድረግ ዕድሳት ሥራ ተከናውኗል፡፡ ለ2,500 ቶን የግዥና ቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ከ16 ድርጅቶች የቀረበውን 36 ዶክመንት በመገምገም ለ2,483.657 ቶን (90.22 መቶ) የዋጋ ግምቱ 4,208,440 የአሜሪካ ዶላር የሆነ የግዥና ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ለ30 የመኖ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ30 የመኖ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠ ሲሆን፣ እነዚህም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው የመኖ ንግድ ተቋማት በዝርዝር፡- የተቀነባበረ መኖ አምራቾች (በቊጥር-በቁ 12) ፣ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪዎች (በቁ. 12) የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች (በቁ.2) እና የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ ንግድ ድርጅቶች (በቁ.4) ናቸው፡፡

በዓመቱ 10 ከውጭ ሀገር የሚገቡ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ለመመዝገብ ታቅዶ 21 የተመዘገበ ሲሆን አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው አስመጪ ድርጅቶቹ ከአንድ በላይ ምርት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በማስመዝገባቸው ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ በተዘጋጀ ቼክሊስት በ40 የመኖ ንግድ ተቋማት ላይ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ39 (97.5 በመቶ) ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ በሕገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ንግድና ስርጭት ላይ 18 የህዝብ ንቅናቄ መድረክ በተቋቋሙ ግብረ ኃይሎች ላይ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 16 (88.9 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ በሕገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ንግድና ስርጭት ላይ የህዝብ ንቅናቄ መድረክ 6 ታቅዶ 5 የተከናወነ ሲሆን በተሳታፊዎች 240 ታቅዶ 190 ተከናዉኗል፡፡ አፈፃጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት ከሰላምና ደህንነት ችግሮች የተነሳ የታቀዱት ቦታዎች ሁሉ መድረስ ባለመቻሉ ነዉ፡፡

## የሰብል ግብዓትና ምርት ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

የዘር ጥራት፣ የፀረ ተባይ እና ማዳበሪያ ጥራት፣ ፍቱንነት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ፤ ፀረ-ተባይዎች ፣ ማይክሮ እና ማክሮ ንጥረ-ነገር ይዘት ያላቸው ማዳበሪያዎች 2,530 የቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ /Import permit/ ለመስጠት ታቅዶ 2,883 የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ /Import Permit/ ሰርተፊኬት ለባንክ ተሰጥቷል፡፡ የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎች፤ ፀረ-ተባይ አስመጪዎች፣ አከፋፋዮች፣ ቸርቻሪዎች እና ተጠቃሚዎች፣ የማዕጠንት አገልግሎት በሚሰጡ ድርጅቶች፤ የፍቱንነት ሙከራ አገልግሎት በሚሰጡ 202 ተቋማት ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

ታቅዶ በ34 ተቋማት ቁጥጥር፣ የክትትልና የድጋፍ ስራው ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የበጀትና የመስክ ተሽከርካሪ ዕጥረት ነው፡፡

ወደ ውጪ የሚላኩና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕፅዋትንና የዕፅዋት ውጤቶች የተቀባይ ሃገራት መስፈርትን አሟልተው መቅረባቸው ለመቆጣጠር ወደ ዉጪ ሀገር ለሚላክ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶቻቸዉና ቁጥጥር በሚካሄድባቸዉ ቁሳቁሶችን ፍተሻ በማካሄድ የዕፅዋት ምርት የጤናና ጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማስጠት 1,050,000 ቶን ምርት ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 957,084 ቶን (91 በመቶ) ምርት ላይ ምርመራ ተከናውኖ ወደ ተለያዩ ሃገራት እንዲላክ ተደርጓል፡፡ ወደ ውጪ ለሚወጣ የዕፅዋት ምርት የጤንነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት መስጠት 12,000 ለመስጠት ታቅዶ 12,068 (100 በመቶ) ተሰጥቷል፡፡ የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ /Import Permit/ ተሰጥቷቸዉ ለብዜት/ዘር አገልግሎት የገቡትን ዕፅዋቶች የድህረ-መግባት ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የምርምር ተቋሞች፣ ዩንቨርሲቲዎች እና የግል ኩባንያዎች የቀረቡ የዕፅዋት እጩ ዝርያዎችን በመስክ ግምገማ ማካሄድ፣ ከተለያዩ የምርምር ተቋሞች፣ ዩንቨርሲቲዎች እና የግል ኩባንያዎች የቀረቡ 110 ዕጩ ዝርያዎችን የመስክ ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ 93 ዝርያዎች (84 በመቶ) ተገምግሟል፡፡

የአትክልት ዝርያዎችን ከውጪ በማስገባትና ለአርሶአደሩ ለማቅረብ ጥያቄ ለሚያቀርብ ለ20 የአትክልት ዘር አስመጪዎች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠትና ለማደስ ታቅዶ 16 (80 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ በ240 የተለያዩ የአትክልትና የሰብል ናሙናዎችን ናሙና በመውሰድ በላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን ታቅዶ በ154 (64 በመቶ) የተለያዩ የአትክልት/የሰብል ናሙናዎች ላይ ተካሂዶ የሚመለከታቸው አካላት ውጤቱን እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

## 14. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### 14.1 የግብርና ዘርፍ የሥራ ዕድል ፈጠራ

የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም የማሳደግ ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ 1,828,183 የስራ ፈላጊዎች ምዝገባና ልየታ ለማድረግ ታቅዶ 3,765,320 (100+ በመቶ) ልየታ ሥራ ተከናውኗል፡፡ ለ5,798,086 ዜጎች ስለ ግብርና ስራ እድል ፈጠራ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ6,004,257 (100+ በመቶ) ዜጎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡

በግብርና ሥራ መስክ ለ1,023,000 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ1,045,424 (102 በመቶ) የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ ውስጥ ለወንድ 511,501 ታቅዶ 729,409 (100+ በመቶ) እና ለሴት 511,501 ታቅዶ 316,015 (30 በመቶ) የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ በግብርናው ዘርፍ ከተፈጠረው ሥራ መስክ ውስጥ በቋሚ ወንድ 608,176 ሴቶች 255,708 በድምሩ 863,884፣

እንዲሁም በጊዜያዊነት ወንድ 121,233 እና ሴት 60,307 በድምሩ 181,540 ሲሆን፣ በአጠቃላይ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ በቋሚነት 83 በመቶ እና በጊዜያዊነት 17 በመቶ የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

ከተፈጠረው የስራ ዕድል በተፈጥሮ ሀብት 315,000 (157,500 ሴት) ታቅዶ 60,782 (17,121 ሴት) (16.89%) በሰብል ልማት 86,100 (43,050 ሴት) ታቅዶ 551,281 (149,891 ሴት) (100⁺ በመቶ) በአትክልትና ፍራፍሬ 268,800 (134,400 ሴት) ታቅዶ 99,459 (24,887 ሴት) (33.22 በመቶ) በእንስሳት 611,100 (305,550) ታቅዶ 328,316 (118,022 ሴት) (50.46 በመቶ)፣ እንዲሁም በሌሎች የግብርና ዘርፎች 16,164 (7,349 ሴት) የስራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን፣ አብዛኞቹ ክልሎች ሰብል ልማት ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው የሰብል ልማት አፈፃፀም እጅግ ከፍተኛ ሲሆን የሌሎች አፈፃፀም አነስተኛ ቢሆንም አማካይ አፈፃፀም መስመዝገብ ተችሏል፡፡ የገበያ ትስስር ለመፍጠር ብር 8,186,973,152 ለ102,692 ኢንተርፕራይዞች ለመፍጠር ታቅዶ ብር 8,296,500,121 (100⁺ በመቶ) ድጋፍ በማድረግ የ102,692 ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ ለ2,670 ኢንተርፕራይዞች፣ የሂሳብ አያያዝ ለ6,624 ኢንተርፕራይዞች እና የኦዲት አገልግሎት ለ3,935 ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለ317 ኢንተርፕራይዞች፣ የሂሳብ አያያዝ ለ4,068 ኢንተርፕራይዞች እና የኦዲት አገልግሎት ለ2,980 ኢንተርፕራይዞች ተሰጥቷል፡፡ የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግርን በተመለከተ በጥቃቅን ደረጀ ለ26,864 ኢንተርፕራይዞች፣ በአነስተኛ ደረጃ ለ4,007 ኢንተርፕራይዞች፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 272 ኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር ለማድረግ ታቅዶ በጥቃቅን ደረጃ 20,735 ኢንተርፕራይዞች፣ በአነስተኛ ደረጃ ለ4,994 ኢንተርፕራይዞች፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 235 ኢንተርፕራይዞች የደረጀ ሽግግር ተደርጓል፡፡

### 14.2 የምግብ ዋስትና

በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በቂ እና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ በመክፈል የምግብ ክፍተትን ከመሙላት አንፃር ለ7.9 ሚ/ን (4.132 ሚ/ን ሴት) ተጠቃሚዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ለፕሮግራሙ ማስፈፃሚያ ማለትም ለቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች፣ ለማህበረሰብ ልማት ሥራዎች፤ ለወረዳ አስተዳደራዊና የደመወዝ በጀት፤ ለክልሎች አስተዳደራዊ በጀት፤ ለክልሎች ለቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ እና ለኤሌክትሮኒክ ክፍያዎች የሚውል ብር 12,090,355,861.87 ወደ ክልሎች ለማስተላለፍ ታቅዶ ብር 12,090,355,861.87 (100 በመቶ) የተላለፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ እስካሁን ድረስ ብር 10,200,342,803 (84.4 በመቶ) ለተጠቃሚዎች ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከ2013 ወደ 2014 በጀት ዓመት የተላለፈው የገንዘብ ክፍያ ብር 83,698,247 ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ክፍያ ለመፈፀም ታቅዶ ብር 83,698,247 (100 በመቶ) ክፍያው የተፈፀመ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የምግብ ክፍያውን በተመለከተ 320,738.70 ኩ/ል ለመክፈል ታቅዶ 317,482 ኩ/ል

(99 በመቶ) ወደ ወረዳ ተንገዞ ለተጠቃሚዎቹ ክፍያው የተፈፀመ ሲሆን ክፍያው ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቀበት ምክንያት ፕሮግራሙ በሚሰራባቸው አንዳአንድ ክልሎች በተለይም በአፋር እና አማራ ክልል ባጋጠመው የፀጥታ ችግር እንደሆነ በተደረገው ክትትል ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን ክፍያ ቀልጣፈና ውጤታማ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ (E-Payment) የክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ ከ147 ወረዳዎች ላይ 57 አዳዲስ ወረዳዎችን በመጨመር ወደ 203 እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በድርቅ ለተጎዱ ለ2,739,182 ተረጂዎች በበጀት ዓመቱ የሶስት ወራት (የጥር፣ የየካቲትና መጋቢት) ብር 2,768,905,618 በኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሶማሌ ክልሎች በ111 ወረዳዎች ለከፋ የድርቅ አደጋ ለተጋለጡ ወገኖች ምላሽ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ 6,803,770 የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን በማህበረሰብ ልማት ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ባላቸው በተለያዩ ርዕሶች ላይ ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የሚተገበርባቸው 35 የገጠር ወረዳዎችን በወረዳ-ኔት የማገናኘት ስራ የተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ በ154 ወረዳዎች ላይ የዝርጋታ ስራው ተከናውኖ ወረዳዎቹ የዳታ እና የኢንተርኔት አገልግሎት በወረዳ-ኔት አማካኝነት እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡

የምግብ እህል ግዥ አፈፃፀምን በተመለከተ በ2013 በጀት ዓመት የግዢ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ የቀረው የ80,000 ሜ/ቶን ስንዴ ግዢ 72,500 ሜ/ቶን ስንዴ በውሉ መሠረት ርክክብ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የ30,000 ሜ/ቶን ስንዴ ግዢ ርክክቡ ተጠናቆ ወደ ማዕከላዊ መጋዘኖች ገቢ ሆኗል፡፡

### 14.3 ምግብና ስርዓተ-ምግብ

የኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት የአቋም ሰነድ እና የምግብ ሥርዓት ረቂቅ ፍኖተ ካርታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማዘጋጀት የተባበሩት መንግስታት ስብሰባ ላይ ቀርቧል፡፡ በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለጸጉ እና በምርምር ተለቀው ፓኬጅ ላልተዘጋጀላቸው ዝርያዎች ከስርዓተ-ምግብ አንጻር ፓኬጅ እና የተሰባጠረ ምግብ አዘጋጃጀት መመሪያ የማዘጋጀት፤ የማሳተምና የማሰራጨት፤ የምግብ አውደ ርዕይ እና የምግብና ስርዓተ-ምግብ ተግባቦት ረቂቅ መመሪያ፣ ለአርብቶ/ከፊል አርብቶ አደር ለልማት ጣቢያ ባለሙያዎች የሚውል የሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና (ሥ/ም/ተ/ግ) ማሰልጠኛ ማንዋል ከአጋር አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ሁኔታ ለመፍጠር መግባቢያ ሰነዶች ተዘጋጅቷል፡፡ በተዘጋጁ ሰነዶች፣ እንዲሁም በሥ/ም/ተ/ግ ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾችና የዲጂታል የግብርና መረጃ መሰብሰቢያ ሲስተም፣ በሞዴል መንደር ጽንሰ ሀሳብ እና በሥ/ም/ተ/ግ ላይ 938 (469 ሴት) የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በሶስት ክልሎች ሥ/ም/ተ/ግ ሞዴል መንደር ለመመስረት ወረዳ እና መንደር የመለየት ሥራ፤ የነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት፣ ይፋዊ የማስጀመሪያ ፕሮግራም፣ ሞዴል መንደሩን ለመመስረት የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውኗል፡፡ ለሞዴል መንደሩ ምስረታ በምግብ ንጥረ ነገር ይዘቱ የበለፀገ 4 ኩ/ል በቆሎ፣

2 ኩ/ል በአይረንና ዚንክ የበለፀገ ቦለቄ፤ 8.5 ኪ/ግ የአትክልት ዘር፣ 1,248 የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞች፣ 2,400 የብርቱካናማ ስኳር ድንችና 300 የካሳቫ ቁርጥራጭ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። በተጨማሪ 33 ኩ/ል የቦሎቄ ዘር፤ 17 ኪ/ግ የተለያየ የአትክልትና የመኖ ዘር፣ 320 የተለያዩ አነስተኛ የእርሻ መሳሪያዎች፣ እንዲሁም 40 ፍየሎችን በመግዛት ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

በማንጎ እና ጎመን ላይ የድህረ ምርት አያያዝ ላይ የማበረታቻ ስርዓት የሚያስፈልጋቸውን የሥ/ም/ተ/ግ ቴክኖሎጂዎች እና የምግብ ማቀነባበሪያ ኢንኩቤሽን ፍላጎት በ10 ግብርና ምርምር ማዕከላትና በ9 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የዳሰሳ ጥናት ተከናውኗል። የምግብና ስርዓተ ምግብ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና አፈፃፀም ላይ በሁሉም ክልሎች አንድ ጊዜ የድጋፍ ክትትል ተደርጓል። ለክልል የሥ/ም/ተ/ግ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ባለሙያዎች 42 ላፕቶፕ ኮምፒውተር የማሰራጨት እና ለፕሮጀክቱ ክልሎች ለእያንዳንዳቸው ብር 1,165,150.00 በድምሩ ብር 3,495,450.00 በማስተላለፍ የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲቀርብ ተደርጓል።

## 14.4 የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ

ዝቅተኛ የካርበን ልቀት ያላቸው ቴክኖሎጂዎች የተተገበረበት የእርሻ ማሳዎች ስፋት 3 ሺ.ህ ሄ/ር ታቅዶ 4.05 ሺ.ህ ሄ/ር ላይ ተከናውኗል። የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችን የሚቀንሱ የማጣጣምያና የማስተሰርይ፣ እንዲሁም ዝቅተኛ የካርበን ልቀት ያላቸው ቴክኖሎጂዎች በእርሻ ማሳዎች 3.67 ሚ/ን ሜ/ቶን CO2e ታቅዶ 2.37 (64.58 በመቶ)፣ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎችን በማከናወን 2.7 ሚ/ን ሜ/ቶን CO2e ታቅዶ 1.75 (64.81 በመቶ) እና የእንስሳት ልማት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ፣ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ስራዎችን በማጎልበት 4.31 ሚ/ን ሜ/ቶን CO2e ታቅዶ 2.78 (64.5 በመቶ) በአጠቃላይ ከግብርና ሴክተር የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝ 10.68 ሚ/ን ሜትሪክ ቶን CO2e ለመቀነስ ታቅዶ 6.9 ሚ/ን ሜትሪክ ቶን (64.61 በመቶ) CO2e መቀነስ ተችሏል። አፈፃፀሙ ከዕቅዱ በታች የሆነበት ምክንያት ከወረዳ የግብርና ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ያለው የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት ያልተጠናከረ እና ለዚህ ስራ ሊያግዝ በሚችል መልኩ ወጥ የሆነ አደረጃጀት አለመኖር፣ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ካርታ ስራ ድርጅት የዓመቱ የመሬት ሽፋን ለውጥ መረጃ በወቅቱ ባለመድረሱና ትንታኔ ውስጥ ባለመካተቱ ነው።

በግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲያረጋግጡ ለማስቻል በኦሮሚያና ጋምቤላ ክልል ለሚገኙ በሆርቲካልቸር፣ በጥጥ፣ በሰሊጥና እንስሳት ልማት ላይ ለተሰማሩ የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የክትትልና ድጋፍ ስራ ማከናወን ተችሏል። በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ የሚገኙ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላይ የተሰማሩ የህብረት ስራ ማህበራት የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲያረጋግጡ በኦሮሚያ ክልል በመቂ-ባቱ የአትክልትና ፍራፍሬ የህብረት ስራ ማህበራት

ታቅፈው የሚገኙትን በአትክልትና ፍራፍሬ በማምረት ስራ ላይ የተሰማሩ አርሶ አደሮችን የድጋፍና ክትትል ስራ ተከናውኗል፡፡ በክልሎች እየተተገበረ ያለውን የማጣጣሚያና የማስተሰርያ ስራዎችን ትግበራ ላይ በአማራ፣ በደቡብ፣ በሀረሪ፣ በድሬዳዋ እና በሶማሌ ክልሎች ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ለማጎልበት በ6 ክልሎች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡

## 14.5 የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ

ከፌዴራል እስከ ቀበሌ ለተወጣጡ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች፣ የዐቃቢ- ህግ ባለሙያዎች፣ ዳኞች፣ የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎች የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የህግ ማህበር፣ እንዲሁም ለፕሮጀክቶች ፈፃሚዎችና አስተባባሪዎች በስርዓተ-ፆታና በወጣቶች ጉዳይ፣ በምግብና ስነ-ምግብ፣ በራስ-መተማመን፣ በስርዓተ-ፆታ፣ አካቶ መስራት፣ Gender and Pastorialism፣ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ በካይዘን ስራ አመራር ፅንሰ ሀሳቦች እንዲሁም የወጡ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦችን ተግባራዊ ለማድረግ አንፃር፣ በሌሎች ተያያዥ አርዕስቶች ዙሪያ ለ1,654 የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ1,456 (918 ሴት) (88 በመቶ) አካላት መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል (ሰበታ) እና ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት የቀረበውን የልዩ ድጋፍ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ለ70 (55 ሴት) በየደረጃዉ ለሚገኙ ፈፃሚዎች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ለተወጣጡ የ3ኛ እና የ4ኛ ዓመት ተማሪዎች በአከባቢው ለሴቶች ነጻ የህግ አገልግሎት ለሚሰጡ 52 ተማሪዎች በFree Legal Service and Gender ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማጎልበት በሚ/ር መ/ቤቱ የሚገኙ ሁሉም የስራ ክፍሎች ተጠሪ ተቋማት፣ ፕሮግራሞች በሚያካሄዱት የልማት ተግባራት ውስጥ የአካታችነት/ አሳታፊነታቸዉን ለማሻሻል የሚያስችል ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ እንዲሁም ከአርብቶ አደር አካባቢዎች ለሶማሌ፣ ለደቡብ ኦሞ ዞኖች ወረዳዎችና ቀበሌዎች ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የሴቶችን የገበያ ትስስር ችግሮችን በመፍታትና ፍትሀዊ ተጠቃሚነታቸዉን ከማሳደግ እና በተቋሙ የሚገኙ ፕሮጀክቶች/ ፕሮግራሞች አላማ አንፃር በአማራ፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያና ሲዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እስከ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ድረስ የክትትል፣ ድጋፍና የዳሰሳ ጥናት ስራዎች ተሰርቷል፡፡ በምግብና ስነ-ምግብ፣ በራስ-መተማመን፣ በስርዓተ-ፆታ እና በከተማ ግብርና ፅንሰ ሀሳብና በሌሎች ተያያዥ አርዕስቶች ዙሪያ በአጠቃላይ ለ30 የፎረሙ አባላት የስልጠና/ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት ተችሏል፡፡ ከፎረሙ አባላት ዉስጥ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ

የሚገኙት 60 ሰራተኞችን በመለየት በቀጣይ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ የሚያስችል የማስፈፀሚያ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተፈጠረዉ ጦርነት ሳቢያ ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን መቶ ሺህ ብር በላይ በማሰባሰብ የምግብና፣ ሌሎችም ልዩ ልዩ ድጋፎች ተደርጓል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናትና አካል ጉዳተኞች የተለያዩ አልሚ ምግቦችንና ለንጽህና መስጫ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በመግዛት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቸይልድ ሁድ የካንሰር ህሙማን ድርጅት፣ እንዲሁም ደብረ-ሊባኖስ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከልን በማስተባበር ከብር 41,725 በላይ የሚያወጡ የምግብና የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ቀን የተለያዩ መሪ ቃሎችን መሰረት በማድረግ የሚ/ር መ/ቤቱ ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎችን፣ የተጠሪ ተቋማት ተወካዮችን እና ባለድርሻ አካላትን አሳታፊ ያደረገ 432 ተሳታዎች (216 ሴት) የግንዛቤና የምክክር መድረክ በማካሄድ እንዲከበር ተደርጓል፡፡ የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በሀረሪ ክልል ለሚገኙ የሴት የልማት ቡድን አደረጃጀቶች በመስኖ ስራዎች ተሰማርተዉ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ የሚያስችል ለመስኖ ስራ የሚዉሉ ግብዓቶች (ፓምፖችና ሌሎች ግብዓቶችን) ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## 14.6 ኤች አይቪ ኤድስ

የባህሪ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የተለያዩ የፀረ-ኤች አይቪ መልእክት የያዙ ጽሁፎች በዩቲኤስ ሁለት ጊዜ ለማስተላለፍ ታቅዶ ሁለቱም ጊዜ መልዕክቱ ተላልፏል፡፡ 2,500 ብሮሸር ለማሳተም ታቅዶ 2,500 ሙሉ በሙሉ ታትሞ ለሠራተኞችና የተጠሪ ተቋማት ተሰራጭቷል፡፡ እንዲሁም 1,000 የኤች አይቪ ኤድስ መልእክቶችን የያዘ ፖስተር ታትሞ ለተጠሪ ተቋማት እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

በተቋማችን ሠራተኞች በተቋቋመው የኤድስ ፈንድ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው 14 ሠራተኞች እና ወላጆቻቸውን በኤድስ ምክንያት ያጡ ሰባት ህጻናት 36,492 ብር ከኤድስ ፈንድ ወጭ በማድረግ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ኤች አይቪ በደማቸው የሚገኝ ሶስት የተቋማችን ሰራተኞች አዲስ ወደ ድጋፍና እንክብካቤው ውስጥ ገብተዋል፡፡ የባዮሜዲካል ሥራዎችን በሚመለከት 4,000 የወንድ ኮንዶም ለማሰራጨት ታቅዶ 4,128 ኮንዶም ለተቋሙ ሰራተኞች እና ለቀን ሰራተኞች ተሰራጭቷል፡፡

የስደተኛ ተቀባይ ክልሎችን (ሶማሌ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል እና ጋምቤላ) የግብርና ቢሮዎች፣ እንዲሁም አዲስ አበባና ኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኤች አይቪን አካተው እንዲሰሩ ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለስምንት ተጠሪ ተቋማት እና ለሌሎችም ስለ 2 ፐርሰንት በጀት አመዳደብና አጠቃቀም እና ስለ ኤድስ ፈንድ አደረጃጀትና አጠቃቀም ከኤች አይቪ ፎካል ፐርሰኖችና ከተቋሙ አመራሮች ጋር በጋራ ውይይት ተደርጓል፡፡ ለቡናና ሻይ ባለስልጣን ሠራተኞችና በስሩ ለሚገኝ ለቡና ጥራት ቁጥጥር ማዕከል

176 (55 ሴት) ሰራተኞች ለሁለት ቀናት የኤች አይቪ ሜይኒስትሪሚንግና የኤድስ ፈንድ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር 2 ፐርሰንት ከስራ መስኬጃ በጀት እንዲመድቡ እና ኤድስ ፈንድ እንዲያቋቁሙ ተደርጓል፡፡ ለጆይቴክ፤ ማናየ፣ ሼር ኢትዮጵያ የአበባ ልማት ድርጅቶች ስለ 2 ፐርሰንት በጀት አመዳደብ፣ የኤድስ ፈንድ አደረጃጀትና አጠቃቀም ከክሊኒክ ሀላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና ከተቋሙ አመራሮች ገለጻ ተደርጓል፡፡

## 15. የከተማ ግብርና ልማት

በረጅም ጊዜ የከተማ ግብርናን በተለያዩ ቴክኖሎጂ አማራጮች የማልሚያ ቦታ ይዞታ ጋር የተገናዘቡ ሞዴል ወይም ስታንዳርድ ዲዛይን ተዘጋጅቶ በባለድርሻ አካላት እና የሚመለከታቸው ተቋማት ተተችቶ ከዳበረ በኃላ በተመረጡ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤትና ከተማዎች የማስተዋወቂያ ሰርቶ ማሳያ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ የሚገባ ይሆናል፡፡ ሰርቶ ማሳያውን ለመተግበር የበጀት ማፈላለግ ሥራ ጎን ለጎን እየተሰራ ነው፡፡

## 16. በክልሎች የተሠጠ ልዩ ድጋፍ

ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ክልሎችን ከመደገፍ አንጻር የተለያየ ሙያ ስብጥር ያላቸው ባለሙያዎችን በክልሎቹ በመመደብ ተከታታይነት ያለው ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለክልሎቹ የአቅም ግንባታ ስልጠና እና የልምድ ልውውጥ በተያዘላቸው ጊዜ እንዲከናወኑ መከታተል፣ ማስተባበርና መተግበር ተችሏል፡፡

ባለድርሻ አካላት በማስተባበር በተመረጡ ወረዳዎች ላይ እየተከናወኑ ያሉ የመንደር ማእከላትን መሰረት ያደረገ የግብርና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን የግንባታ ሂደት በመከታተል፣ በቁሳቁስ እንዲሟሉ በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

በጓሮ አትክልት፣ በሰብል ልማት፣ በንብ፣ በዓሣ እና በዶሮ እርባታ ስራዎች ላይ ሙያዊ እገዛ በ3ቱም ክልሎች (ከቤ/ጉሙዝ ክልል በስተቀር) 2 ወረዳዎችን ከየክልሉ በመምረጥ ሞዴል ወረዳ (የአርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላትን) ለመፍጠር 2 ዙር ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

## 17. በተደጋጋሚ በድርቅ የሚጎዱ አካባቢዎችን ዘላቂ መፍትሄ መስጠት

በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎችን ለመደገፍ በተደረገው ጥረት የተጎዱ አከባቢዎች የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በመስራት ምርታማነታቸውን ለመመለስ 2.5 ሚ/ን ሄ/ር ታቅዶ 2.47 ሚ/ን ሄ/ር በሕብረተሰብ ተሳታፎ ተሰርቷል፡፡ የመስኖ ልማት ስራዎችን ማስፋፋት ከብሔራዊ ሜትሪዮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚሰጠውን ትንበያ መሠረት በማድረግ ወቅታዊ፣ ወርሃዊና የ10 ቀን ምክረ-ሀሳብ በማዘጋጀት ለግብርና ስራ ለባለሙያዎችና ለአ/አደሮች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ የአየር ንብረትን መሠረት ያደረገ የግብርና አሰራርን ለመተግበር አከባቢውን መሠረት ያደረገ የአየር ንብረት መረጃ በመስጠት

ሕብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በድርቅ መቋቋምና ዘላቂ አርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት መኖን በልማት አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግና የመኖ ባንክ እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

በአምስተኛው ዙር ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም (PSNP 5) ትኩረት በማግኘት ለሰብዓዊ ድጋፍ የሚሹ የሰብአዊ ድጋፍ ተጠቃሚዎች (Shock Responsive Transfer) ድጋፍን በተመለከተ የዕለት ደራሽ ተጠቃሚዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ የድርቅ ምላሽ እና ድጋፍ እቅድ መሠረት በድርቅ ለተጎዱ ለ2.9 ሚ/ን ተረጅዎች ብር 1.965 ቢ/ን በኦሮሚያ፣ ደቡብ እና ሶማሌ ክልሎች ለከፋ የድርቅ አደጋ ለተጋለጡ ወገኖች ምላሽ እንድተላለፍ ተደርጓል፡፡

## 18. የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም

የፋይናንስ አጠቃቀም በሚመለከት ለሚ/ር መ/ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት በመደበኛ 0.55 ቢ/ን እና በካፒታል 15.18 ቢ/ን ብር በድምሩ 15.72 ቢ/ን የተፈቀደ ቢሆንም የበጀት ዕጥረት ምክንያት ተጨማሪ በጀት ተፈቅዷል፡፡ ይህም ተጨማሪ መደበኛ በጀት (ለእፅዋት ጥበቃ የአውሮፕላንና ድሮን ግዥ ብር 900.55 ሚ/ን፣ ለእንስሳት ድንበር ዘላል በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ብር 70 ሚ/ን እና ለሰርዶ ልማት የወጣቶች መቋቋሚያ ድጋፍ ብር 26.78 ሚ/ን በድምሩ 997.33 ሚ/ን) በጀት አፈጻጸም ላይ ተጨምሯል፡፡

ተጨማሪ መደበኛ በጀት አካቶ አፈጻጸሙ 1.54 ቢ/ን ብር (100+ በመቶ) ፣ የካፒታል በጀት 18.67 ቢ/ን ብር (100+ በመቶ) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በመደበኛና በካፒታል አፈጻጸሙ 20.21 ቢ/ን ብር (100+ በመቶ) ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች እና የካፒታል በጀቱ በእርዳታ ከተፈቀደው በላይ ድጋፍ በመገኛቱ፣ ከአበዳሪ ተቋማት የተገኙ ድጋፎች ለላቦራቶሪ እቃዎች እና ለመስሪያ ቤቱ የፈርኔቸር ግዢ በጀቱ ተቀናጅቶ ሥራ ላይ በመዋሉ ምክንያት ነው፡፡ **(ዝርዝሩ በሠንጠረዥ 2፣ አባሪ ሁለት እና ሦስትን ይመልከቱ)**

**ሠንጠረዥ 2፡- የ2014 ዓ.ም የግብርና ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማት የመደበኛና የካፒታል በጀት ዕቅድ አፈጻጸም**

| ተ. ቁ | የፕሮግራም ስምና የበጀት ዓይነት | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የግብርና ዘርፍ (ሀ+ለ)** | **17,984.38** | **22,143.34** | **123.13** | |
| | መደበኛ | 2,277.14 | 3,173.78 | 139.38 | |
| | ካፒታል | 15,707.24 | 18,969.56 | 120.77 | |
| **ሀ** | **ግብርና ሚኒስቴር** | **15,723.60** | **20,207.73** | **128.52** | |
| | መደበኛ | 548.09 | 1,537.64 | 280.54 | |
| | ካፒታል | 15,175.51 | 18,670.09 | 123.03 | |
| 1 | **ስራ አመራርና አስተዳደር** | **292.76** | **297.06** | **101.47** | |
| | መደበኛ | 254.35 | 282.22 | 110.96 | ከዕቅድ በላይ የመጣበት ምክንያት ከሌላ ክፍል በጀት ዝውውር ስለተፈፀመ ነው፡፡ |
| | ካፒታል | 38.41 | 14.84 | 38.62 | |
| 2 | **እርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ፕሮግራም** | **1,834.15** | **3,857.31** | **210.31** | |
| | መደበኛ | 175.96 | 1,064.64 | 605.05 | ተጨማሪ 900.55 ሚ/ን ብር ለአውሮፕላንና ድሮን ግዢ በጀት በመፈቃዱ ነው፡፡ |
| | ካፒታል | 1,658.19 | 2,792.67 | 168.42 | |
| 3 | **የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም** | **11,785.24** | **13,858.65** | **117.59** | |
| | መደበኛ | 43.47 | 59.71 | 137.35 | ተጨማሪ የወጣቶች ማቋቋሚያ 26.78 ሚ/ን ከገንዘብ ሚኒስቴር በመሠጠቱ ነው፡፡ |
| | ካፒታል | 11,741.77 | 13,798.95 | 117.52 | ተፈቀደው በጀት በላይ አፈፃፀም የመጣበት ምክንያት ከእርዳታ ከተፈቀደው በላይ ስለተገኘ ነው፡፡ |
| 4 | **የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ምርትና ምርታማነት ፕሮግራም** | **1,788.63** | **2,179.19** | **121.84** | |
| | መደበኛ | 51.49 | 115.56 | 224.42 | ተጨማሪ 70 ሚ/ን ብር ለተለያዩ የድንበር ዘለል በሽታዎች የእንስሳት ክትባት አገልግሎት በመፈቃዱ ነው፡፡ |
| | ካፒታል | 1,737.14 | 2,063.63 | 118.79 | ከተፈቀደ በላይ ከአበዳሪ ተቋም ስለተገኘ በጀቱ ለላቦራቶር እቃ ግዢ እና ለመስሪያ ቤቱ ፈርኔቸር ግዢ ተጠቅሟል |
| 5 | **የግብርና ኢንቨስትመንት ግብዓትና ምርት ግብይት ፕሮግራም** | **22.82** | **15.52** | **67.99** | |
| | መደበኛ | 22.82 | 15.52 | 67.99 | |
| | ካፒታል | - | - | - | |
| **ለ** | **ተጠሪ ተቋማት** | **2,260.78** | **1,935.61** | **85.62** | |
| | መደበኛ | 1,729.05 | 1,636.13 | 94.63 | |
| | ካፒታል | 531.73 | 299.48 | 56.32 | |

## 19. የግብርና ሚኒስቴር የኦዲት ግኝት ምልከታ

ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ለረጅም ዓመታት የተከማቹና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ነቀፌታ አዘል የኦዲት አስተያየት (Adverse Audit Opinion) ሲያሰጡ የቆዩ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይ እና የተፈጥሮ ሚዘናቸዉን ያልጠበቁ ሂሳቦች ለማስተካከል በተደረገ ጠንካራ ድጋፍና ክትትል ከፍተኛ ለውጥ ለመምጣት የተቻለ ሲሆን፣ **ለአብነትም፡- ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ** በዋናው መ/ቤት ለረዥም ዓመታት ሲንከባለሉ የመጡ ብር 102.57 ሚ/ን እና በግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጆችና ማስተባበሪያው ብር 201.33 ሚ/ን በድምሩ 303.90 ሚ/ን ከነበረው ተሰብሳቢ ውስጥ በሚ/ር መ/ቤቱ ብር 88.98 ሚ/ን እና በኮሌጆችና ማስተባበሪያው ብር 135.13 ሚ/ን ብር በድምሩ 224.11 ሚ/ን (73.74 በመቶ) ሂሳቡ እንዲወራረድ የተደረገ ሲሆን፣ ቀሪው 79.79 ሚ/ን (26.26 በመቶ) የሚወራረድበት ወይም ከሂሳብ መዝገብ የሚሰረዝበት ውሳኔ ሃሳብ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ ቀርቧል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ **ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ** በሚ/ር መ/ቤቱ ብር 47.86 ሚ/ን ለሚመለከታው አካል ክፍያ በመፈጸም በሙሉ እንዲስተካካል ተደርጓል፡፡ በግብርና ቴ/ሙ/ሥ ኮሌጆችና ማስተባበሪያው ብር69.25 ሚ/ን ተከፋይ ውስጥ ብር 56.7 ሚ/ን (82 በመቶ) ተጣርቶ እንዲወራረድ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ እንደ አጠቃላይ የኦዲት ግኝት ከነበረዉ ተከፋይ ሂሳብ ብር117.09 ሚ/ን ወስጥ 104.54 ሚ/ን ብር (89 በመቶ) ማስተካከል ተችሏል፡፡

የግብርና ሚ/ር ለረዥም ዓመታት ነቀፌታ አዘል የኦዲት አስተያየት (Adverse Audit Opinion) ውስጥ የቆየ ሲሆን፣ አሁን በተወሰደው እርምጃ ከ2013 በጀት ዓመት ወዲህ አጥጋቢ የኦዲት አስተያየት (Clean Audit Opinion) ውስጥ ሊገባ ችሏል፡፡

## 20. ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ

በአዲሱ የአስፈጻሚ መ/ቤቶች አደረጃጀት በሀገር ደረጃ ከተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አደረጃጀቱ በሲቪል ሰርቪስ ፀድቆ የሠራተኛ ምደባ ስራ የተጀመራ ሲሆን ከ9ኙ ተጠሪ ተቋማት ውስጥ የ5ቱ ተቋማት የማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ጸድቋል፡፡ በሚ/ር መ/ቤቱ ከቡድን መሪ ጀምሮ ያሉ የስራ መደቦች ላይ ምደባው የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የሠራተኞች ምደባ 90 በመቶ ተጠናቋል፡፡ የ8 ተጠሪ ተቋማትን በሚመለከት የ6ቱ ተጠሪ ተቋማት (የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣ ኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን እና የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት) አደረጃጀቱ ላይ አስተያየትና ግብረ-መልስ ተሠጥቶ ምደባዉን የጀመሩ ሲሆን፣ የተቀሩት 3ቱ (የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ደን ልማት) አስተያየትና ግብረ-መልስ ተሰጥቶአቸው የማስተካከል ስራ እየሰሩ ነው፡፡
ከወሳኝ የሪፎርም ሥራዎች ውስጥ አንዱ የፖሊሲ ሪፎርም ሲሆን የማሻሻል ሥራው በአዲሱ የግብርና ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት አደረጃጀት መሰረት እንደገና ታይቶ፣ ረቂቅ ሰነዱ ተጠናቆ ለኢፌዲሪ

ፕላንና ልማት ሚኒስቴር የቀረበ ሲሆን በሚኒስቴሩ አስተያየት ከደበረ በኃላ ለሚኒስትሮች ምክር ቀርቦ ይጸድቀል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የስራ አካባቢን ምቹ ከማድረግ አኳያ የ3 ህንፃዎች የማሻሻያ ስራው ተጠናቆ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የአዳራሽ ግንባታና የህዝብ ቤተመጽሃፍት ግንባታ ሥራም 90 በመቶ ተጠናቋል፡፡ የግቢ ማስዋብ /ግሪኒንግ/ ሥራም ተጠናቋል፡፡ ወቅታዊ የሆኑ የግብርና ስራዎችን በቅርብ ለመከታተል የሚረዳ የሁኔታዎች መከታተያ (Situation Room) ተጠናቆ ስራ ጀምሯል፡፡

የግብርና መረጃን ዲጂታላይዝ ከማድረግ አኳያም ወደየክልሉ የተሰራጩ ታብሌቶች ወደ ስራ እንዲገቡ ከትግራይ እና ደቡብ ምዕረብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልሎች በስተቀር ለሁሉም ክልሎች እና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የተሰጡ ታበሌቶች ላይ ሶፍትዌር የመጫንና የአጠቀቃም ሥልጠና ለ979 (196 ሴት) ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡ ከሦስት ክልሎች በስተቀር (ትግራይ፣ ሲዳማ እና ደቡብ ምዕረብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች) ለተቀሩት ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የረሳቸዉን ዳታ-ቤዝ መፍጠር የሚያስችል ሰርቨርና ተያያዥ አክሰሰሪዎች ግዥ ተፈጽሟል፡፡

የዕቅድና ሪፖርት ሥርዓትን ዲጂታላይዝ ለማድረግ የ100 ቀን አቅድ አፈጻጸም በፓዎር ቢአይ (Power BI) እንዲሰራ በማድረግ የሚመለከተቸው አካላት መረጃ በያሉበት መሙላት እንዲችሉና መረጃዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## 21. የፕሮግራሞችና ኢኒሽቲቮች አፈፃፀም

የ10 አመት የልማት ዕቅዱን እና የተሻሻለውን ፖሊሲ በትኩረት ለመተግባር አራት አላማ ያለው 10 ሃገራዊ ፕሮግራሞች ተቀርፀው ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ እነዚህ ፕሮግራሞች የምግብና ስርዓተ-ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ በተለይም በአገር ውስጥ ገበያ ያለውን የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም በማጥበብ የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር እና በምግብ ንጥረ ነገር የበለፀገ ምግቦች አቅርቦት ማሳደግ፣ ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እና ሀገራዊ የምግብ ሉዓላዊነት ማረጋገጥ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ለማሳደግና እሴት ለመጨመር፣ የውጪ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግና ተወዳዳሪነት ማሳደግ ዋና አላማ ያደረጉ ናቸው፡፡ አስሩ ፕሮግራሞቸ ስንዴ፣ ሩዝ፣ ቅባት እህሎች፣ አትክልት፣ፍራፍሬ፣ ቡና፣ ዶሮ፣ ወተት፣ ቀይ ስጋ ልማትና አስቻይ ሁኔታዎችን ያካትታል፡፡

ወደ ተግባር ከገቡት ፕሮግራሞች ውስጥ የመስኖ ስንዴ አንዱ ሲሆን በበጀት አመቱ አዲስ 400 ሺህ ሄ/ር መሬት በማልማት 16 ሚ/ን ኩል ተጨማሪ ስንዴ ለማግኘት ታቅዶ የተሰራ ሲሆን 450.17 ሺህ መሬት በማልማት አስካሁን ድረስ ወደ 15.9 ሚ/ን (99.38 በመቶ) ኩ/ል ተሰብስቧል፡፡

የዶሮ ልማት ሌላው ወደ ስራ የተገባ ፕሮግራም ሲሆን የሞዴል የቤተሰብ ዶሮ እርባታ በ8,100 ቤተሰቦች በሲዳማ፣ ደቡብ፣ አማራና ኦሮሚያ ክልሎች በመተግበር በሚቀጥሉት አመታት ተጨማሪ 23 ሚ/ን እንቁላል እና 53.2 ቶን የዶሮ ስጋ ለማምረት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተከናውኗል፡፡ ሞዴል

የቤተሰብ ዶሮ እርባታ ፕሮጀክትን ለክልሎች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የማስተዋወቅ እና ግንዛቤ የማስጨበጥ  ስራ ተሰርቷል፡፡ ለመጀመሪያ ዙር 18 የጫጩት ማሳደጊያና 6 የመኖ ማቀናበሪያ ማዕከላት ግንባታ በአራቱ ክልሎች ተጀምሯል። በተጨማሪም የአንዳሳ፣ የፍቼ እና የቢሾፍቱ ዶሮ ማባዣ ማዕከላት ለፕሮጀክቱ የሚሆን 6,500 መስራች (እናት) የዶሮ ዝርያ በማዕከላቸው ማሳደግ ጀምሯል፡፡

የወተት ምርትን ማሳደግ ሌላው ፕሮግራም ሲሆን የወተት ላሞች ዝርያ ማሻሻል፣ መኖና አመጋገብ ማሻሻል እና ጤና አጠባበቅ በማሳደግ በሚቀጥሉት አመታት ተጨማሪ የላም ወተት ለማምረት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተከናውኗል። በአዳአ-በርጋ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ወልቂጤ እና ቻግኒ የምርምርና ዝርያ ማሻሻያ ማእከላት 680 የተሻለ የወተት ምርት ያላቸውን የሀገር በቀል ዝርያዎች (ቦረናና ፎገራ) ጊደሮችን በሰው ሰራ ዘዴ ማዳቀል ተጀምሯል። በተጨማሪም 3,924 የሴቴ ፆታ የሚያስወልዱ አባለዘር (Sexed Semen) እና ሌሎች የዝርያ ማሻሻል ግብዓቶች (ፈሳሽ ናይትሮጅንና ሲንክሮናይዜሽን ሆርሞን) ለክልሎች በማቅረብ የአንደኛና ሁለተኛ ዙር የማዳቀል ስራዎች ተከናውኗል። እንዲሁም 70 የተሻሻሉ ኮርማዎች ከዉጪ ሀገር በግዥ ማስገባት እና የኢምብራዮ ማሸጋገር (Embryo Transfer) ቴክኖሎጂን ለመተግበር የውጪ ግዢ በሂደት ላይ ነው። የዝርያ ማሻሻል ስራዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ሌላው ትግበራ የጥጃ ሞት መቀነስ ሲሆን በበጀት አመቱ በ5 ክልሎች እና 1 ከተማ መስተዳድር ከተለያዩ ወረዳዎች የተወጣጡ 170 ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ከወሰዱ በኃላ 795 በወተት ላም እርባታ ለተሰማሩ አርቢዎች የጥጆች ሞት ቅነሳ ፖኬጅ ላይ ትኩረት ያደረገ የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል። በተሻሻለ የጥጃ አያያዝ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። የወተት ምርት ለማሳደግ ክፍተኛ አስተዋፆ ያለው መኖና አመጋገብ ማሻሻል ሲሆን ይህንን ለማገዝ የሰብል ተረፈ ምርት ንጥረ ምግብ ይዘት ማሻሻያ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተረፈ ምርቱን ማሻሻል ላይ 3,500 ተጠቃሚዎች ስልጠና፣ በአርብቶ አደር አከባቢዎች የተፈጥሮ ግጦሽ አያያዝና አጠቃቀም በማሳደግ የግጦሽ ምርታማነትን ለማሻሻል 1,500 ሄ/ር ግጦሽ ልማት እንዲሁም የተሻሻለ የእንስሳት መኖ አመራረት፣ አያያዝ እና አጠቃቀምን ለማሳደግ 13,200 ሞዴል እና ተከታይ አርሶ አደሮች ስልጠና ተሰጥቷል።

## 22. ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ

በበጀት ዓመቱ ሚ/ር መ/ቤቱና ክልሎች በጋራ ተናበው የዓመቱን ዕቅድ ለመተግበር ይቻል ዘንድ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት የ2013 በጀት ዓመት አፈጻጸም በመገምገምና የ2014 እቅዶችን በማናበብ በቂ ኦረንቴሽን በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

የሴክተሩን የክትትልና ግምገማ አቅም ለማሳደግ ከልማት አጋሮች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በእቅድ ዝግጀት ክትትልና ግምገማ፣ እንዲሁም በፕሮጀክት አስተዳደር 30 ባለሙያዎች ሥልጠና ለማስጠት ታቅዶ ለ25 ባለሙያዎች (5 በመቶ ሴቶች) የ10 ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በሥርዓተ-ምግብ ተኮር

ግብርና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ከሚደገፉ ሶስት ክልሎች የሚተገበሩ ተግባራትን በመለየት ለእያንዳንዳቸው ብር1,165,150 በድምሩ 3,495,450 እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡

የገጠር መሬት አስተዳደር ሥርዓቱን በጠናከረ መሠረት ላይ በመገንባት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በቀበሌ ደረጃ መስጠት እንዲያስችል የቀበሌ የልማት ጣቢያ እና የወረዳ ሠራተኞችን በመሬት አስተዳደርና የመሬት ግብይት ዙሪያ በጽንሰ ሀሳብና በተግባር ላይ ያተኮረ ዕውቀት ለማስጨበጥ በተለያዩ ርዕሶች 3,190 (ሴት 503) ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

የመኸርና በልግ ሰብል ልማት ዋና ዋና የሰብል አብቃይ ክልሎች የበልግ ዝናብ ባለመጣሉ ጉዳት የደረሰበት የሰብል አይነት የቀነሰ ምርት በሰዉ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ከብሄራዊ አደጋ መከላከል ጋር ጥናት በማድረግ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የዕለት ደረሽ ድጋፎችን ያደረገ ሲሆን ሚ/ር መ/ቤቱ ከሴፍቲ ኔት፣ ከአንበጣ መከላከል ፕሮጀክት 15.5 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ተመንዝሮ ለዘር ግዢ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ከእንስሳት ፕሮጀክቶች 14 ሚ/ን ብር ለመኖ 2 ሚ/ን ለእንስሳት መድሃኒት ግዢ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በሀገራችን የሰሜኑ ክፍል በተከፈተዉ ጦርነት በአማራ እና አፋር ብሄራዊ ክልሎች በጦርነቱ ምክንያት በርካታ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በመፈናቀላቸው ለጉዳት የተዳረገዉን የማህብረሰብ ክፍሎች እንዲሁም በኦሮሚያ አፋር፤ አማራና በሶሚሊ ክልሎች በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት የደረሱ ጉዳቶችን ለማካካስ የጥናት ቡድን ተቋቁመ የጉዳት ዳሰሳ በማድረግ ሃብት ለማሰበሰብ የሚረዳ ዶክሜንት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን እንደየጉዳታቸው መጠን የመደገፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁም መሰረት በአፋር ክልል ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን 400 ኩ/ል ዱቄት፣ 2,896 ሊትር የምግብ ዘይት እና የምግብ ማብሰያና የንፅህና መጠበቅያ ቁሳቁሶችን፣ እንዲሁም በአማራ ክልል ተፈናቅለዉ በደብረብርሃን ከተማ ለተጠለሉ ወገኖቻችን 140 ኩ/ል ዱቄት እና 67 ቦንዳ የተለያዩ አልባሳቶችን በአጠቃላይ 11,024,904 ብር ዋጋ ያላቸዉን ቁሳቁሶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጦርነቱ ለተጎዱ 4 ዞኖች ግምታቸው 3.9 ሚ/ን ብር የሚሆን የቢሮ እቃዎች ለመልሶ ማደረጃ እንዲሆኑ ተሰራጭቷል፡፡

ለአማራ ክልል ግብርና ቢሮና መሬት አስተዳደር አዊ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ወሎ፣ ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞኖች እና ሰሜን ሜጫ ወረዳ ሲሆኑ በመስኖ ስንዴ አፈፃፀም ያስመዘገቡት ዉጤት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና በጦርነቱ ለደረሰው ጉዳት ማቋቋሚያ የሚሆን በአጠቃላይ 31 ተሽከርካሪዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ለኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ እና መሬት አስተዳደር የተጀመረው የልማት ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና በመስኖ ስንዴ አፈፃፀም ላስመዘገቡት ዉጤት 18 ተሽከርካሪዎች፤ ለደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል 10 ተሽከርካሪዎች፤ ለሲዳማ ክልል ግብርና ቢሮ 2 ተሽከርካሪዎች ተሰጥቷል፡፡ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አዲስ የተመሰረተ ክልል 3 ተሽከርካሪዎች፤ ለአፋር ክልል 5 ተሽከርካሪዎች፤

ለሀረሪ ክልል ግብርና ቢሮ 1 ተሽከርካሪ በድምሩ ለ7 ክልሎች 70 ተሽከርካሪዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በአማራና አፋር ክልሎች በጦርነት የተጎዱ ወረዳዎችን በመለየት ለቢሮ መልሶ ማደራጃ የሚሆኑ 165 ኮምፒውተሮችና 20 ፕሪንተሮች ተሰራጭቷል፡፡

በበረሃ አንበጣና በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች ለአፋር፣ ኦሮሚያ፤ ደቡብ፣ ሶማሊ፣ ድሬደዋና አማራ ክልሎች ለምርጥ ዘር ለመኖና ማዳበሪያ ግዝ 720 ሚ/ን ብር ተልኳል፡፡ ከዘህ ውስጥ የአማራ ክልል ብር 233.6 ሚ/ን ብር ለአፋር ክልል ብር 60.6 ሚ/ን ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ለኦሮሚያ፣ ለደቡብና ሶማሊ ክልሎች 25.7 ሚ/ን የሚገመት የመኖ ሳር ተገዝቶ ተሰራጭቷል፡፡ ለአማራ፣ ኦሮሚያና ሶማሊ ክልሎች 5 ሚ/ን ብር የሚገመት የእንስሳት መድሃኒት ተልኳል፡፡ የጉዳት መጠን የዳሰሳ ጥናት ለሁለቱ ክልሎች እንዲሁም የጉዳቱ ማገገሚያ የሚሆን የሚያስፈልገዉን ድጋፍ ምላሽ ለመስጠት በአጭር ጊዜ ዉስጥ የሚከናወኑ ስራዎች ዕቅድ ለአማራ ክልል ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

**የሰርዶ የተቀናጀ የግብርና ልማት ማዕከል** ከተለያዩ ክልሎች የተወጣጡና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ ወጣቶች በአፋር ክልል አሚበራ ወረዳ ከክልሉ በተሰጠው መሬት ላይ የመስኖ መሰረተ-ልማት በማስፋፋት 481 ወጣቶች በልማት ሥራ ተሰማርተው ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም የመስኖ መሰረተ-ልማት ማስፋፋት ባለመቻሉ መንግስት ለወጣቶቹ ማቋቋሚያ በጀት ድጋፍ በማድረግ ወደ ፈለጉበት አካባቢ በመሄድ ሥራ እንዲፈጥሩ በመንግስት ተወስኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በጠቅላላ ለ481 ተጠቃሚዎች እና ለ135 ቤተሰቦቻቸው ለማቋቋሚያና ለትራንስፖርት የተጠየቀና የተፈቀደላቸው ተጨማሪ በጀት ብር 26,780,000 ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በአካል ቀርበው ውል የፈረሙና መረጃቸው ለባንክ ተላልፎ ክፍያ የተፈጸመላቸው ተጠቃሚዎች ብዛት 471 እና የቤተሰቦቻቸው ብዛት 134 ሲሆን የተከፈላቸው የገንዘብ መጠን ብር 26,224,000 ነው፡፡ በአካል ቀርበው ውል ያልፈረሙና ክፍያ ያልተፈጸመላቸው 10 ተጠቃሚዎችና 1 የቤተሰብ አባል የተመደበዉን በጀት ባለመውሰደቸው ምክንያት በጀቱ በግብርና ሚኒስቴር አካውንት ውስጥ በማስቀረት ብር 556,000 ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጓል፡፡

## 23. የዋና ዋና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም

### 23.1. የአደራሽ ግንባታ ፕሮጀክት

የአዳራሽና የህዝብ ቤተመጽሃፍት ግንባታ ሥራ 90 በመቶ ተጠናቋል፡፡

### 23.2. የግብርና እድገት ፕሮግራም

የግብርና እድገት ፕሮግራም በግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚታየዉን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለመቅረፍና ምርታማነትን ለማሳደግ እና ገበያ ተኮር ለማድረግ ታስቦ ከዕድገትና

ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስሮ የተዘጋጀና ይህንንም ግብ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የተቀረፀ መንግስታዊ ፕሮግራም ነዉ፡፡የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ግቦች የግብርና ተቋማትን ማጠናከር፣ በግብርና ምርምር የታገዘ ምርታማነታቸው ከፍተኛ የሆኑ የሰብልና የእንስሳት ዝርያዎችን ማፍለቅ፣ አዳዲስ የአነስተኛ የመስኖ ተቋማትን መገንባትና ባህላዊ የመስኖ ጠቋማትን ማሻሻል፣ የገበያ ማዕከላትን፣ መጋዘኖችንና አነስተኛ ድልድዮችን በመገንባት የግብርና ምርት ግብይትና የእሴት ሰንሰለት መገንባት ሲሆኑ ስራዎቹም የግንባታ ስራዎቻቸው የተጠናቀቁ ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች የግንባታ ስራቸው በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

ፕሮግራሙ በሰባት (8) ክልሎች እና በአንድ የከተማ አስተዳደር (ማለትም፤- በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በትግራይ፣ በሲዳማ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በሀረሪ ክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር) በሚገኙና በተመረጡ 181 ወረዳዎች እና 4,181 ቀበሌዎች ዉስጥ የሚንቀሳቀስ ነዉ፡፡ በፕሮግራሙ ዘመን በድምሩ 3.7 ሚ/ን አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1.6 ሚ/ን የሚሆኑ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮች የፕሮግራሙ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በግብርና እድገት ፕሮግራም በ2014 በጀት ዓመት የፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያዎች የግንባታ ስራቸው ከ85 በመቶ በላይ ደርሷል፡፡ የአነስተኛ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ፕሮጀክቶችና የጥቃቅንና የቤተሰብ የመስኖ አዉታር ግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከታቀዱት ፕሮጅክቶች ውስጥ የ83 አነስተኛ የመስኖ አውታሮች ግንባታ እና የ2,176 ጥቃቅንና የቤተሰብ የመስኖ አዉታሮች የግንባታ ስራዎቻቸው ተጠናቋል፡፡ የግብርና ምርት ግብይትና የእሴት ሰንሰለት ልማት በኩል የዘጠኝ ገበያ ማዕከል ግንባታ ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም ለዩኒየን እና ለመሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት የመጋዝን ግንባታን በተመለከት ከታቀዱት መጋዘኖች ውስጥ የ22 መጋዘኖች ግንባታ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ 10 የአነስተኛ ድልድይ ግንባታ ለማካሄድ ታቅዶ የስድስት አነስተኛ ድልድይ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግንባታ ስራዎቻቸው ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ የተቀሩት በበጀት ዓመቱ ለመስራት ከታቀዱት የግንባታ ፕሮጀክቶች የ6 የአነስተኛ ድልድይ ግንባታዎችን ጨምሮ የግንባታ ስራዎቻቸዉ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

## 23.3. የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት

የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት በአምስት ክልሎች /ሶማሌ፣ አፋር፣ ትግራይ፣ ጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ/፣ በአስራ ስድስት ወረዳዎች እና በአንድ መቶ አስራ ሰባት ቀበሌዎች ላይ 1.2 ሚ/ን ተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ የተቀናጀ የልማት ስራዎችን እየሰራ የሚገኝ ፕሮጀክት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ በ4 ዋና ዋና ኮምፖነንቶች የተከነወኑ ዋና ዋና ሥራዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችና መሰረተ ልማት ኮምፖነንት ከባለፈው ዓመት

ሳይጠናቀቁ ወደ 2014 በጀት ዓመት ከዞሩ 10 ንዑስ ፕሮጀክቶች ውስጥ 8 ተጠናቋል። ይህውም 1 የሰው ጤና ጣቢያ ማስፋፊያ፣ 1 አዲስ የሰው ጤና ኬላ ግንባታ፣ 1 ትምህርት ቤት ማስፋፊያ እና 5 የመጠጥ ዉሃ ንዑስ ፕሮጀክቶ ተጠናቋል። አፈፃፀሙ 80 ከመቶ ነው። ቀሪዎቹ 2 ት/ቤት ማስፋፊያ በአፋር እና በጋምቤላ ክልሎች ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

በዘላቂ የአካባቢ አያያዝ፣ እንክብካቤ ኮምፖነንት 2,673 ሄ/ር ላይ የተለያዩ የስነ-አካላዊና ስነ ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ለማከናወን በታቀደው 3,988.88 ሄ/ር መሬት ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ተሰርቷል። አፈፃፀሙም 150 በመቶ ነው። ባለፈው ዓመት ከተዘጋጁ የተለያዩ የደን ችግኞች ውስጥ 2,850,165 ችግኞችን በ1,025 ሄ/ር መሬት ላይ የመትከል ስራ ተሰርቷል፡፡

ከባለፈው ዓመት ሳይጠናቀቁ የዞሩ 12 አነስተኛ የመስኖ ተቋማትን ለማጠናቀቅ በታቀደው መሰረት 615.8 ሄ/ር ሊያለማ የሚያስችል 8 የመስኖ ተቋማት የተጠናቀቁ ሲሆን ቀሪዎቹ 4ቱ በግንባታ ስራ ላይ ይገኛሉ። በዚሁ መሰረት የቀሪው 4ቱ ተቋማት የግንባታ ደረጃ ከ 5 በመቶ-87 በመቶ ሲሆን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት የአፋር የመስኖ ተቋማት ናቸው። ይህም 3 በአፋር እና 1 በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የሚገኙ ሲሆን በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት 2 መስኖዎች ወደኋላ የቀሩ ሲሆን 2ቱ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። የ8 አዳዲስ አነስተኛ መስኖዎች ግንባታ የቦታ መረጣ እና የዲዛይንና ስፔስፊኬሽን ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በጋምቤላ ክልል የሚገነቡት 4 አነስተኛ የመስኖ ተቋማት ወደ ግንባታ ስራ የገቡ ሲሆን ግንባታቸውም በጥሩ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በተለይ 3ቱ በመጠናቀቅ ሂደት ላይ ይገኛሉ። ቀሪው 4ቱ በሶማሌና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚገነቡ ሲሆኑ የዲዛይን እና የጨረታ ዶክሜንት ተዘጋጅቶ ለአለም ባንክ ለ“No Objection” የተላኩ ቢሆንም በተያዘው በጀት ዓመት ውስጥ መጠናቀቅ ስለማይችሉ ከእቅዱ ተሰርዟል።

14,663 የአማራጭ ኃይል ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ የታቀደ ሲሆን የተጠቃሚዎችና የቴክኖሎጂ ልየታ እንዲሁም የስፔስፊኬሽንና የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ስራዎች ተከናውኗል። በዚህም 12,245 (83.5 በመቶ) (11,773 ማገዶ ቆጣቢ እና 472 ሶላር መብራት) ተገዝቶ ለተጠቃሚ ማህበረሰብ ተሰራጭቷል። በሌላ በኩል 14,663 ተጠቃሚዎች ስልጠና ለመስጠት በታቀደው መሰረት ለ10,890 (9,801 ሴቶች) ተጠቃሚዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

በኑሮ መሰረት ማሻሻል ኮምፖነንት የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓትን ለማጠናከር ባለፈው ዓመት ከተዘጋጅቶ ሳይተከሉ ከቀሩት 692,404 የቡናና የፍራፍሬ ችግኞች በ338 ሄ/ር ማሳ ላይ ተተክሏል። ከዚህ ውስጥ 538,542 የቡና ችግኞች ናቸው። 6,155 አርሶ አደሮችን /1,407 ሴቶች/ ተጠቃሚ ሆነዋል።

በአርሶና በአርብቶ አደሮች ማሳ ላይ ሰርቶ ማሳያ ለመተግበር እንዲያስችል 454 (57 ሴት) አርሶ አደሮች ተመልምለው በሰብልና በእንስሳት የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ላይ ስልጠና ተሰጥቷል።

በተጨማሪም በ412 (75 ሴት) አርሶ አደሮች ማሳ ላይ አኩሪ አተር ክላስተር፣ በአኩር አተር ባዮፌርቲላዘር፣ በቦቆሎ ልማት፣ በሙዝ ልማት፣ በቡና ልማት በበግና ፍየል እርባታ፣ በንብ ማነብ እና በዓሣ ማርባት ላይ ሠርቶ መሳያ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በ12 የአርሶና አርብቶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላት ላይ የሰርቶ ማሳያ ስራ ለመስራት ታቅዶ ተከናውኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ980 አርሶና አርብቶ አደሮች ላይ የማስፋት ስራ እንዲሰራ ታቅዶ በ14,033/ 2,343 ሴቶች/ አርሶአደሮች ተመልምሎ በሰብልና በእንስሳት ቴክኖሎጂዎች ላይ ስልጠና ወስዶ የማስፋቱን ስራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

የመጨረሻው ኮምፖነንት የፕሮጀክት አስተዳደር ክትትልና ግምገማ ሲሆን የፕሮጀክት አስተዳደር የ2014 በጀት ዓመት እቅድን በማዘጋጀት የሚመለከታቸውን ፈፃሚ ክልሎችና ባለድርሻ አካላትን በማስተፍ እቅዱን የማፀደቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ አራት ጊዜ በክልሎች ላይ በመገኘት የድጋፍና የክትትል ስራ ለመስራት የታቀደ ሲሆን በአራቱም ክልሎች /አፋር፣ በጋምቤላ፣ ሶማሌ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ/ በመገኘት አራት ጊዜ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተሰርቷል፡፡ ከአለም ባንክ ጋር በተደረገው 9ኛ የፕሮጀክት የጋራ ምክክር እና ግምገማ ላይ የ2013 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም እና የፕሮጀክቱ የ4 ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት የሁሉም ዋና ኮምፖነንቶች፣ የማህበራዊና አከባቢያዊ ደህንነት እንዲሁም የስርዓተ ፆታ ሪፖርቶች ተገምግሟል፡፡

## 23.4. አካታች እና ቀጣይነት ያለው የእሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት

አካታች እና ቀጣይነት ያለው የእሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት በኦሮሚያ፣ በደቡብ እና ሲዳማ ክልሎች የሚተገበር የሶስት አመት ፕሮግራም ሲሆን፤ ከጣልያን መንግስት በተገኘ 30 ሚ/ን ዩሮ የረዥም ጊዜ ብድር የሚሰራ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ዋና አላማ በኦሮሚያ፣ በደቡብ እና ሲዳማ ክልሎች የሚገኙ ሁለት የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ የተመረጡ የግብርና እሴት ሰንሰለቶችን ማልማት ነው፡፡ ለእሴት ሰንሰለት ልማት የተመረጡት ሰብሎች፤ በኦሮሚያ ክልል የዳቦ እና የማካሮኒ ስንዴ እንዲሁም የፋብሪካ ቲማቲም ሲሆኑ በደቡብ እና ሲዳማ ክልሎች ደግሞ አቮካዶ እና ፓይን አፕል (አናናስ) ናቸው፡፡ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን በተመለከተ በቀጥታ ተጠቃሚ የሆኑ አንድ ሚ/ን በላይ አርሶ አደሮች እና 1.7 ሚ/ን በላይ ደግሞ በኢቀጥተኛ ተጠቃሚነት ይካተታሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር አምራቾች እና የህብረት ስራ ማህበራ ዩኒየኖች ከመሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ጋር፣ የእርሻ ምርምር ተቋማት፣ ትንንሽ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ የአነስተኛ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች፣ ግብዓት አቅራቢዎች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም የጅምላ እና ችርቻሮ ላይ የሚሰሩ የእሴት ሰንሰለቱ ተዋናዮች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

ፕሮጀክቱ በ49 ወረዳዎች ውስጥ በቀጥታ የሚሰራ ሲሆን የአቅም ግንባታ ስራዎች በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል በአምስቱም የፕሮጀክት ዞኖች ለሚገኙ 8 የህብረት ስራ ማህበራት ተከታታይ የሆነ ክትትልና ድጋፍ ለ46 ተሳታፊዎች (7 ሴት) ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም በነዚሁ ዞኖች ለሚገኙ 34

የመጀመሪያ ደረጃ ማህበራት ለሚገኙ 203 ተጠቃሚዎች (41 ሴት) የገንዘብ አያያዝ እና አመራር ጥበብ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። በአርሲ፣ ባሌ (ኢተያ) እንዲሁም ምእራብ አርሲ (ኮፈሌ) ዞን ያሉ የገበሬ ማስልጠኛ ማእከላትን ለማጠናከር ብር1,065,600 ድጋፍ ተደርጓል። በኦሮሚያ ክልል ለሁለት የህብረት ስራ ማህበራት 3,201,728 ብር የውል ስምምነት የዘር ማባዣ ለማሻሻል ድጋፍ ተደርጓል፤ በዚህም መሰረት ለዲደአ የህብረት ስራ ማህበር ብር1,281,728 እና ለኤረር የህብረት ስራ ማህበር ብር1,920,00 ድጋፍ ተደርጓል። ከዚህ ባሻገር በኦሮሚያ ክልል ለስምንት ዩኒየኖች 80,000 ኩ/ል የመያዝ አቅም ያላቸው ስምንት መጋዘኖች የግንባታ ስራ እየተከናወነ ሲሆን አንዱ ተጠናቋል። በመሠረታዊ የህብረት ስራ ማህበራትም ለሰብል ማሰባሰቢያ እና ማቆያ የሚሆኑና 5,000 ኩ/ል የመያዝ አቅም ያላቸው 28 መጋዘኖች እየተገነቡ ሲሆን ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተጠናቋል። የሲዳማ ክልል አዲስ ለተደራጁ ወጣቶች የልምድ ልውውጥ በመልካሳ የግብርና ምርምር ማእከል በአቮካዶ ችግኝ አመራረት ላይ አካሂዷል። በልምድ ልውውጡ ላይ 24 ወጣቶች (3 ሴት) ተሳትፈዋል። የደቡብ ክልል ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ቢሮ የግንዛቤ ማሳደጊያ ወርክሾፕ ከክልል፡ ከዞን እና ከወረዳ ለተውጣጡ የግብርና ባልሙያዎች ተሰጥቷል። በወርክሾፑ ላይ 24 ባለሙያዎች (13 ከሲዳማ እና 11 ከደቡብ) ተሳትፈዋል።

የዘር እና ችግኝ ምርት እና ምርታማነትን ለማሻሻል በደቡብ እና በሲዳማ ክልሎች 15 የዘር እና ችግኝ ማባዣ ማእከላት ተለይቷል: በዚህም መሰረት 8 ማእከላት ከሲዳማ እና 7 ማእከላት ከጌዲኦ ተለይቷል። በጌዲኦ ዞን 5 ትናንሽ እና መካከለኛ የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች ተቋቁሟል። 15 የአቮካዶ እና ፓይን አፕል ችግኝ ማፍያ ጣብያዎች ተለይተው 340,000 የአቮካዶ ችግኝ አምርተዋል። በተጨማሪም 8 ነባር ችግኝ ጣቢያዎቸን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል። የደቡብ ክልል ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ከደቡብ እና ከሲዳማ ግብርና ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በሲዳማ የፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያ መረጣ አካሂዷል። በተጨማሪም በጌዴኦ ዞን 7 አዳዲስ የፍራሬ ችግኝ ጣቢያዎች ተሰርተዋል።

የደቡብ ግብርና ምርምር ተቋም የልምድ ልውውጥ ከተለያዩ ወረዳዎች ለመጡ ገበሬዎች በተሻሻለ የአቮካዶ ችግኝ አመራረት ላይ በጌዲኦ ዞን ተካሂዷል። በዚህም የልምድ ልውውጥ ላይ 45 (16 ወንድ እና 29 ሴት) ገበሬዎች ተሳታፊ ሆነዋል። በሲዳማ እና ደቡብ ክልሎች ለሚገኙ ጀማሪ የህብረት ስራ ዩኒየኖች ቢሮዎችን ጨምሮ የአቮካዶ እና አናናስ ምርት ማሰባሰቢያ ማዕከላት ግንባታዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ በፕሮጀክቱ ድጋፍ ለምርምር ተቋማት (ደ/ዘይት፣ መልካሳ፣ አዳሚቱሉ፣ ሲናና፣ ቁሉምሳ እና ደቡብ ግብርና ምርምር ማዕከል) የቲሹ ካልቸር ላቦራቶሪዎች ግንባታ ስራዎች በመካሄድ ላይ ናቸው።

## 23.5. የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች መስኖ ልማት ፕሮጀክት

ፕሮጀክቱ ከተጀመረ (2012 በጀት ዓመት) ጀምሮ እስካሁን 4,927.37 ሄ/ር ማልማት የሚችሉና 12,801 አ/አደር ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ 74 የአነስተኛ መስኖ አውታር ግንባታ በማጠቃለል

ለተጠቃሚ እንዲተላለፉ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በ2014 በጀት ዓመት 1,883.40 ሄ/ር የማልማት አቅም ያላቸውና 4,602 አ/አደር ተጠቃሚ የሚያደርጉ 25 አውታሮች ወደ ልማት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 1,250 ሄ/ር የማልማት ዓቅም ያላቸውና 4,150 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ 22 ፕሮጀክቶች ውል በመያዝ ቅድመ ክፍያ ተከፍሏል፡፡

**ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ የውሃ አማራጮችን በመለየት** ከ2012 እስከ 2014 ዓ.ም 9,935.72 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 147 በላይ የአነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ጥናት ለክልሎች ድጋፍ ተደርጎ ተጠንቷል፡፡ በተጨማሪም በአማካሪ ድርጅቶች የበጀት ድጋፍ በማድረግ 780.11 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ የ8 ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ስራ በፕሮጀክቱ ድጋፍ ተጠናቋል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት አዲስ ለሚጠኑ በአማካሪ ድርጅቶች 10 ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ለደቡብ ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ውል ተገብቶ ስራ ተጀምሯል፡፡ በክልሎች ከተጠኑት ፕሮጀክቶች የ65 ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን የሰነድ ግምገማ ተደርጎ ተጠናቋል፡፡ ይህም በሄ/ር ደረጃ 4,997.07 ሄ/ር ማልማት ይችላል፡፡ በተጨማሪም 35 ፕሮጀክቶች በክልልና በፌዴራል ባለሙያዎችና ትብብር ለማስጠናት በጀት ተልኮ የጥናትና ዲዛይን ስራ በማስጀመር ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ቴክኖሎጂዎችን ከማቅረብ አኳያ 3,700.23 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 400 የመስኖ ፓምፖችን በ2012 በጀት ዓመት ግዥ በማከናወን ለክልሎች የተከፋፈለ ሲሆን በ2013 በጀት ዓመት 120 በፀሐይ ኃይል የሚሰራ 99.6 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ የሶላር ፓምፖች ግዥ በማከናወን ለአራት ክልሎች በማከፋፈል ተከላ ተካሂዷል፡፡ እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት 130 ሶላር ፓምፖችን ግዥ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ሲሆን የሶላር ግዥው ባለመሳካቱ በነዳጅ የሚሰሩ 7,720 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 1,930 በናፍጣ የሚሰሩ የውሃ ማሳቢያ ፓምፖች ግዥ ተከናውኗል፡፡ የአቅም ማጎልበት ስልጠናዎችን በክልሎች ያለውን ክፍተት ዳሰሳ በማድረግ በተመረጡ የስልጠና ዓይነቶች ማለትም በኮንትራት አስተዳደር፣ በወንዝ ጠለፋ ጥናትና ዲዛይን፣ በሞተር ፓምፕ ጥናትና ዲዛይን፣ በተመረጡ የምህንድስና አጋዥ ሶፍትዌሮች ማለትም በAutoCAD Civil3D፣ በHydrological Analysis Models ላይ በድምሩ ለ114 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## 23.6. የተሳትፎአዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም

የተሳትፎአዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ዋና ዓላማው የመስኖ አውታሮችን በመገንባት 18,400 ሄ/ር በመስኖ እርሻ በማልማት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብት መራቆትን በመቀነስ፣ የግብዓትና ግብይት ስርዓት እንዲሻሻል በማድረግ አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸውን 108,750 አባ/እማ ወራዎችን በምግብ እና በስርዓተ-ምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የገቢ አቅማቸው እንዲጎለብት የማድረግ ዓላማዎች ላይ በትኩረት ይሠራል፡፡ ይህንን ዓለማ ለማሳካት በሦስት ንዑሳን ፕሮግራሞች ማለትም የአነስተኛ መስኖ መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት፤ አቅም ግንባታ ለዘላቂ ግብርና

ኢንቨስትመንት እና የፕሮግራም ማኔጅመንት፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ዕውቀት ማኔጅሜንት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ከዚህም አንፃር የአነስተኛ መስኖ መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት ንዑስ ፕሮግራም ውስጥ የመስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን በበጀት ዓመቱ 8 የጠብታ/የርጭትና የቤተሰብ ኩሬ የጥናትና ዲዛይን ለማከናወን ታቅዶ 8ቱም የጥናትና ዲዛይን ስራዎች ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ የማህበረሰብ መስኖ አውታሮች ግንባታ ፕሮግራሙ ከጀመረበት ከየካቲት 2009 ዓ.ም ጀምሮ 17,085 ሄ/ር በማልማት 39,966 (7,579 ሴት) ተጠቃሚ የሚያደርግ 116 የመስኖ ተቋማት ግንባታቸው አፈፃፀም በአማካይ 87.03 በመቶ ላይ ይገኛል፡፡ ከ116 የመስኖ ተቋማት መካከል 12,138 ሄ/ር የሚያለሙና 22,517 አርሶአደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 79 የመስኖ አውታሮች ግንባታው ተጠናቆ 73ቱ ወደ ልማት ገብቷል፡፡ 16ቱ በአዲሱ በጀት አመት ወደ ግብርና ልማት በሙሉ አቅማቸው ይገባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከቀሪው ከ37ቱ የመስኖ ተቋማት 14ቱ በጸጥታው ችግር ምክንያት ወደ ግንባታ መግባት ያልቻሉ ሲሆን የ23ቱ ደግሞ የግንባታቸው አፈፃፀም በአማካይ 50 በመቶ ላይ ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአማራጭ የውሃ ምንጭ ግንባታ 871 በፕሮጀክቱ ቆይታ ጊዜ የአማራጭ ዉሃ ለመስራት ታቅዶ በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን የ4 የማህበረሰብ ኩሬ 5.26 ሄ/ር እና 15 አባላትን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም 30 ሄ/ር በማልማት 60 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 12 የሶላር ፓምፖች ተጠናቀው ወደ ልማት ለማስገባት ተችሏል፡፡ የግብርና ግብይትና ገበያ ትስስር ሥራዎች 28 የመስኖ ግብዓት ገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራት ለማቋቋም ታቅዶ 23 (82 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ በሌላ በኩል 24 የመስኖ ግብዓት የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራት ለማጠናከር ታቅዶ 24ቱም ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

የመስኖ ሰብል ከማልማት አንፃር በ61 የመስኖ ተቋም የበጋ መስኖ ልማት ለማልማት ታቅዶ በ48 የመስኖ ተቋም 4,664 ሄ/ር በመጀመሪያ ዙር እና በ2ኛ ዙር መስኖ 1,721 ሄ/ር ለምቷል፡፡ በተሳትፎዓዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ስነ-አካላዊ የአፈርና ዉሃ ጥበቃን ለማጠናከር የተለያዩ ችግኞችን ለማዘጋጀት 38 ችግኝ ጣቢያዎችን ለማጠናከር ታቅዶ 46 (121 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ በእነዚህ ችግኝ ጣቢያዎች ብዙ ጠቀሜታ ያላቸዉ ችግኞችን ለማፍላት 9,465 ኪ.ግ ዘር እና 3,350 ኪግ ፖሊተን ቲዩብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በእነዚህ ችግኝ ጣቢያዎች ዉስጥ ከ12,607,639 በላይ ችግኝ በማፍላት ለተከላ ዝግጁ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ተፋሰስን በስነ-ህይወታዊ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ዘዴዎች ከማልማት አንፃር 5,098.67 ሄ/ር ላይ ታቅዶ 3,965.15 ሄ/ር (76 በመቶ) ላይ የተከናወነ ሲሆን በጠቅላዉ 15,928,724 የሚሆኑ የተለያዩ ጠቀሜታ ባላቸዉ ችግኞች በስነ ህይወታዊ ዘዴ እንድሸፈን በማድረግ 158,187 (ሴት 37,277) ሰዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አግሮ ፎረስትሪ እና ፍራፍሬ ልማት በሁሉም የፕሮግራሙ ክልሎች ዉስጥ በሚገኙ ተፋሰሶች ላይ ያሉ አርሶአደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ 428 ሄ/ር ታቅዶ 531 ሄ/ር (100$^{+}$

በመቶ) ተከናዉኗል፡፡ በዚህም 2,248 አነስተኛ አርሶአደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ የተቀናጀ አፈር ለምነት ስራዎችን በተመለከተ በተለያዩ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዘዴዎችን በመጠቀም 371 ሄ/ር መሬት ላይ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 347 ሄ/ር መሬት ማከናወን ተችሏል፡፡

## 23.7. ዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮግራም

ዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮግራም ውጤታማ ስኬታማ የተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅና አጠቃቀም ልምዶችንና ሥርዓትን ለማስፋፋት እንድሁም በአፈፃፀም ሂደት ላይ መሠረታዊ ተግዳሮቶችን በመለየትና በመተንተን በብር 6.7 ቢ/ን በጀት በ4 ዋና ዋና ንዑስ ፕሮግራሞች (Components) የተጠቃለሉ ተግባራትን አቅዶ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ የፕሮግራሙ ዋና ዋና አፈፃፀም በየንዑስ ፕሮግራሙ (ስትራቴጂክ የኢንቨስትመንት ማዕቀፍ) እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን በተመለከተ በዘላቂ የመሬት አያያዝ ዘዴዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተራቆቱ መሬቶች ምርታማነትን ከመመለስ (Restoration) አንፃር 163,548 ሄ/ር መሬት ለማልማት አቅዶ 176,541 ሄ/ር (108 በመቶ) እንድለማ ተድርጓል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተስማሚ ግብርና ተግባራትን በተመለከተ የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም ግብርና ከማስፋፋት ጋር በተያዘ በእቅባ እርሻ በተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያና በአግሮ ፎረስትሪ ስራዎችን በአርሶ አደር ማሳ በማከናወን ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል 40,728 ሄ/ር ታቅዶ 35,360 ሄ/ር (87 በመቶ) የእርሻ መሬት ላይ ተተግብሯል፡፡

የገቢ ማስገኛ በሆኑ የእሴት ሰንሰለቶች ሥራዎች 70,918 የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን ለማሳተፍ ታቅዶ 40,124 (20,597 ሴት) (57 በመቶ) ተከናዉኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 802,627 ማሳዎች የሁለተኛ ደረጃ ሠርተፊኬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 490,231 (61 በመቶ) ማሣዎች ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መሬት ሠርተፊኬት ለ200,657 አባወራዎችና እማወራዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ157,648 (113,403 ሴት) (78.56 በመቶ) ቤተሰቦች ተሰጥቷል፡፡

## 23.8. የእንስሳት እና የአሳ ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት

ፕሮጀክቱ የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግና የእንስሳትና ዓሣ አምራቾችንና ፕሮሰሰሮችን ለመደገፍ የተቋቋመ ሲሆን 1.2 ሚ/ን የእንስሳትና ዓሣ አምራቾችና ፕሮሰሰሮች በ58 ወረዳዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ፕሮጀክቱ በዋነኝነት እየሠራ ያለው በአራቱ የእንስሳት ሰንሰለቶች ማለትም በወተት ልማት፣ በዶሮ እርባታ፣ በቀይ ስጋ እና በዓሣ ላይ ምርትና ምርታማነትን እና ወደ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ማሻሻል ላይ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በፕሮጀክቱ 10,560 የጋራ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች (150,280 ተጠቃሚ

አባላት ያሉት) ተደራጅተው ማምረትና ወደ ገበያ ማቅረብ ጀምረዋል፡፡ ከነዚህ የተደራጁት ማህበራት (CIG) 3 ቢ/ን ያልተጣራ ገቢ አግኝቷል፡፡ ፕሮጀክቱ በተጨማሪ የተመጣጠነ ምግብን ከማሻሻል አንፃር ጥሩ ውጤት እያመጣ ነው፡፡ በተለይም የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎቹ ከሚያመርቱት የእንስሳት ተዋፅኦ ምግብ አመጋገብ ላይ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡ ይኸውም በጋራ ፍላጐት የተደራጁት ማህበራት አባላት 11 ሚ/ን ሊትር ወተት፣ 12 ሚ/ን እንቁላል፣ 29,783 በግና ፍየል ወይም ቀይ ስጋ እና 110 ሺህ ኪ.ግ ዓሣ ለምግብ ጥቅምነት አውሏል፡፡

በሁሉም ክልሎች ለሚገኙ የጋራ ፍላጎት ለተደራጁ ግለሰቦች የገበያ ትስስር ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የገበያ ችግር ባይጋጥምም በቀጣይ ሲያጋጥም እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ግንዛቤ ተሰጥቷል፡፡ በደረጃ ሁለት ለተደራጁ 120 ማህበራት ሰነድ ዝግጅት እና በአፅዳቂ ኮሚቴ ማፅደቅ ስራዎች ተጠናቆ 110 ማህበራት ወደ ግዥ ስራ ውስጥ ገብተዋል፡፡

በእያንዳንዳቸው ማለትም በኦሮሚያ 23፤ በአማራ 15፤ በደቡብ 11፣ በሲዳማ 2፣ በቤንሻጉል 2፤ በጋምቤላ 1፤ በአጠቃላይ 54 የወረዳ አፅዳቂ ኮሚቴ በደረጃ ሁለት ለማቋቋም ታቅዶ 54ቱም እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ በደረጃ ሦስት 19 ዩኒየኖችን ለማደራጀት እና ለመደገፍ ታቅዶ 9 በኦሮሚያ ክልል 5 በአማራ ክልል፣ እንዲሁም 3 በደቡብ ክልል አጠቃላይ ሂደቱ ተጠናቆ ወደ ግዢ ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡

ከውጭ ለሚገቡ ጊደሮች እና ወይፈኖች የሚሆን በሆለታ የማቆያ ቤቶች በመገንባት ላይ ሲሆን ግንባታው ባለመጠናቀቁ ምክንያት እስከ አሁን ጊደሮችን ማስገባት አልተቻለም፡፡ አሁን ግንባታው የደረሰበት 71 በመቶ ነው፡፡ በአዳአ በርጋ ምርምር ማዕከል 200፣ በወላይታ ሶዶ 100 እንዲሁም በወልቂጤ 100 በድምሩ 400 የሃገር ውስጥ ዝርያዎችን እንዲገዙ ተደርጓል፡፡ ለተገዙት 400 የሀገር ውስጥ ዝርያዎች መኖ ተገዝቷል፡፡

የቻግኒ ወተት የዳልጋ ከብት ዝርያ ማሻሻያ አስመልክቶ አሁን ከፍተኛ መሻሻል እያደረገ ያለ እና ፕሮጀክቱም አስፈላጊውን ድጋፍ ካደረጋቸው መካከል፤ ለዝርያ ማሻሻያው ፕሮግራም የሚውሉ፡ የእንስሳት መረጣ፤ የመኖ ልማት ስራ እና የእንስሳት በረት ጥገና ስራ ተከናውኗል፡፡

የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል 77,770 ዶዝ የማዳሪያ ሆርሞንና 16 Sexed Semen ተገዝቶ የገባና በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ለአርሶ አደርና የመንግሥት የእርባታ ማዕከላት ተሠራጭቷል፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰብን መሠረት ያደረገ የበጐች ዝርያ ማሻሻል ሥራ ተሰርቷል፡፡ ስለዚህ 72,000 የበግ ኮርማዎች በተለያዩ የፕሮጀክቱ ክልሎች ተሠራጭቷል፡፡

የእንስሳት መለያ ዘዴ (Ear Tag) ለማድረግ ለ200,000 ለሚሆኑ በግና ፍየሎች ተከናውኗል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሥራው ይረዳ ዘንድ 10 ዴስክቶፕና 10 ላፕቶፖች መረጃ መሰብሰቢያና መመዝገቢያ ተከፋፍሏል፡፡

የዳልጋ ከብት ዝርያ ማሻሻያ አስመልክቶ የብሔራዊ እንስሳት ዝርያ ማሻሻያ እና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በወልቂጤ ምርምር ማዕከል እንዲሁም የብሔራዊ እንስሳት ዝርያ ማሻሻያ እና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በወላይታ ሶዶ ጀርሲ ከብቶች ዝርያ ብዜት ማዕከል ውስጥ ለማካሄድ የመግባቢያ ስምምነት መሰረት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ደስታ መሰል በሽታን ለመከላከል 8.6 ሚ/ን ክትባት የተደረገ እና መድን ጥናት ክትትል የተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች የዓሣ ኩሬዎች የተዘጋጁና የዓሣ ጫጩቶች ለእርባታ ማባዣ ግብዓት ቀርቧል፡፡ በዚህም መሠረት በኩሬ ዓሣ ማርባት ሥራ ላይ ከተደራጁት የጋራ ፍላጐት ያላቸው ማህበራት ወደ 755,753 ኪ.ግ. ዓሣ ሲገኝ ከዚህ ውስጥ 96,289 አባላት ለምግብነት ተጠቅመዋል፡፡ የቀረው 679,402 ኪ.ግ. የሚሆን ዓሣ ለአካባቢው ገበያ ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም ፕሮጀክቱ በእንስሳት መኖ ማልማት ጥሩ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡ ይህም ባለፈው ዓመት 310 ሄ/ር የጋራ የግጦሽ መሬት በ11 የፕሮጀክቱ ወረዳዎቹ መልሶ የማቋቋም ሥራ ተሠርቷል፡፡

## 23.9. የክፍለ አህጉራዊ የድርቅ መቋቋሚያና የአርብቶ አደር ኑሮ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት

ክፍለ አህጉራዊ የአርብቶ አደር ኑሮ መቋቋሚያ ፕሮጀክት ዓላማዉ ድርቅንና ድንገተኛ አደጋን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መከላከልን መሰረት በማድረግ በአካባቢዉ ያለዉን እምቅ ሀብት /የተፈጥሮና የእንስሳት ሀብት/ ላይ ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ዘላቂና አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እንዲሁም የ132,000 የአርብቶ/ከፊል አርብቶ አደር እማ/አባወራዎች ኑሮ በማሻሻል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡

በፕሮጀክቱ 146 የውሃ ተቋማት መገንባትና መልሶ ማልማት፣ 8,000 ሄ/ር የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት መልሶ ማልማት፣ 4 የመኖ ባንክ መቋቋም፣ 24 የእንስሳት ገበያ ማዕከላት መገንባትና የመረጃ ስርዓት መዘርጋት፣ 5 አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ማስተዋወቅ፣ 333 የማህበረሰብ የእንስሳት ጤና ሰራተኞች ማቋቋም፣ 512 የማህበረሰብ አርቢ ቡድኖች ማቋቋም፣ 131 ማህበራት በአማራጭ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ማደራጀት እና በ43 ወረዳዎች የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ማጠናከር ታቅዶ149 የውሃ ተቋማት መገንባትና መልሶ ማልማት፣ 10,436.9 ሄ/ር የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት መልሶ ማልማት፣ 9 የመኖ ባንክ መቋቋም፣ 24 የእንስሳት ገበያ ማዕከላት መገንባትና የመረጃ ስርዓት መዘርጋት፣ 6 አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ማስተዋወቅ፣ 182 የማህበረሰብ የእንስሳት ጤና ሰራተኞች ማቋቋም፣ ከ7 ሚ/ን በላይ እንስሳት ክትባት መስጠት፣ 178 የማህበረሰብ አርቢ ቡድኖች ማቋቋም፣ 130 ማህበራት በአማራጭ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ማደራጀት እና በ53 ወረዳዎች የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ማጠናከር ስራዎች በማከናወን 775,024 አርብቶ አደሮች (44.6 በመቶ ሴቶች) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## 23.10. በኢጣሊያን ልማት ትብብር /AICS/ የሚደገፍ ድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶአደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት

የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ከኢጣሊያን ልማት ትብብር በተገኘ 12 ሚ/ን ዩሮ የብድር ስምምነት በ4 የአፋር ክልል አርብቶአደር ወረዳዎች ማለትም ጭፍራ፣ ተላላክ፣ ደዌ እና አሚባራ ወረዳዎች የሚተገበር የአንድ አመት ተኩል ፕሮጀክት ነው፡፡

የፕሮጀክቱ ዓላማ በአፋር ክልል 4 ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙትን አርብቶና ከፊል አርብቶአደር የማህበረሰብ ክፍሎች ድርቅ መቋቋሚያ አቅም በመገንባት ኑሮአቸው እንዲሻሻል ማድረግ እና የምግብ ዋስትና እንዲያረጋግጡ ማስቻል ነው፡፡ በዚህ ፕሮጀክት 29,0000 አርብቶአደሮች፣ ከፊል አርብቶአደሮች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ታቅዷል፡፡

በዚሁ መሰረት ብዙዎቹ ስራዎች በጅምር ላይ ቢሆኑም 11 ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ተሰርቷል፣ 2 የማህበረሰብ ውሃ ኩሬ ግንባታ (30,000 ሜ/ኩብ) ስራ በዳዌ እና ጭፍራ ወረዳዎች ተጠናቋል፡፡ 190 ሄ/ር የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት መልሶ በማልማት፣ 2 የችግኝ ጣቢያዎች (በጭፍራ እና በተላላክ ወረዳዎች) ፣ 2 የመኖ ማከማቻ መጋዘን በአሚባራ እና ጭፍራ ወረዳዎች ተገንብቷል፡፡ አንድ አዲስ የእንስሳት ገበያ ማዕከል በዳዌ ወረዳ፣ አንድ መልሶ ማልማት ስራ በጭፍራ ወረዳ፣ እንዲሁም 8 የእንስሳት ጤና ኬላዎች እና 2 የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች መልሶ ማልማት እና ቁሳቁስ ማሟላት ስራዎች በማከናወን አርብቶአደሩን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## 23.11. የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም 1

የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ኢትዮጵያ ፕሮጀክት 1 ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ 30 ሚ/ን UA ወይም 43.3 ሚ/ን ዶላር የብድር ስምምነት በ15 የአርብቶ አደር ወረዳዎች (በአንድ ወረዳ 5 ቀበሌዎች) ማለትም በአፋር ክልል 6 ወረዳዎች እና በሶማሌ ክልል 9 ወረዳዎች እየተተገበረ ያለ የ5 ዓመት ፕሮጀክት ሲሆን አንዳአንድ ስራዎች በተለይም የውሀ ሀብት ልማት ስራዎች ባለመጠናቀቃቸው እስከ 2014 በጀት ዓመት ዓ.ም. እንዲራዘም ተወስኖ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ፕሮጀክት ነው፡፡

በሱማሌ ክልል ቁፋሯቸው የተጠናቀቀ የሶስት ውሀ ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ ለማከናወን ታቅዶ ሶስት የውሀ ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ እየተከናወነ ሲሆን፣ አንዱ የውሀ መስመር ዝርጋታ 90 በመቶ እንዲሁም ሁለቱ የውሀ መስመር ዝርጋታ እያንዳንዳቸው 40 በመቶ የግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ ዘመን መጨረሻ ድረስ ከታቀዱት 8 የውሀ ጉድጓድ የመስመር ዝርጋታ ውስጥ የ5ቱ የውሀ ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡

በሱማሌ እና በአፋር ክልል 21 የገጸ ምድር የውሀ ተቋማት ግንባታ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን፣ በሱማሌ ክልል የ3 ኩሬ ግንባታ እና በአፋር ክልል የአንድ ቢርካ ግንባታ ተጠናቋል፡፡

በፕሮጀክት ዘመን በአጠቃላይ እስከ 2014 በጀት መጨረሻ ድረስ አዳዲስ በተገነቡት እና ጥገና በተደረገላቸው የውሀ ተቋማት 160,200 (50 በመቶ ሴት) የአርብቶአደር ማህበረሰብ እና 865,860 እንስሳት የውሀ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በአፋር ክልል 70 ሄ/ር መሬት ላይ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ዘር ልማት ለማካሄድ እንዲቻል 13.5 ኩ/ል የመኖ ዘር ወደ ቦታው የማጓጓዝ ስራ የተከናወነ ሲሆን፣ ዘሩን ለመዝራት የመሬት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡ የመጋቢ መንገድ ግንባታን በተመለከተ በፕሮጀክት ዘመን በአጠቃላይ 67.6 ኪ.ሜ መጋቢ መንገድ ግንባታ የተጠናቀቀ ሲሆን ከ50,538 በላይ (49 በመቶ ሴቶች) አርብቶአደር ማህበረሰብ የመንገድ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## 23.12. የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም 2

የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ኢትዮጵያ ፕሮጀክት 2 ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ 28.48 ሚ/ን UA ወይም 43.57 ሚ/ን ዶላር የብድር ስምምነት በኦሮሚያ ስምንት እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ህዝቦች ክልሎች ሰባት በድምሩ በአስራ አምስት የአርብቶ አደር ወረዳዎች የሚተገበር የአምስት ዓመት ፕሮጀክት ነው፡፡ ለሰው እና ለእንስሳት አገልግሎት የሚውል የውሀ ሀብት ልማት ስራዎች ተከናውኗል፣ እስከ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ አዳዲስ በተገነቡት እና ጥገና በተደረገላቸው የውሀ ተቋማት 333,642 (50 በመቶ ሴት) የማህበረሰብ ክፍሎች እና 1,308,936 እንስሳት ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ የተለያዩ የተፈጥሮ ግጦሽ ልማት ስራዎች በመከናወናቸው እስከ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ 69,886 አባወራ (49 በመቶ ሴት) እና 982,545 እንስሳት የመኖ አቅርቦት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በአንዳአንድ አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ ለተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች በፕሮጀክቱ የተሰሩ የውሀ ተቋማት ከፕሮጀክት ወረዳ ውጪ ለሆኑም አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡ በተጠናቀቀው የመጋቢ መንገድ ግንባታ 44,526 (47 በመቶ ሴት) የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጠናቀቁት የገበያ ማዕከላት 451,645 አባወራ/ እማወራ (27 በመቶ ሴት) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ተዘዋዋሪ ብድር የወሰዱ በኦሮሚያ ክልል 80 እና በደቡብ ክልል 98 በድምሩ 178 ማህበራት ብድሩን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸው ክትትል የተደረገ ሲሆን በፕሮጀክት ዘመን እስከ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በኦሮሚያ ክልል 1,182 (60 በመቶ ሴት) አባላት ብር 6,727,979 ብድራቸውን መልሰዋል፡፡ 1,430 (58 በመቶ ሴት) አባላት ብር 976,833 ቆጥበዋል፡፡ እንዲሁም 1,035 (65 በመቶ ሴት) የህ/ስ/ማ አባላት በተሰማሩበት ዘርፍ 8,059,011 ብር ትርፍ አግኝተዋል፡፡ በደቡብ ክልል 699 (75 በመቶ ሴት) አባላት ብር 3,040,443 ብድራቸውን መልሰዋል፡፡ 1,444 (74 በመቶ ሴት) አባላት

ብር 170,222 ቆጥበዋል፡፡ እንዲሁም 1,444 የህ/ስ/ማ በተሰማሩበት ዘርፍ ብር 3,229,696 ትርፍ አግኝተዋል፡፡

## 23.13. የድርቅ መቋቋሚያና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም

ክፍለ ሀጉራዊ የድርቅ መቋቋሚያና ማጠናከርያ ፈንድ ፕሮጀክት ከKFW ድርጅት የገንዘብ እርዳታና በኢትዮጵያ መንግስት በሚደረግ የገንዘብ አስተዋጽኦ የሚከናወን ሲሆን፣ ጠቅላላ ወጪውም 16 ሚ/ን EURO ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ዝርዝር ዓላማዎች የአርብቶአደርና ከፊል አርብቶአደር አካባቢዎችን የአመራረት ሥርዓት ማጠናከር፣ በኢትዮጵያና ጂቡቲ መካከል በሚገኙ አዋሳኝ አካባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦችን ገቢ ማሳደግና በርካታ አማራጭ የኑሮ ዘዴዎችን እንዲከተሉ ማድረግ ናቸው፡፡የፕሮጀክቱ ዋና ዋና የስራ ዘርፎችም የውሃ ሀብት ልማትና የገጠር መሰረተ ልማቶች፣ የግጦሽ መሬትና የመኖ ልማት ማሻሻያ ሥራዎች እና አማራጭ የኑሮ ዘዴዎችና መሰረታዊ አገልግሎቶች የስራ ዘርፎች ናቸው፡፡

የአፈር እና ጥበቃ ስራ ዋናውና አንደኛው ማህበረሰቡ የሚኖርበትን የተጎዳ ስነ-ምህዳር እንዲያጋግም እና እንዲያሻሽል እንዲያደርግ አንደኛው ነው፡፡ በአጠቃላይ ኤሊዳር ወረዳ ሲየሮ እና አዲጊኖ ቀበሌ 25 ሄ/ር ላይ የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ስራ የተሰራ ሲሆን በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ በ270 ሄ/ር ላይ የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ማከናወን ተችሏል፡፡

አፋንቦ ወረዳ 50 ሄ/ር የመኖ ቦታ በመምረጥ እና መኖ አምራች ቡድን በማደራጀት እና በማሰልጠን 40 ሄ/ር ምንጣሮ ተጠናቆ 30 ሄ/ር ማሳ ተዘጋጅቷል፡፡ 2 ኩ/ል አልፋ አልፋ ዘር፤ 10 ኪ.ግ ሮደስ ዘር፤ 3 ኩ/ል ፓኒከም የሳር ዘር ቀርቧል፡፡ 450 ሜትር የሚረዝም የመስኖ ቦይ ቁፋሮ ስራ ተሰርቷል፡፡ በፕሮጀክቱ ወረዳዎች 12 የቁጠባ ማህበራት 532 (ወንድ 207 እና ሴት 345) አባላት ያሉት የተቋቋሙ ሲሆን፤ አባለቱም በአጠቃላይ ብር 434,520 መቆጠብ ችሏል፡፡

## 23.14. የኢትዮጵያ እንስሳት ጤና ለገጠር ልማት ፕሮጀክት

የኢትዮጵያ እንስሳት ጤና ለገጠር ልማት የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት በኢትዮጵያ እንስሳት ጤና ለገጠር ልማት ፕሮግራም ስር ከሚገኙ 5 ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ሁሉንም ፕሮጀክቶች የማስተባበር እና የመምራት ኃላፊነትም አለው፡፡

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ እየጨመረ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የግልና የመንግሥት የእንስሳት ጤና አገልግሎት አቅርቦት ጥራትና ብቃት በማሻሻል የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እና የእንስሳት ግብይትን ለማሻሻል ነው፡፡ ይህንንም ዓላማ ለማሳካት የተቀመጡለት ዋና ዋና ግቦች/ ኮምፖኔንቶች ምቹ አከባቢ ሁኔታዎችን በመፍጠር የግልና የመንግሥት የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና አቅርቦት ማሻሻል፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎት አቅራቢዎችን የቴክኒክ ብቃት እና ተጠቃሚነትን በማሳደግ የአገልግሎቱን አቅርቦትና ፍትሀዊነት ማሻሻል እና

የእንስሳት እና የእንስሳት ውጤቶችን ጥሬ ምርት ደህንነት እና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ቁጥጥርን ማሻሻል ናቸው፡፡

በበጀት ዓመቱ 1 ስጋትን መሠረት ያደረገ ባዕድ/በአገር ውስጥ የሌሉ የእንስሳት በሽታዎች ቅኝት ለማከናወን በታቀደው መሠረት የበሽታ ቅኝቱ በወፎች ኢንፍሉዌንዛ /HPAI እና በምስራቅ ዳርቻ ትኩሳት/ECF በሽታዎች ላይ በኬንያ እና ደቡብ ሱዳን አዋሳኝ ቦታዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 100 በመቶ ነው፡፡ በዚህ ሥጋትን መሠረት ያደረገ የእንስሳት በሽታ መከላከያ ክትባት በአፋር ክልል በ5 ወረዳዎች በማካሄድ በሽታዎች የሚያደርሱትን ጉዳት ለመከላከል በታቀደው መሰረት ሥጋትን መሠረት ያደረገ ለፍየሎችና ለበጎች የፒፒአር በሽታ መከላከያ ክትባት በ4 ወረዳዎች የተሰጠ ሲሆን እስከአሁን 8 ወረዳዎች ክትባቱ በመሰጠቱ አፈጻጸሙ 66.67 በመቶ ሆኗል፡፡

በከተማ ማዘጋጃ ቤት እና በኤክስፖርት ቄራ የሥጋ ምርመራ አገልግሎት የሚሠጡ ባለሙያዎችን ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ በቄራዎቹ የሚቀርበው ሥጋና ተረፈ ሥጋ ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንስሳት ጤናና ግብርና ፋካልቲ ጋር በተደረገ ስምምነት በበጀት ዓመቱ ለ60 ለሥጋ መርማሪዎች ደረጃውን የጠበቀ የሥጋ ምርመራ ሥልጠና ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሠረት ለ59 ሥጋ መርማሪዎች ሥልጠናው የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም 99 በመቶ ሆኗል፡፡

## 24. ያጋጠሙ ተግዳሮቶች የተወሰዱ እርምጃዎችና በቀጣይ ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮች

### ተግዳሮቶች

- ✓ ሀገራዊ የጸጥታ ችግር፣
- ✓ የውጪ ምንዛሬ እጥረት፤
- ✓ የዓለም አቀፍ የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ መናር፣
- ✓ የፕሮጀክት የግንባታ ግብዓቶች ዋጋ መናር፣
- ✓ ለግብዓት መግዣ፣ ለሀገር ውስጥ ወጪዎች፣ ለምርጥ ዘር፣ ለትራንስፖርት እና ለግብርና ኖራ መግዣ የብድር እጥረት፣
- ✓ የተሻሻሉ የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት (ምርጥ ዘር… ፋይናንስ ብድር) በተሟላ ሁኔታ ለባለሀብቶች የሚቀርብበት አሰራር አለመኖር፣
- ✓ የክልሎችና የፌዴራል ተቋማዊ አደረጃጀት አለማናበብ፣
- ✓ የተዘጋጁ የግብይትና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች በአጭር ጊዜ ጸድቀው ተግባራዊ አለመደረጋቸው ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

## ለተግዳሮቶች የተሰወሰዱ ዕርምጃዎችና የመፍትሄ ሀሳቦች

- ✓ አንጻራዊ ሰላም ያለበቸውን አከባቢዎችን በጥናት በመለየት የማካካሻ ዕቅድ ተዘጋጅቶ የመንግስትና የባለድርሻ አካላትን፣ እንዲሁም አመራሩና ፈጻሚው ርብርብ አድርጎ ድጋፍ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡
- ✓ የማዳበሪያ የዋጋ ንረትን አርሶአደሩ መቋቋም እንዲችል የፌዴራል መንግስት 15 ቢ/ን ብር ድጎማ አድርጓል፡፡
- ✓ የፕሮጀክቶች ዋጋ መናርን ለማሻሻልም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የግንባታ ግብዓቶች በተለይም ሲሚንቶ በተደራጁ ማህበራት በቀጥታ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርብ ጥረት ተደርጓል፡፡
- ✓ በእንስሳትና በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነትን ለሚያስችለው አሰራር ወደ ተግባር እንዲገባ እየተሰራ ነው፡፡
- ✓ የአደረጃጀት ማነቆን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመወያየት ለመፍታት እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ✓ የህግ ማዕቀፎች በመለየት እንዲጸድቁ በህዝብ ተወካዮች የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ፣ የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት እና ከፍትህ ሚ/ር ጋር በቅርበት እየተሰራ ይገኛል፡፡

## የበላይ ውሳኔ ሰጭ አካላት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ✓ ከክልሎች ጋር የተናበበ፣ በበጀትና ሎጀስቲክስ የተደራጀ ጠንካራ የዕጽዋት ተባይና በሽታ መከላከል አደረጃጀት፣ እንዲሁም የአነስተኛ መስኖ ልማትን ውጤታማ ለማድረግ አደረጃጀት የማስተካከልና ሎጂስቲክስ የመሟላት ሥራዎች በትኩረት መስራት፤
- ✓ የአሲዳማ አፈርን ለማከም እንዲቻል የሚያስፈልገው ውህድ ኖራ በመንግስትና በግል ድርጅቶች የማምረት፣ የማጓጓዝ፣ ለአርሶ አደሩ በካሽና በብድር የሚሰራጭበት አሠራር ላይ በልዩ ትኩረት መስራት፣
- ✓ የማዳበሪያ አጠቃቀማችንን በአፈር ምርመራ ውጤት ላይ የተመረኮዘ ለማድረግ ከግብርና ምርምር ጋር የተጀመረውን የተቀናጀ የማዳበሪያ ማረጋገጫ ምርምር፣ እንዲሁም የራሳችን የማዳበሪያ ማምረቻ ፋብሪካዎች እንዲኖር በትኩረት መስራት፣
- ✓ የእርሻ፣ የሆርቲካልቸር፣ ሜከናይዜሽን፣ የመስኖ ልማት እና የእንስሳት ኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ ለክልል ግብርና ቢሮዎች ቴክኒካልና አስተዳደራዊ ድጋፍ በመስጠት የስራ ግንኙነቱ እንዲጠናከር ማድረግ፣

- ✓ ከክልል እስከ ፌዴራል ድረስ ዘመናዊነትን የተከተለ፣ የተናበበ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የግኑኙነት አግባብ እና የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት ላይ በትኩረት መስራት የሚሉ **ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች** ናቸው፡፡

## 25. ማጠቃለያ

በሀገራችን የተወሰኑ አካባቢዎች የተከሰተው የፀጥታ ችግር በእርሻና ሆርቲካልቸር፣እንዲሁም በእንስሳት ሀብት ልማት ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመከላከል በየደረጃው የሚገኘው ባለሙያ፣ እንዲሁም አርሶ/አርብቶ አደሩ የግብርና ሥራውን ከወትሮ በላቀ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፣ በፀጥታ ችግር ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የምርት ጉድለት ለመቅረፍ አንፃራዊ ሰላም ባላቸው አካባቢዎች የምርት ጉድለቱን ማካካስ በሚያስችል አግባብ በመኸርና በልግ፣ እንዲሁም በመስኖ የሚለሙ የሰብል ምርቶች ያለብክነት በተደራጀ መንገድ እንዲሰባሰብ፣ ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ ለመተካት በበጋ የመስኖ ስንዴና አትክልትና ፍራፍሬ ልማት በልዩ ትኩረት የማከናወን፣ ለአርሶ አደሩ ዋጋው በዓለም አቀፍ ደረጃ በእጅጉ የናረዉን የአፈር ማዳበሪያ ላይ መንግስት ድጎማ በማድረግ፣ እንዲሁም በሰብል ምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትሉ ተባዮችን የመከላከል ስራ በተደራጀ ሁኔታ የተከናወነ ሲሆን፣ አማካይ አፈፃፀሙም **የፊዚካል ሥራዎች 90.39 በመቶ - በጣም ከፍተኛ** እና የሚ/ር መ/ቤቱንና የተጠሪ ተቋማት ዓመታዊ የበጀት **በጣም ከፍተኛ አፈጻጸም ደረጀ** ላይ መሆኑን ተገምግሟል፡፡

በቀጣይ ለ2014/15 የምርት ዘመን ከወዲሁ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ በመኸር እና በአትክልትና ፍራፍሬ ሥራዎች፣ እንዲሁም የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ አመራሩና ፈጻሚው፣ እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው ከፍተኛ ርብርብ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የተፈጥሮ ሃብት መመናመንና መራቆትን፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ በአቅም ውስንነት ምክንያት የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን፤ በሁሉም ገጠር አከባቢዎች ጎልቶ የሚታዩ የሥራ አጥነት ችግሮችን፣ እንዲሁም ሌሎችም የተያያዙ ተግዳሮቶችን በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላትን በማሳታፍ ደረጃ በደረጃ በመቀነስ፣ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የህዝብ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንፃር የተጀመረው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ረገድ የተገልጋዮችን ተሳትፎና እርካታን የማሳደግ ሥራዎች ላይ ያተኮረ፤ አዲስ መሬትን ለመስኖ ልማት ዝግጁ ማድረግ፣ መስኖ ተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎች ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## 26. ቁልፍ የውጤት አመልካቾች ዝርዝር አፈፃፀም

### አባሪ አንድ: - የግብርና ቁልፍ የውጤት አመልካቾች

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| I | እርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ | | | | | |
| 1.1 | ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ | | | | | |
| 1.1.1 | የአነስተኛ ይዞታ አዝዕርት ልማት (2013/14 ምርት ዘመን) | | | | | |
| | የታረሰ መሬት ስፋት | ሺ.ህ ሄ/ር | 12,980.00 | 13,230.00 | 13,137.00 | 99.30 |
| | በዘር የተሸፈነ መሬት ስፋት | ሺ.ህ ሄ/ር | 12,980.00 | 13,230.00 | 12,980.00 | 98.11 |
| | በትራክተር የታረሰ መሬት ስፋት | ሺ.ህ ሄ/ር | 2,535.00 | 2,550.00 | 2,040.00 | 80.00 |
| | በክላስተር የተዘራ መሬት ስፋት | ሺ.ህ ሄ/ር | 1,000.00 | 5,560.00 | 4,740.00 | 85.25 |
| | የምርጥ ዘር ብዜት | ሺ.ህ ሄ/ር | 69.14 | 97.84 | 79.92 | 81.68 |
| | በዘር ብዜት ከተሸፈነው መሬት ላይ የተሰበሰበ ምርጥ ዘር | ሚ/ን ኩንታል | 1.33 | 1.90 | 1.09 | 57.37 |
| | በዋና ዋና ሰብሎች የተሰበሰበ ምርት | ሚ/ን ኩንታል | 341.83 | 374.00 | 336.60 | 90.00 |
| | በመስኖ የለማ ስንዴ | ሺ.ህ ሄ/ር | 300.00 | 400.00 | 450.17 | 100+ |
| | በመስኖ የተሰበሰበ የስንዴ ምርት | ሚ/ን ኩንታል | | 16.00 | 15.90 | 99.38 |
| | በበልግ እርሻ የለማ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 1,836.34 | 2,204.00 | 2,381.00 | 100+ |
| | በበልግ እርሻ በዘር የተሸፈነ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 1,836.34 | 2,204.00 | 1,910.00 | 86.66 |
| | አትክልት፣ፍራፍሬና ስራስር ምርት በመስኖ | ሚ/ን ኩ/ል | 178.25 | 196.00 | 176.20 | 89.90 |
| 1.1.2 | የሆርቲካልቸር ሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ (2013/14 ምርት ዘመን መኸር) | | | | | |
| | የተሰበሰበ የአትክልት ምርት | ሺ.ህ ቶን | 10,718.00 | 1,178.98 | 1,118.08 | 94.83 |
| | አማካይ የአትክልት ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 53.00 | 85.00 | 81.60 | 96.00 |
| | የተሰበሰበ የፍራፍሬ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 14,192.00 | 1,561.16 | 1,419.24 | 90.91 |
| | አማካይ የፍራፍሬ ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 70.00 | 90.00 | 87.89 | 97.66 |
| | የተሰበሰበ የስራስር ምርት | ሺ.ህ ቶን | 51,606.00 | 5,573.54 | 5,114.41 | 91.76 |
| | አማካይ የስራስር ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 129.00 | 212.00 | 208.53 | 98.36 |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አትክልት በበልግ | ሺ.ህ ቶን | 864.00 | 933.20 | 739.56 | 79.25 |
| | ስራስር በበልግ | ሺ.ህ ቶን | 3,800.00 | 4,104.00 | 4,111.60 | 100⁺ |
| 1.1.3 | የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ማጠናከር | | | | | |
| | **የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች** | በሺ. ቁጥር | 10,287.00 | 11,982.00 | 19,237.00 | 100⁺ |
| | **አርሶ አደር** | በሺ. ቁጥር | 9,336.00 | 10,185.00 | 16,407.00 | 100⁺ |
| | አባወራ | በሺ. ቁጥር | 6,752.00 | 7,333.00 | 9,091.00 | 100⁺ |
| | እማወራ | በሺ. ቁጥር | 1,658.00 | 1,833.00 | 1,455.00 | 79.38 |
| | ባለትዳር ሴቶች | በሺ. ቁጥር | 926.00 | 3,666.00 | 4,828.00 | 100⁺ |
| | ወጣቶች | በሺ. ቁጥር | 3,121.00 | 1,018.00 | 1,975.00 | 100⁺ |
| | **አርብቶ አደር** | በሺ. ቁጥር | 976.00 | 1,043.00 | 990.00 | 94.92 |
| | አባወራ | በሺ. ቁጥር | 715.00 | 776.00 | 574.00 | 73.97 |
| | እማወራ | በሺ. ቁጥር | 169.00 | 194.00 | 115.00 | 59.28 |
| | ባለትዳር ሴቶች | በሺ. ቁጥር | 91.00 | 388.00 | 210.00 | 54.12 |
| | ወጣቶች | በሺ. ቁጥር | 353.00 | 108.00 | 91.00 | 84.26 |
| | **ከፊል አርብቶ አደር** | በሺ. ቁጥር | 3,185.00 | 696.00 | 898.00 | 100⁺ |
| | አባወራ | በሺ. ቁጥር | 2,042.00 | 519.00 | 496.00 | 95.57 |
| | እማወራ | በሺ. ቁጥር | 699.00 | 130.00 | 96.00 | 73.85 |
| | ባለትዳር ሴቶች | በሺ. ቁጥር | 246.00 | 259.00 | 247.00 | 95.37 |
| | ወጣቶች | በሺ. ቁጥር | 198.00 | 72.00 | 59.00 | 81.94 |
| | የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚዎች | በሺ. ቁጥር | 6,741.00 | 7,804.00 | 8,281.00 | 100⁺ |
| | የሞዴል አርሶ/አርብቶ/ አደሮች ቁጥር ብዛት | በሺ. ቁጥር | 3,751.00 | 4,114.00 | 4,765.00 | 100⁺ |
| 1.1.4 | የቡና ልማት | | | | | |
| | **በአነስተኛ አርሶ አደር እና በባለሀብት** | | | | | |
| | ምርት | ሚ/ን ኩንታል | 6.73 | 12.35 | 6.52 | 52.79 |
| | ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 7.00 | 7.15 | 7.50 | 100⁺ |
| | **በአልሚ ባለሀብቶች እና በአውት ግሮወርስ** | | | | | |
| | ምርት | ሺ.ህ ቶን | 92.00 | 11.95 | 10.34 | 86.49 |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 26.00 | 31.80 | 27.33 | 85.94 |
| 1.1.5 | የቅመማቅመም ልማት | | | | | |
| | ምርት | ሺ.ህ ቶን | 595.00 | 744.80 | 715.00 | 96.00 |
| | ምርታማነት | ኩ/ል/ሄ/ር | 15.00 | 16.00 | 15.80 | 98.75 |
| II | እንስሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ | | | | | |
| 2.1 | ገበያ ተኮር የእንስሳትና አሳ ምርትና ምርታማነት | | | | | |
| 2.1.1 | **አጠቃላይ የወተት ምርት** | **ሚ/ን ሊትር** | **7,225.00** | **7,443.00** | **7,080.35** | **95.13** |
| | የላም ወተት | ሚ/ን ሊትር | 4,692.00 | 5,923.00 | 5,751.00 | 97.10 |
| | የፍየል ወተት | ሚ/ን ሊትር | 99.00 | 192.00 | 225.39 | 100+ |
| | የግመል ወተት | ሚ/ን ሊትር | 2,434.00 | 1,328.00 | 1,103.96 | 83.13 |
| 2.1.2 | **አጠቃላይ የስጋ ምርት** | **ሺ.ህ ቶን** | **348.80** | **431.52** | **447.77** | **100+** |
| | የበሬ ስጋ | ሺ.ህ ቶን | 214.00 | 261.00 | 283.85 | 100+ |
| | የበግ ስጋ | ሺ.ህ ቶን | 76.00 | 91.00 | 84.40 | 92.75 |
| | የፍየል ስጋ | ሺ.ህ ቶን | 57.00 | 78.00 | 78.00 | 100.00 |
| | የግመል ስጋ | ሺ.ህ ቶን | 1.80 | 1.52 | 1.52 | 100.00 |
| 2.1.3 | **ቆዳና ሌጦ** | **በሚ/ን ቁጥር** | **15.15** | **18.38** | **18.33** | **99.73** |
| | የዳልጋ ከብት ቆዳ | ሚ/ን ቁጥር | 1.82 | 1.99 | 2.46 | 100+ |
| | የበግ ሌጦ | ሚ/ን ቁጥር | 7.23 | 8.68 | 8.96 | 100+ |
| | የፍየል ሌጦ | ሚ/ን ቁጥር | 6.10 | 7.71 | 6.91 | 89.62 |
| 2.1.4 | **አጠቃላይ የዶሮ ስጋ ምርት** | **ሺ.ህ ቶን** | **70.00** | **78.00** | **90.55** | **100+** |
| | የዶሮ ምርት (ስጋ) - ስፔሻላይዝድ | ሺ.ህ ቶን | 42.00 | 48.00 | 54.84 | 100+ |
| | የዶሮ ምርት (ስጋ) - የተሻሻለ የቤተሰብ | ሺ.ህ ቶን | 21.00 | 10.00 | 17.71 | 100+ |
| | የዶሮ ምርት (ስጋ) - ባህላዊ የቤተሰብ | ሺ.ህ ቶን | 7.00 | 20.00 | 18.01 | 90.03 |
| 2.1.5 | **አጠቃላይ የእንቁላል ምርት** | **በሚሊዮን ቁጥር** | **2,771.13** | **3,254.70** | **3,246.54** | **99.75** |
| | የዶሮ ምርት (እንቁላል)- ስፔሻላይዝድ | በሚሊዮን ቁጥር | 1,662.68 | 2,926.30 | 2,770.00 | 94.66 |
| | የዶሮ ምርት (እንቁላል)-የተሻሻለ የቤተሰብ | በሚሊዮን ቁጥር | 831.34 | 224.80 | 266.80 | 100+ |
| | የዶሮ ምርት (እንቁላል)-ባህላዊ የቤተሰብ | በሚሊዮን ቁጥር | 277.11 | 103.60 | 209.74 | 100+ |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.6 | **የጫጩት ምርት** | **በሚልዮን ቁጥር** | **26.20** | **27.00** | **27.93** | **100+** |
| 2.1.7 | **የአሳ ምርት** | **ሺ.ህ ቶን** | **60.50** | **78.95** | **73.14** | **92.64** |
| | የአሳ ምርት ከመደበኛ የውሃ አካላት | ሺ.ህ ቶን | 60.00 | 78.00 | 72.40 | 92.82 |
| | ከአኳካልቸር | ሺ.ህ ቶን | 0.50 | 0.95 | 0.74 | 77.89 |
| | የደረቀ አሳ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 0.30 | 3.50 | 3.10 | 88.57 |
| | በጨው የታጀለ የአሳ ምርት | ሺ.ህ ቶን | 0.60 | 0.60 | 0.50 | 83.33 |
| | የሚያስፈልግ የአሳ ጫጩት መጠን | ሚ/ን ቁጥር | 0.90 | 1.15 | 1.08 | 93.83 |
| | አሳ የተጨመረባቸው የኩሬ ብዛት | ቁጥር | 1,671.00 | 1,800.00 | 1,520.00 | 84.44 |
| 2.1.8 | **የማር፣ የሰምና የሐር ምርት** | | **129.00** | **138.00** | **146.70** | **100+** |
| | የማር ምርት | ሺ.ህ ቶን | 129.00 | 138.00 | 146.70 | 100+ |
| | የሰም ምርት | ሺ.ህ ቶን | 6.00 | 9.00 | 11.50 | 100+ |
| | የሐር ኮኮን ምርት | ቶን | 32.60 | 40.00 | 36.69 | 91.73 |
| | **የወተት ምርታማነት** | | | | | |
| | የወተት ላም ምርታማነት (Indigenous) | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 1.45 | 1.55 | 2.22 | 100+ |
| | የወተት ላም ምርታማነት (Crossbreed) | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 6.00 | 6.74 | 6.78 | 100+ |
| | የወተት ላም ምርታማነት (Exotic) | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 13.07 | 13.76 | 13.29 | 96.58 |
| | የፍየል ወተት ምርታማነት | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 0.50 | 0.52 | 0.50 | 97.09 |
| | የግመል ወተት ምርታማነት | ሊ.ት/እንስሳ/ቀን | 2.90 | 3.32 | 3.00 | 90.36 |
| | **የስጋ ምርታማነት** | | | | | |
| | የበሬ ስጋ ምርታማነት | ኪ.ሎ/እንስሳ | 111.04 | 112.10 | 112.12 | 100+ |
| | የበግ ስጋ ምርታማነት | ኪ.ሎ/እንስሳ | 10.64 | 10.80 | 10.60 | 98.15 |
| | የፍየል ስጋ ምርታማነት | ኪ.ሎ/እንስሳ | 8.60 | 8.70 | 8.75 | 100+ |
| | የግመል ስጋ ምርታማነት | ኪ.ሎ/እንስሳ | 250.34 | 255.40 | 255.50 | 100+ |
| | **የማር ምርታማነት** | | | | | |
| | የባህላዊ ቀፎ | (ኪ.ሎ/ቀፎ/ስብሰባ) | 5.54 | 8.00 | 8.50 | 100+ |
| | የሽግግር ቀፎ | (ኪ.ሎ/ቀፎ/ስብሰባ) | 8.15 | 18.00 | 18.20 | 100+ |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የፍሬም ቀፎ | (ኪ.ሎ/ቀፎ/ስብሰባ) | 10.74 | 24.00 | 26.00 | 100+ |
| | የሰም ምርታማነት | (ኪ.ሎ/ቀፎ/ስብሰባ) | 0.54 | 0.60 | 0.85 | 100+ |
| | **የዶሮ ስጋ ምርታማነት** | | | | | |
| | የዶሮ ምርታማነት (ስጋ) - ስፔሻላይዝድ | ኪ.ሎ/ዶሮ | 1.80 | 2.10 | 1.90 | 90.48 |
| | የዶሮ ምርታማነት (ስጋ) - የተሻሻለ የቤተሰብ | ኪ.ሎ/ዶሮ | 1.40 | 1.60 | 1.50 | 93.75 |
| | የዶሮ ምርታማነት (ስጋ) - ባህላዊ የቤተሰብ | ኪ.ሎ/ዶሮ | 1.20 | 1.40 | 1.30 | 92.86 |
| | **የዶሮ እንቁላል ምርታማነት** | | | | | |
| | የዶሮ ምርታማነት (እንቁላል)-የተሻሻለ የቤተሰብ | እንቁላል/ዶሮ/ዓመት | 185.00 | 192.00 | 175.00 | 91.15 |
| | የዶሮ ምርታማነት (እንቁላል)- ስፔሻላይዝድ | እንቁላል/ዶሮ/ዓመት | 244.00 | 260.00 | 250.00 | 96.15 |
| | የዶሮ ምርታማነት (እንቁላል)-ባህላዊ የቤተሰብ | እንቁላል/ዶሮ/ዓመት | 66.00 | 75.00 | 70.00 | 93.33 |
| | **የዓሳ ምርታማነት** | | | | | |
| | የአሳ ምርታማነት | ኪ.ግ/መ.ኩ | 0.90 | 1.00 | 1.00 | 100.00 |
| | **ዝርያ ማሻሻያ** | | | | | |
| 2.1.9 | **አጠቃላይ የተመረተ የአባለዘር** | **በሺህ ዶዝ** | **1,096,150.00** | **1,400.00** | **1,333.23** | **95.23** |
| | በኢንስቲትዩት የተመረተ አባለዘር | በሺህ ዶዝ | 884,125.00 | 1,060.36 | 1,060.36 | 100.00 |
| | በክልሎች የተመረተ አባለዘር | በሺህ ዶዝ | 212,025.00 | 414.24 | 272.88 | 65.87 |
| 2.1.10 | **አጠቃላይ የተሠራጨ የአባለዘር** | **በሺህ ዶዝ** | **786,488.00** | **1,314.24** | **786.00** | **59.81** |
| | በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨ የአባለዘር | በሺህ ዶዝ | 717,670.00 | 900.00 | 717.67 | 79.74 |
| | በክልሎች የተሠራጨ የአባለዘር | በሺህ ዶዝ | 68,818.00 | 414.24 | 68.82 | 16.61 |
| 2.1.11 | **አጠቃላይ የተመረተ ፈሳሽ ናይትሮጂን** | **በሺህ ሊትር** | **317,011.00** | **385.00** | **337.85** | **87.75** |
| | በኢንስቲትዩት የተመረተ ፈሳሽ ናይትሮጂን መጠን | በሺህ ሊትር | 57,692.00 | 65.00 | 57.31 | 88.16 |
| | በክልሎች የተመረተ ፈሳሽ ናይትሮጂን መጠን | በሺህ ሊትር | 259,319.00 | 298.00 | 280.55 | 94.14 |
| 2.1.12 | **የተሠራጨ ፈሳሽ ናይትሮጂን** | **በሺህ ሊትር** | **244,819.50** | **346.00** | **311.44** | **90.01** |
| | በኢንስቲትዩት የተሠራጨ ፈሳሽ ናይትሮጂን መጠን | በሺህ ሊትር | 42,892.50 | 58.00 | 47.77 | 82.36 |
| | በክልሎች የተሠራጨ ፈሳሽ ናይትሮጂን መጠን | በሺህ ሊትር | 201,927.00 | 288.00 | 263.67 | 91.55 |
| | ተመርጠው የተሰራጩ አውራ በጎችና ፍየሎች | በሺህ ቁጥር | 6,884.00 | 27.55 | 21.10 | 76.59 |
| 2.1.13 | **የእንስሳት ጤና አገልግሎት** | | | | | |
| | የክትባት አገልግሎት ሽፋን | መቶኛ | 89.00 | 90.00 | 91.00 | 100+ |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተሰራጨ የድንበር ዘለል በሽታዎች ክትባት | ሚሊ. ዶዝ | 120.00 | 140.00 | 129.30 | 92.36 |
| | የድንበር ዘለል ክትባት የተከተቡ እንስሳት ብዛት | ሚ/ን ቁጥር | 113.00 | 80.00 | 153.60 | 100+ |
| | ድንበር ዘለል ላልሆኑ በሽታዎች የመከላከያ ክትባት የተሰጣቸው እንስሳት ብዛት | ሚ/ን ቁጥር | 8.00 | 45.00 | 54.70 | 100+ |
| | ለበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ (PPR) ቁጥጥር የተከተቡ በጎችና ፍየሎች | ሚ/ን ቁጥር | 7.60 | 10.00 | 10.50 | 100+ |
| | የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል የተሸፈነ መሬት | ካ.ኪ.ሜ | 84,100.60 | 119,851.00 | 96,780.94 | 80.75 |
| | በገንዲ በሽታ ለታመሙ እንስሳት ህክምና መስጠት | በሺ.ህ ቁጥር | 16,726.00 | 31.58 | 35.64 | 100+ |
| | ሀገራዊ የእንስሳት በሽታ ወረርሽኝ ቅኝትና ሪፖርት የመላክ ምጣኔ | መቶኛ | 78.10 | 100.00 | 85.00 | 85.00 |
| | በተንቀሳቃሽ ስልክ የተመሠረት ዕለታዊ የሪፖርት ምጣኔ | መቶኛ | 24.00 | 50.00 | 40.00 | 80.00 |
| | የመመርመር አቅምን በማሳደግ ምላሽ የተሰጣቸው የእንስሳት በሽታ ፍንዳታዎች ክስተት ብዛት | ቁጥር | 132.00 | 145.00 | 136.00 | 93.79 |
| 2.1.14 | **የመኖ ልማት** | | | | | |
| | ከሁሉም የመኖ ምንጮች የተመረተ ጠቅላላ ድርቆ መኖ ምርት | ሚ/ን ቶን | 133.30 | 146.63 | 142.89 | 97.45 |
| | የተፈጥሮ ግጦሽን (Rangeland) የማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች፣ ግብዓቶችና አሰራሮች በመጠቀም የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት፣ | ሚ/ን ቶን | 40.30 | 44.60 | 37.10 | 83.18 |
| | የተሻሻሉ የመኖ ዓይነቶችን በማስፋፋት የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት፣ | ሚ/ን ቶን | 9.68 | 11.00 | 10.60 | 96.36 |
| | የሰብል ተረፈ ምርትን አሰባሰብ፣ አከመቻቸትና አጠቃቀም ማሻሻያ አሰራሮችን በመተግበር የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት መጠን፣ | ሚ/ን ቶን | 58.60 | 64.50 | 63.30 | 98.14 |
| | የኢንዳስትሪ (ስኳርና ሌሎች) ተረፈ ምርቶችን በማስፋፋት የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት፣ | ሚ/ን ቶን | 6.00 | 7.00 | 7.40 | 100+ |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የወል ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመጠቀምና በማልማት የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት፣ | ሚ/ን ቶን | 17.60 | 18.40 | 17.60 | 95.65 |
| | የግል የአርሶ አደር ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመጠቀምና በማልማት የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት መጠን፣ | ሚ/ን ቶን | 1.08 | 1.14 | 4.28 | 100+ |
| | የመኖ ዘር ምርታማነትን ለማሳደግና ጥራት ያለዉ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮች ማምረት | ሺህ ቶን | 2.80 | 3.00 | 3.60 | 100+ |
| | በሁሉም ስነ ምህዳር በመስኖ የመኖ ማልማት ትግበራ ላይ የስልጠናና የመስክ ላይ ድጋፍ በማድረግ ምርት ማሳደግ፣ | ሄ/ር | 19,515.00 | 21,466.00 | 15,370.00 | 71.60 |
| III | **ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም** | | | | | |
| | ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበራት የተቋቋመላቸው ተፋሰሶች | ቁጥር | 500.00 | 1,000.00 | 1,528.00 | 100+ |
| | የልማት ዕቅድ የተዘጋጀላቸው ተፋሰሶች ብዛት | ቁጥር | 1,000.00 | 1,800.00 | 1,689.00 | 93.83 |
| | ከንክኪ ነጻ የተደረጉና ተከልለው እንዲያገግሙ የተደረጉ ተፋሰሶች ስፋት | በሺ. ሄ/ር | 215.00 | 400.00 | 529.78 | 100+ |
| | በሥነ-አካላዊ የአውጥ ሥራዎች የተሸፈኑ ተፋሰሶች ስፋት | በሺ. ሄ/ር | 1,800.00 | 2,500.00 | 2,503.32 | 100+ |
| | ጥገና፣ ዕድሳት እና ደረጃ ማሳደግ የተካሄደባቸው ተፋሰሶች ስፋት | በሺ. ሄ/ር | 1,200.00 | 1,500.00 | 290.72 | 19.38 |
| | በልየ ልዩ ተከላዎች የተሸፈነ መሬት ስፋት | በሺ. ሄ/ር | 204.00 | 2,200.00 | 2,076.00 | 94.36 |
| | የተሰራጨ ዘርፈ-ብዙ ጥቅም የሚሠጥ የዛፍ ዘር | በኩ/ል | 6,477.24 | 6,500.00 | 7,374.00 | 100+ |
| | የተተከለ የዕፅዋት ችግኞች ብዛት (ቀርከሀ፣ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው እፅዋት፣ ፍራፍሬ፣ የእንስሳት መኖ እና የውበት ዛፍ) | ቢ/ን ቁጥር | 6.00 | 7.00 | 7.49 | 100+ |
| | የመሬት አስተዳደር መረጃ ሥርዓት የተዘረጋላቸው ወረዳዎች | ቁጥር | 114.00 | 105.00 | 93.00 | 88.57 |
| | የተለካ ማሳ ብዛት | ቁጥር (በሚሊዮን) | 1.36 | 2.60 | 2.90 | 100+ |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **የሁለተኛ ደረጃ የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ተጠቃሚዎች (አባወራ/እማወራ)** | **ቁጥር (በሚሊዮን)** | **0.21** | **0.74** | **0.66** | **88.83** |
| | አባወራ | ቁጥር (በሚሊዮን) | 0.15 | 0.52 | 0.46 | 88.46 |
| | እማወራ | ቁጥር (በሚሊዮን) | 0.06 | 0.22 | 0.20 | 89.69 |
| | የተሰራጨ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት ብዛት (በማሳ) | ቁጥር (በሚሊዮን) | 0.74 | 2.60 | 2.30 | 88.46 |
| | የተዘጋጀ የተቀናጀ የቀበሌ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ብዛት | ቁጥር | 383.00 | 400.00 | 247.00 | 61.75 |
| | የተተገበረ የተቀናጀ የቀበሌ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ብዛት | ቁጥር | 232.00 | 220.00 | 280.00 | $100^{+}$ |
| | የኮትቻ አፈርን በማንጣፈፍ እንዲለማ ማድረግ | ሺ.ህ ሄ/ር | 624.52 | 650.00 | 637.42 | 98.06 |
| | በኮምፖስት የለማ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 3,858.75 | 4,500.00 | 6,767.00 | $100^{+}$ |
| | በቨርሚ ኮምፖስት የለማ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 6.00 | 8.00 | 7.40 | 92.50 |
| | በህየወ ማዳበሪያ የለማ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 95.00 | 150.00 | 147.00 | 98.00 |
| | በባዮ ስለሪ የለማ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 128.40 | 33.32 | 31.48 | 94.48 |
| | በጥብቅ እርሻ የለማ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 8.90 | 12.50 | 11.75 | 94.00 |
| | ለመስኖ ልማት ዝግጁ የሆነ የመሬት ስፋት | ሺ.ህ ሄ/ር | 56.54 | 27.10 | 40.04 | $100^{+}$ |
| | የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር | በሺህ ቁጥር | 129.00 | 298.30 | 119.60 | 40.09 |
| | በማህበረሰብ የሚተዳደሩ አዳዲስ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ብዛት | ቁጥር | 134.00 | 197.00 | 218.00 | $100^{+}$ |
| | ህጋዊ ሰውነት ያገኙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር | ቁጥር | 62.00 | 197.00 | 167.00 | 84.77 |
| 3.1 | **ደን ልማት** | | | | | |
| | የተካሄደ የቀርከሃ መሬት መለየት | ሚ/ን ሄ/ር | 0.015 | 0.02 | 0.06 | $100^{+}$ |
| | ከደን ሮያሊት እና ከተወረሰ ደን ሀብት እና የሀገሪቱ የደን ህግን ከተላለፉ አካላት ቅጣት የተገኘ ገቢ | ሚ/ን ብር | 257.96 | 200.00 | 293.00 | $100^{+}$ |
| | ወደ ውጭ ከተላከ የደን ምርት ውጤት የተገኘ የውጭ ምንዛሬ | ሚ/ን የአሜሪካ ዶላር | 12.03 | 20.00 | 2.38 | 11.90 |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ግብርና ልማት ውጤታማነት ለማሻሻል የቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት | ሚ/ን ሜትሪክ ቶን $Co_{2e}$ | 2.8 | 5.00 | 10.00 | 100+ |
| | ያደገ ሀገራዊ የደንና የጥበቃ ቦታዎች ሽፋን | በመቶኛ | 17.20 | 18.50 | 17.00 | 91.89 |
| | የተሻሻለ የተፈጥሮ እና የሰው ሰራሽ ነባር ደን አጠባበቅ | ሚ/ን ሄ/ር | 19.20 | 19.20 | 19.20 | 100.00 |
| | የተዘጋጀ ሀገራዊ የደን ማኔጅመንት ፕላን | ሚ/ን ሄ/ር | 0.20 | 0.20 | 0.97 | 100+ |
| 3.2 | **ብዝሀ ሕይወት** | | | | | |
| | **የብዝሀ ህይወትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀት ለመለየት የተካሄደ ጥናት** | **የተካሄደ ጥናት** | **22.00** | **31.00** | **43.00** | **100+** |
| | **የብዝሀ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀት** | | | | | |
| | በዘቦታ የተነበረ ዝርያ | የተነበረ ዝርያ | 76.00 | 78.00 | 76.00 | 97.44 |
| | በዘቦታ የተነበረ ናሙና | የተነበረ ናሙና | 80.00 | 82.00 | 86.00 | 100+ |
| | በኢዘቦታ የተነበረ ዝርያ | የተነበረ ዝርያ | 236.00 | 239.00 | 250.00 | 100+ |
| | በኢዘቦታ የተነበረ ናሙና | የተነበረ ናሙና | 1,126.00 | 1,070.00 | 1,178.00 | 100+ |
| | የብዝህ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በዘላቂታዊነት አጠቃቀሙን ለማሳደግ የተሰራጨ ዝርያዎች | የተሰራጨ ዝርያዎች በቁጥር | 50.00 | 50.00 | 74.00 | 100+ |
| | የብዝህ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በዘላቂታዊነት አጠቃቀሙን ለማሳደግ የተወሰዱ የዝርያ ናሙናዎች | የተወሰዱ የዝርያ ናሙናዎች በቁጥር | 12,093.00 | 10,200.00 | 23,019.00 | 100+ |
| IV | **የግብርና ኢንቨስትመንት ግብዓት አቅርቦትና ምርት ግብይት** | | | | | |
| 4.1 | **የእርሻ ኢንቨስትመንት አፈፃፀም** | | | | | |
| | **2013/14 ምርት ዘመን በባለሀብቶች እርሻ** | | | | | |
| | የለማ መሬት | ሺ.ህ ሄ/ር | 970.43 | 2,287.00 | 884.80 | 38.69 |
| | የተገኘ ምርት | ሺ.ህ ኩንታል | 19,150.00 | 27,600.00 | 19,398.00 | 70.28 |
| 4.2 | **የእንስሳት ኢንቨስትመንት አፈፃፀም** | | | | | |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በተሰጠ ኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰረት እየለሙ ያሉ የእንስሳት እርባታ ማዕከላት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ማድረግና ማጠናከር | የማዕከላት ብዛት | 1,237.00 | 1,622.00 | 1,148.00 | 70.78 |
| | የግል ባለሀብቱን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ/ለገበያ የቀረበ ምርት/ | | | | | |
| | የእርድ ፍየል | ቁጥር | 39,800.00 | 66,732.00 | 28,454.00 | 42.64 |
| | የዕርድ በግ | ›› | 19,916.00 | 25,206.00 | 11,835.00 | 46.95 |
| | የዕርድ ዳልጋ ከብት | ›› | 20,131.00 | 24,143.00 | 29,017.00 | 100+ |
| | የስጋ ዶሮ | ›› | 100,227.00 | 129,682.00 | 215,906.00 | 100+ |
| | እንቁላል | ሚ/ቁ | 5.70 | 6.72 | 28.85 | 100+ |
| | ወተት | ሚ/ሊት | 4,070.00 | 4.70 | 16.70 | 100+ |
| | ማር | ቶን | 62.80 | 88.00 | 67.70 | 76.93 |
| | የመኖ ምርት /በቆሎ፣ አኩሪ አተር፣ ሲናር/ | ሺ/ኩ/ል | 38.25 | 48.00 | 77.60 | 100+ |
| 4.3 | **የሰብል ግብዓት አቅርቦት** | | | | | |
| | **የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት** | | | | | |
| | ለ2014 የቀረበ የአፈር ማዳበሪያ | ሚሊየን ኩ/ል | 14.50 | 12.90 | 11.77 | 91.24 |
| | የቀረበ ዘር | በሺህ ኩ/ል | 1,200.00 | 1,310.33 | 922.14 | 70.37 |
| 4.4 | **የግብርና ምርት ግብይት** | | | | | |
| | **የተመረተ የቡና፣ ሻይና ቅ/ቅመም ምርት (ድምር)** | **ቶን** | **263,006.36** | **314,291.00** | **312,196.20** | **99.33** |
| | ቡና | ቶን | 248,311.65 | 298,340.00 | 302,762.00 | 100+ |
| | ሻይ | ቶን | 1,814.46 | 1,922.00 | 902.00 | 46.93 |
| | ቅ/ቅመም | ቶን | 12,880.25 | 14,029.00 | 8,532.20 | 60.82 |
| | **የተመረተ የሆርቲካልቸር ምርት (ድምር)** | **ቶን** | **309,857.00** | **363,267.00** | **326,917.00** | **89.99** |
| | አበባ | ቶን | 101,579.00 | 118,857.00 | 112,996.00 | 95.07 |
| | አትክልት | ቶን | 173,115.00 | 200,768.00 | 177,729.00 | 88.52 |
| | ፍራፍሬ | ቶን | 35,163.00 | 43,642.00 | 36,192.00 | 82.93 |
| | **የተመረተ የስጋና ወተት ምርት** | | **16,359.12** | **18,938.28** | **22,932.12** | **100+** |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የበግና ፍየል ስጋ | ቶን | 13,269.48 | 15,510.24 | 17,204.59 | 100+ |
| | የዳልጋ ከብት ስጋ | ቶን | 226.03 | 219.48 | 359.15 | 100+ |
| | የእርድ ተረፈ-ምርት | ቶን | 2,304.38 | 2,618.80 | 4,632.76 | 100+ |
| | የዓሣና ሌሎች ስጋ ምርት | ቶን | 313.42 | 342.89 | 523.68 | 100+ |
| | ማር | ቶን | 16.81 | 13.46 | 53.91 | 100+ |
| | ሰም | ቶን | 229.00 | 233.41 | 158.02 | 67.70 |
| | ወተት | ሊትር | 1,176,830.00 | 1,229,300.00 | 805,595.00 | 65.53 |
| | **ከተለያዩ የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት የተገኘ ገቢ** | | **1,538.29** | **1,840.45** | **2,083.74** | **100+** |
| | **የቡና፣ ሻይና ቅ/ ቅመም (ድምር)** | **በሚ/ን ዶላር** | **925.68** | **1,155.33** | **1,351.04** | **100+** |
| | ቡና | በሚ/ን ዶላር | 907.04 | 1,135.02 | 1,424.60 | 100+ |
| | ሻይ | በሚ/ን ዶላር | 2.93 | 3.07 | 1.88 | 61.21 |
| | ቅ/ቅመም | በሚ/ን ዶላር | 15.71 | 17.24 | 17.85 | 100+ |
| | **የሆርቲካልቸር ምርቶች (ድምር)** | **በሚ/ን ዶላር** | **531.48** | **589.89** | **612.59** | **100+** |
| | አበባ | በሚ/ን ዶላር | 470.62 | 508.02 | 522.90 | 100+ |
| | አትክልት | በሚ/ን ዶላር | 47.49 | 65.90 | 71.53 | 100+ |
| | ፍራፍሬ | በሚ/ን ዶላር | 13.37 | 15.95 | 18.16 | 100+ |
| | **የስጋና ወተት ምርቶች (ድምር)** | **በሚ/ን ዶላር** | **81.13** | **95.23** | **120.11** | **100+** |
| | የበግና ፍየል ስጋ | በሚ/ን ዶላር | 72.71 | 85.23 | 104.29 | 100+ |
| | የዳልጋ ከብት ስጋ | በሚ/ን ዶላር | 0.79 | 1.37 | 1.44 | 100+ |
| | የእርድ ተረፈ-ምርት | በሚ/ን ዶላር | 5.62 | 6.43 | 12.77 | 100+ |
| | የዓሣና ሌሎች ስጋ ምርት | በሚ/ን ዶላር | 0.06 | 0.07 | 0.66 | 100+ |
| | ማር | በሚ/ን ዶላር | 0.07 | 0.07 | 0.22 | 100+ |
| | ሰም | በሚ/ን ዶላር | 1.76 | 1.92 | 1.16 | 60.52 |
| | ወተት | በሚ/ን ዶላር | 0.12 | 0.13 | 0.10 | 72.16 |
| V | **የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት** | | | | | |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **የምርምር ጥናቶች** | **ቁጥር** | **2,269.00** | **2,584.00** | **2,490.00** | **96.36** |
| | **የምርምር ውጤቶች** | | **458.00** | **491.00** | **420.00** | **85.54** |
| | ቴክኖሎጂ | ቁጥር | 104.00 | 133.00 | 111.00 | 83.46 |
| | መረጃ | ቁጥር | 354.00 | 358.00 | 309.00 | 86.31 |
| | **ቴክኖሎጂ ብዜት** | | | | | |
| | **አራቢ ዘር (የሰብል ዝርያዎች)** | | | | | |
| | ኩንታል | በሺህ ኩ/ል | 1.53 | 1.35 | 1.47 | 100+ |
| | ቁርጥራጭ | በሺህ ቁጥር | 391.20 | 372.20 | 463.50 | 100+ |
| | ችግኝ | በሺህ ቁጥር | 21.50 | 91.95 | 136.54 | 100+ |
| | ቀንበጥ | በሺህ ቁጥር | 3.00 | 22.00 | 23.49 | 100+ |
| | **ቅድመ-መስራች ዘር (የሰብል ዝርያዎች)** | | | | | |
| | ኩንታል | በሺህ ኩ/ል | 8.11 | 9.54 | 7.18 | 75.32 |
| | ቁርጥራጭ | በሺህ ቁጥር | 7,038.00 | 8,152.00 | 7,562.00 | 92.76 |
| | ችግኝ | በሺህ ቁጥር | 383.13 | 24.00 | 21.00 | 87.50 |
| | **መስራች ዘር (የሰብል ዝርያዎች)** | | | | | |
| | ኩንታል | በሺህ ኩ/ል | 3.76 | 7.03 | 6.33 | 90.11 |
| | **የእንስሳት መኖ ዝርያዎች** | | | | | |
| | ኩንታል | በኩ/ል | 579.70 | 122.00 | 166.10 | 100+ |
| | ቁርጥራጭ | በሺህ ቁጥር | 844.49 | 25,000.00 | 38,500.00 | 100+ |
| | ችግኝ | በሺህ ቁጥር | 352.65 | 5.39 | 7.64 | 100+ |
| | ጊደሮች | ቁጥር | 176.00 | 160.00 | 155.00 | 96.88 |
| | በጎች | ቁጥር | 608.00 | 320.00 | 348.00 | 100+ |
| | ኮርማዎች | ቁጥር | 376.00 | 25.00 | 24.00 | 96.00 |
| | የዓሣ ጫጩት | ቁጥር (በሺህ) | 1,066.80 | 1,150.00 | 1,062.90 | 92.43 |
| | እንቁላል ጣይ የሐር ትል | ቁጥር | 1,250.00 | 1,550.00 | 1,510.00 | 97.42 |
| | ፍየል | ቁጥር | 107.00 | 100.00 | 120.00 | 100+ |
| | የራይዞቢያ ሕያው-ማዳበሪያ (ባዮፈርቲላይዘር) | ፓኬት | 7,100.00 | 7,000.00 | 7,148.00 | 100+ |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቨርሚ ኮምፖስት ትል | ኩንታል | 2.83 | 2.00 | 3.60 | 100+ |
| | ቨርሚ ኮምፓስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) | ኩንታል | 28.00 | 30.00 | 60.51 | 100+ |
| | የቅድመ-ምርትና ድሕረ- ምርት የግብርና መሳሪያዎች | ቁጥር | 549.00 | 206.00 | 185.00 | 89.81 |
| | ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ | የተሳታፊ ቁጥር | 41,886.00 | 30,883.00 | 31,609.00 | 100+ |
| | ቴክኖሎጂ ማስፋፋት | የተሳታፊ ቁጥር | 47,076.00 | 20,914.00 | 23,975.00 | 100+ |
| VI | ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | | | | | |
| | ህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር | | | | | |
| | የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባለት እድገት በገጠር | በመቶኛ | 44.00 | 48.00 | 47.00 | 97.92 |
| | የላቀ አገልግሎት የሚሰጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት | በመቶኛ | 22.70 | 45.00 | 44.00 | 97.78 |
| | የኅ/ሥራ እና የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡ በግብርና ዘርፍ ላይ የተደራጁ ኅ/ሥ/ማህበራት | በመቶኛ | 10.00 | 15.00 | 14.00 | 93.33 |
| | የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦትን ማሳደግ | | | | | |
| | የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት | በመቶኛ | 98.35 | 98.50 | 92.00 | 93.40 |
| | በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚባዛ ምርጥ ዘር መጠን | በቶን | 36,510.00 | 38,600.00 | 35,760.00 | 92.64 |
| | የፀረ-አረም፣ የፀረ-ተባይ እና በሽታ ግብዓቶች አቅርቦት | በቶን | 553.00 | 581.00 | 482.00 | 82.96 |
| | የኅ/ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ግብይት ማሳደግ | | | | | |
| | የኅ/ሥ/ማህበራት የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ግብይት ድርሻ | በመቶኛ | 20.00 | 24.00 | 22.30 | 92.92 |
| | ኅ/ሥ/ማህበራት ግብርና ምርቶች የወጪ ግብይት ዶላር ድርሻ | በመቶኛ | 17.00 | 22.00 | 15.50 | 70.45 |
| | ኅ/ሥራ/ማህበራት ግብርና ምርቶች የወጪ ግብይት መጠን ድርሻ | በመቶኛ | 11.00 | 16.00 | 10.00 | 62.50 |
| | በግብርና ኅ/ሥራ ማህበራት የተቋቋሙ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | በቁጥር | 1,699.00 | 111.00 | 20.00 | 18.02 |
| | የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን | በቢሊ. ብር | 2.80 | 3.00 | 3.14 | 100+ |

| ተ.ቁ. | የቁልፍ ውጤት አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም/ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሚሰጥ ብድር መጠን | በቢሊ. ብር | 3.80 | 3.00 | 6.85 | 100⁺ |
| | ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር | ቁጥር | 30,000.00 | 20,000.00 | 457,562.00 | 100⁺ |
| | የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር | ቁጥር | 12,611.00 | 21,058.00 | 19,435.00 | 92.29 |
| | የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት | ቁጥር | 5,756.00 | 1,000.00 | 2,289.00 | 100⁺ |
| | የኅብረት ሥራ ማህበራትን ካፒታል ማሳደግ | በቢሊ. ብር | 2.88 | 2.28 | 2.39 | 100⁺ |

**አባሪ ሁለት ፡- የ2014 ዓ.ም የግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት መደበኛ በጀት ዕቅድ አፈጻጸም**

| ተ. ቁ | ፕሮግራም/ን/ፕሮግራም | የ2014 ዓ.ም መደበኛ በጀት (በሚ/ን ብር) | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም በመቶኛ | |
| I | **ግብርና ዘርፍ (ሀ+ለ)** | **2,277.14** | **3,173.78** | **139.38** | |
| ሀ | **ግብርና ሚኒስቴር** | **548.09** | **1,537.64** | **280.54** | |
| 1 | **የስራ አመራር አስተዳደር** | **254.35** | **282.22** | **110.96** | |
| 1.1 | ሥራ አመራር | 79.35 | 121.52 | 153.14 | ከዕቅድ በላይ የመጣበት ምክንያት ከሌላ ክፍል በጀት ዝውውር ስለተፈፀመ ነው፡፡ |
| 1.2 | የሰቆጣ ቃልኪዳን ስምምነት | 175.00 | 160.71 | 91.83 | |
| 2 | **የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት** | **175.96** | **1,064.64** | **605.05** | |
| 2.1 | ኤክስቴንሽን | 5.76 | 4.84 | 84.03 | |
| 2.2 | እርሻ እንቨስትመንት | 5.68 | 4.45 | 78.42 | |
| 2.3 | ሰብል ምርትና ምርታማነት | 5.64 | 4.56 | 80.89 | |
| 2.4 | ልዩ ድጋፍ | 7.23 | 5.20 | 71.92 | |
| 2.5 | ዕፅዋት ጥበቃ | 143.53 | 1,038.50 | 723.54 | ተጨማሪ 900.55 ሚ/ን ብር ለአውሮፕላን ግዢ በጀት በመፈቃዱ ነው፡፡ |
| 2.6 | ሜካናይዜሽን | 2.62 | 2.47 | 94.18 | |
| 2.7 | አነስተኛ ይዞታ ሆርቲካልቸር | 5.50 | 4.61 | 83.91 | |
| 3 | **የተፈጥሮ ሀብት ልማት** | **43.47** | **59.71** | **137.35** | |
| 3.1. | ተፈጥሮ ሀብት | 6.23 | 5.74 | 92.17 | |
| 3.2. | ገጠር መሬት አስተዳደር | 6.45 | 6.05 | 93.72 | |
| 3.3. | አፈር ካርታ | 3.56 | 2.27 | 63.76 | |
| 3.4. | አፈር ለምነት | 4.08 | 3.49 | 85.54 | |
| 3.5. | አነስተኛ መስኖ | 4.00 | 3.52 | 88.00 | |
| 3.6. | ምግብ ዋስትና | 4.12 | 2.94 | 71.26 | |
| 3.7. | ገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ | 7.66 | 5.48 | 71.54 | |
| 3.8. | ሰርዶ የተቀናጀ ግብርና ልማት | 7.37 | 30.22 | 410.10 | ተጨማሪ የወጣቶች ማቋቋሚያ 26.78 ሚ/ን ከገንዘብ ሚኒስቴር በመሰጠቱ ነው፡፡ |
| 4 | **የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት** | **51.49** | **115.56** | **224.42** | |

| ተ. ቁ | ፕሮግራም/ን/ፕሮግራም | የ2014 ዓ.ም መደበኛ በጀት (በሚ/ን ብር) | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም በመቶኛ | |
| 4.1. | መኖ ልማት | 4.69 | 3.94 | 84.10 | |
| 4.2. | ወተት ምርት | 2.90 | 2.39 | 82.46 | |
| 4.3. | ሥጋ ፤ ቆዳና ሌጦ | 2.83 | 2.39 | 84.40 | |
| 4.4. | ዶሮ ምርት | 3.82 | 3.03 | 79.34 | |
| 4.5. | ዓሳ ሀብት | 3.45 | 2.69 | 77.85 | |
| 4.5. | ማርና ሰም | 3.15 | 2.75 | 87.31 | |
| 4.6. | እንስሳት በሽታ መረጃ አያያዝ ኢፒዲዮሞሎጂ | 2.93 | 1.88 | 64.16 | |
| 4.7. | እንስሳት በሽታ መከላከል | 18.78 | 89.30 | 475.51 | ተጨማሪ 70 ሚ/ን ብር ለተለያዩ የድንበር ዘለል በሽታዎች የእንስሳት ክትባት አገልግሎት በመፈቃዱ ነው፡፡ |
| 4.8. | ከእንስሳት ወደ ሰዉ የሚተላለፍ በሽታዎች | 6.93 | 5.67 | 81.82 | |
| 4.9. | የከተሞች ግብርናና እንስሳት ኢንቨስትመንት | 2.01 | 1.52 | 75.37 | |
| **5** | **የግብአት፣ ግብይትና ኢንቨስትመንት** | **22.82** | **15.52** | **67.99** | |
| 5.1. | እንስሳት ግብዓት ግብይትና አቅርቦት | 2.64 | 2.47 | 93.43 | |
| 5.2. | እንስሳትና እንስሳት ምርት ግብይት | 4.40 | 3.34 | 75.92 | |
| 5.3. | ግብይት መሰረተ ልማት | 2.90 | 2.24 | 77.37 | |
| 5.4. | ግብርና ግብዓት ግብይትና አቅርቦት | 3.58 | 2.83 | 78.99 | |
| 5.5. | እንስሳት ልማት ኢንቨስትመንት | 3.09 | 2.42 | 78.40 | |
| 5.6. | ሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት | 6.22 | 2.22 | 35.71 | |
| **ለ** | **የ8 ተጠሪ ተቋማትየ (ኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ሳይጨምር)** | **1,729.05** | **1,636.13** | **94.63** | |
| 6.1 | የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት | 128.35 | 101.03 | 78.72 | |
| 6.2 | ኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | 926.59 | 897.98 | 96.91 | |
| 6.3 | የኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት | - | - | - | |
| 6.4 | የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት | 108.35 | 86.18 | 79.54 | |
| 6.5 | የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን | 105.42 | 101.87 | 96.64 | |
| 6.6 | የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን | 73.96 | 77.73 | 105.10 | |
| 6.7 | የኢትዮጵያ ደን ልማት | 232.30 | 220.60 | 94.96 | |
| 6.8 | የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን | 68.40 | 68.40 | 100.00 | |
| 6.9 | የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት | 85.68 | 82.34 | 96.10 | |

**አባሪ ሦስት ፡- የ2014 ዓ.ም የግብርና ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማት የካፒታል በጀት ዕቅድ አፈጻጸም**

| ተ. ቁ | የፕሮጀክት ስም | ፕሮጀክት ኮድ | የ2014 ዓ.ም ካፒታል በጀት (በሚ/ን ብር) | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም በመቶኛ | |
| **I** | **የግብርና ዘርፍ ድምር (ሀ+ለ)** | | **15,707.24** | **18,969.56** | **120.77** | |
| **ሀ** | **ግብርና ሚኒስቴር** | | **15,175.51** | **18,670.09** | **123.03** | |
| **1** | **የስራ አመራር አስተዳደር** | | **38.41** | **14.84** | **38.62** | |
| 1.1 | የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግንባታ ኘሮጀክት | 211/01/01/00/001 | 38.41 | 14.84 | 38.62 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| **2** | **የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት** | | **1,658.19** | **2,792.67** | **168.42** | |
| 2.1 | የግብርና ዕድገት ፕሮጀክት | 211/02/01/01/002 | 914.07 | 2,198.87 | 240.56 | የተፈቀደው በጀት በላይ አፈፃፀም የመጣበት ምክንያት ከእርዳታና ብድር ከተፈቀደው በላይ ስለተገኘ ነው፡፡ |
| 2.2 | የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ ሰጪ ፕሮጀክት | 211/02/01/01/001 | 500.00 | 491.80 | 98.36 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 2.3 | የግብርና እሴት ሰንሰለት ልማት ፕሮጀክት | 211/02/01/01/006 | 244.09 | 101.97 | 41.78 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 2.4 | የዘር ጥራት ቁጥጥር አቅም ግንባታ ፕሮጀክት | | 0.03 | 0.03 | 100.00 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| **3** | **የተፈጥሮ ሀብት ልማት** | | **11,741.77** | **13,798.95** | **117.52** | |
| 3.1 | ዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት | 211/03/01/01/001 | 1,238.50 | 887.00 | 71.62 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 3.2 | ተሳትፎአዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | 211/03/01/01/005 | 997.55 | 720.19 | 72.20 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 3.3 | ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም | 211/03/07/01 | 9,000.72 | 11,695.68 | 129.94 | ተፈቀደው በጀት በላይ አፈፃፀም የመጣበት ምክንያት ከእርዳታ ከተፈቀደው በላይ ስለተገኘ ነው፡፡ (የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት) |
| 3.4 | የተቀናጀ የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች የመስኖ ልማት ፕሮጀክት | 211/03/01/01/009 | 505.00 | 496.08 | 98.23 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| **4** | **የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት** | | **1,737.14** | **2,063.63** | **118.79** | |
| 4.1 | የኢትዮጵያ እንስሳት ጤና ለገጠር ልማት ፕሮጀክት/HEARD/ | 211/08/05/00/001 | 44.16 | 27.40 | 62.05 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 4.2 | ክፍለ አህጉራዊ የአርብቶ አደር ኑሮ መቋቋሚያ ፕሮጀክት/RPLRP/ | 211/08/03/01/002 | 170.77 | 793.18 | 464.48 | ከተፈቀደ በላይ ከአበዳሪ ተቋም ስለተገኘ በጀቱ ለላቦራቶር እቃ ግዢ እና ለመስሪያ ቤቱ ፈርኒቸር ግዢ ተጠቅሟል (የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት) |
| 4.3 | በኢጣሊያን ልማት ትብብር /AICS/ የሚደገፍ ድርቅ መቋቋምና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት /በአፋር ክልል/ | 211/08/03/01/004 | 159.07 | 11.68 | 7.34 | አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በበጀት አመቱ የጣሊያን ኢምባሲ ከደሞወዝ ውጪ በጀት ስላልተለቀቀ |

| ተ. ቁ | የፕሮጀክት ስም | ፕሮጀክት ኮድ | የ2014 ዓ.ም ካፒታል በጀት (በሚ/ን ብር) | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም በመቶኛ | |
| | | | | | | ነው። (የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት) |
| 4.4 | የድርቅ መቋቋምና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም 1 | 211/08/03/01/001 | 215.59 | 117.66 | 54.58 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 4.5 | ድርቅ መቋቋምና ዘላቂ የአርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም 2 | 211/08/03/01/003 | 210.88 | 163.98 | 77.76 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 4.6 | የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ፕሮጀክት/LFSDP/ | 211/06/08/01/00/001 | 808.97 | 836.85 | 103.45 | የተፈቀደው በጀት በላይ አፈፃፀም የመጣበት ምክንያት ብድር ከተፈቀደው በላይ ስለተገኘ ነው። (የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| 4.7 | ክፍለ ሃገራዊ የድርቅ መቋቋሚያና ማጠናከሪያ ፈንድ ፕሮጀክት /KfW/ ድጋፍ ፕሮጀክት | 211/08/03/01/005 | 127.70 | 112.88 | 88.39 | የግብርና ሚ/ር ፕሮጀክት |
| **ለ** | **የ6 ተጠሪ ተቋማት** (የኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ሣይጨምር) | | **531.73** | **299.48** | **56.32** | |
| **5.1** | **የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት** | | **8.66** | **3.58** | **41.39** | |
| 5.1.1 | የአርባ ምንጭ ከተማ የብሄራዊ የገንዲ በሽታ ማጥፊያና መቆጣጠሪያ የማእከል ቢሮ ግንባታ፣ | 248/01/01/00/001 | 8.00 | 2.92 | 36.55 | የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ፕሮጀክቶች |
| 5.1.2 | የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል የጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፕሮጀክት | 211/08/07/01/002 | 0.36 | 0.36 | 100.00 | |
| 5.1.3 | የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል የአጥር ሥራ ፕሮጀክት | 211/08/07/01/003 | 0.30 | 0.30 | 100.00 | |
| **5.2** | **የኢትዮጵያ ደን ልማት** | | **250.00** | **113.75** | **45.50** | |
| 5.2.1 | የአካባቢና የደን ምርምር ላብራቶሪ ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት | 249/03/03/00/001 | 166.57 | 69.03 | 41.45 | የኢትዮጵያ ደን ልማት ፕሮጀክቶች |
| 5.2.2 | የእንጨት ቴክኖሎጂ ምርምር ላብራቶሪ ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት | 249/03/03/00/002 | 83.43 | 44.72 | 53.60 | |
| **5.3** | **የእንስሳትና እንስሳት ውጤቶች ጥራት ፕሮጀክት** | **211/08/04/01/001** | **48.74** | **0.07** | **0.14** | የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ፕሮጀክት (ለተሰሩ ሥራዎች ክፍያ ሳይፈፀም በመጨረሻ ክፍያ ቢመጣም የኦዲተር ፊርማ እየተጠባቀ ይገኛል) |
| **5.4** | **ኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን** | | **125.00** | **106.42** | **85.14** | |
| 5.4.1 | የቡናና ሻይ ባለሥልጣን የህንፃ ጥገና ፕሮጀክት | 256/01/01/00/001 | 25.00 | 41.71 | 166.84 | የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን |

| ተ. ቁ | የፕሮጀክት ስም | ፕሮጀክት ኮድ | የ2014 ዓ.ም ካፒታል በጀት (በሚ/ን ብር) | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም በመቶኛ | |
| 5.4.2 | ተግባራዊ የቡና ድጋፍ በኢትዮጵያ ፕሮጀክት | 256/02/01/00/001 | 100.00 | 64.71 | 64.71 | ፕሮጀክቶች (የህንጻ ጥገና ፕሮጀክት በጀት ከእቅድ በላይ የመጣበት ምክንያት ከገንዘብ ሚንስቴር ተጨማሪ 17 ሚሊየን ስለተጨመረ ነው።) |
| **5.5** | **የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት** | | **39.33** | **38.20** | **97.12** | |
| 5.5.1 | ቃሊቲ የቢሮና የኮርማ በረት ግንባታ ፕሮጀክት | 258/02/01/00/001 | 6.69 | 6.49 | 96.99 | የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ፕሮጀክቶች |
| 5.5.2 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ባዮሴኩሪቲ አጥር ግንባታ ፕሮጀክት | 258/02/01/00/002 | 32.64 | 31.71 | 97.15 | |
| **5.6** | **የላብራቶሪ ግንባታ ፕሮጀክት** | **214/02/04/00/001** | **60.00** | **37.45** | **62.42** | የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት |